የ97ን ምርጫና ያስከተለውን ውዝግብ፣ የካርድ ንጥቂያና የአቤቱታ ሰሚ ማጣትን በተመለከተ አንዳርጋቸው ጽጌ ፓርላማ አለመግባት ጋር የተወሰደውን እርምጃ በተመለከተ የሚከተለውን እውነታ ጽፎ ነበርና እሱን እዚህ ውስጥ ማካተቱ ጥሩ ግንዛቤ ይሰጣል አንዳርጋቸው ኢህአዴግንም ቅንጅትንም በሚገባ ስለሚያውቅ ለፍረድ አሰጣጥ ስለሚያመች አቅርቤዋለሁ::

**መስከረም 1998**

## ቅንጅትና የግንቦት 7ቱ ምርጫ መጭበርበር ያስነሳቸው ጥያቄዎች

## ከአንዳርጋቸው ጽጌ

### መንደርደሪያ

የግንቦት 7ቱ ምርጫ መጭበርበሩ ከታወቀ በኋላ፣ ወያኔ ከህዝብ የዘረፈውን ድምጽ ለማስመለስ ቅንጅት ቃል ገብቶ የተለያዩ እንቅስቃሴችዎን አድርጓል:: ቅንጅት ሰላማዊና ህጋዊ የትግል አቅጣጫ በመከተል፣ ወደ ፍርድ ቤት በመሄድ፣ በራሱ በምርጫ ቦርድ መድረክ ላይና በዲፕሎማሲያዊው ዘርፍ ትግል በማድረግ በወያኔ የተዘረፈውን የህዝብ ድምጽ ለማስከበር ብዙ ጥሯል::

የተሰረቀውን የህዝብ ድምጽ ለማስመለስ መደረግ የነበረበትን ጥረት ሁሉም የምደግፊው ቢሆንም ወደ ፍርድ ቤትና ወደ ምርጫ ቦርዱ እየተመላለሱ የመሄዱ የትግል አቅጣጫ የህዝብን ድጋፍ ሙሉ በሙሉ ያገኘ ነበር ማለት ግን አይቻልም:: ይህ አመለካከት የሃገር ቤቱንም ሆነ በውጭ ሃገር ቅንጅትን የሚደግፈውን አብዛኛውን ህዝብ ያካተተ ነበር:: ወያኔ አምባገነን ስለሆነ ከዚህ የበለጠ ጠንካራ የሆነ የሰላማዊ ተቃውሞ እንጂ፣ራሱ በፈጠራቸው ፍርድ ቤት ዳኞችና የምርጫ አስፈጻሚ አካላት፣እንዲሁም የራሳቸውን ብሄራዊ



ጥቅም አስቀድመው በሚያስሉና በወያኔ ኪስ ውስጥ ቀድሞውኑ በተያዙ የውጭ መንግስታት አማካይነት የህዝብን ድምጽ ማስከበር እንደማይቻል የተሟገቱ በርካቶች ነበሩ:: ያም ሆነ ይህ ፍርድ ቤትን፣ ምርጫ ቦርድንና አለምአቀፍ ህብረተሰቡን በመጠቀም የህዝብ መብት ማስከበር ባይቻልም፣ ጥረቶቹ ሁለት መሰረታዊ ቁምነገሮች ማስረገጥ ችለዋል:: የመጀመሪያው፣ ሰላማዊና ህጋዊ ጎዳናዎች ከመርፌ ቀዳዳ ጠብበው በሚታዩበት ወቅትም እንኳን ችግሮችን ሰላማዊና ህጋዊ በሆነ መንገድ ለመፍታት ቅንጅት ያለውን የእምነት ጽናት ማረጋገጥ የተቻለበት ነው:: በዚህም ወያኔ እራሱን ብቻ ለሰላም አሳቢና ተጨናቂ እያደረገ የሚያቀርበውን ጨኸት ባዶነት አረጋግጧል:: የወያኔን የግድያ፣ የአፈናና የወከባ ትንኮሳዎች በትእግስት በማሳለፍ ለሰላምና መረጋጋት ከወያኔ በላይ ቅንጅት እንደሚጨነቅ አስመስክሯል::

ሁለተኛው፣ በሃገሪቱ ውስጥ ከወያኔ በጎ ፈቃድ ውጭ የሚንቀሳቀሱ የፍትህም ሆነ የምርጫ አስፈጻሚ አካላት እንደሌሉ አረጋግጧል:: ወያኔም ከባዶ ጩኸት ያለፈ የዴሞክራሲ፣ የፍትህና የሰላም እምነት ያልዘራበት እንደሆነ ለሁሉም ማሳየት ችሏል:: ይህ በተለይ፣ ወያኔ ስለራሱ ዴሞክራሲያዊነትና ሰላማዊነት በሚያሰራጨው የፕሮፓጋንዳ አስማት ደንዝዘው የነበሩትን በርካታ የውጭ መንግስታት ዲፕሎማቶችን ነጻ ለማውጣት ችሏል:: ከዚህ በኋላ የውጭ መንግስታት ለወያኔ የሚሰጡት ድጋፍ ካለ፣ ወያኔ በኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ስርአትን ለመገንባት በሚደረገው ጥረት ውስጥ አዎንታዊ ሚና ስለሚጫወት እንዳልሆነ የሃገራችን ህዝብም እንዲረዳው ማድረግ ችሏል::

በተለይ፣ ከምርጫው በፊት የነበረው አንጻራዊ ዴሞክራሲያዊ እውነታ ተጋኖ መታየት እንደሌለበት ለውጭ መንግስታት ለማሳየት፣ ማጭበርበር በተደረገባቸው ቦታዎች ላይ በተወሰደው የማጣራት ሂደት ውስጥ መሳተፉ ጠቀሜታ አስገኝቷል:: ይህም ለቅንጅትና ለህብረት ከፍተኛ ዴፕሎማሲያዊ ድል

ያጎናጸፈ ሆኗል። የአውሮፓ ህብረትና የካርተር ማዕከል ታዛቢዎች በዚህ የማጣራት ሂደት ላይ በመገኘት የወያኔን መሰረታዊ ጸረ-ዴሞክራሲያዊ ባህርያት እንዲረዱ አስችሏቸዋል።

በደሉን ለመናገር በየማጣሪያ ጣቢያው በሚመጣው የገጠር ህዝብ ላይ የወያኔ የአፈና መዋቅር እየፈጸመ የነበረውን ግፍ በአይናቸው ያዩበት ሁኔታ በአመለካከታቸው ላይ ከፍተኛ ለውጥ አስከትሏል። ሌላው ቀርቶ ተዋጊ ጀቶችን ገበሬው በሚኖርበት መንደር ላይ በጣም ዝቅ አድርጎ በማብረር ወያኔ ህዝብን ለማሸበር የሚያደርገውን ጥረት ሳይቀር የአውሮፓ ህብረት ታዛቢዎች እራሳቸው ባይናቸው ያዩትና በጆሮአቸው የሰሙት ጉድ ሆኗል። የአውሮፓ ህብረት የምርጫ ግምገማ ሙሉ ሪፖርት ገና ሳይወጣ ወያኔ ጨርቁን ጥሎ እንዲያብድ ያደረገውም ታዛቢዎቹ በማጣራት ሂደቱ ላይ ያዩትን ሽፍጥና ግፍ ዘርዝረው እንደሚያቀርቡ ስለታወቀ ነው። ይህ ሪፖርት የተቃዋሚዎችን እጅ በማጠናከር የሚጫወተውን ሚና አንኳስሰን ማየት አይገባንም።

ይሁንና ለዚህ ድል ሲባል ህዝብ የከፈለው መስዋዕትነት፣ የጠፋው ጊዜና ጉልበት የተለየ የትግል አቅጣጫ ባለመከተል የደረሰው ጉዳት ተገቢ ነው፣ ወይም አይደለም? የሚለው ክርክር አሁን ባለንበት ወቅት ዕልባት ማግኘት የሚችል ባለመሆኑ የታሪክን ፍርድ መጠበቁ የተሻለ ይመስለኛል። የእስካሁኑ የትግል አቅጣጫ በሃገራችን የነገሰውን አምባገነን የፖለቲካ ስርአት አፍርሶ ዴሞክራሲያዊነትን ማስፈን የሚችሉ የሌሎች ትግሎች አካል ሆኖ መቀጠል ከቻለ በታሪክ ፊት ጥያቄ የሚነሳበት ምክንያት አይኖርም። የተጠቀሰው ፍርድ በርካታ የታሪክ ዘመናት የሚፈጅ ሳይሆን በሳምንታትና በወራት ውስጥ የሚጠናቀቅ ነው። ቅንጅት እንዲህ አይነቱን የትግል ስልት መጠቀሙ የወያኔን አምባገነናዊ ባህርይ በሚገባ ካለማወቅ፣ ወይም ሌሎችን የሰላማዊ የትግል ዘዴዎችን ለመጠቀም አመራሩ ያልተዘጋጀ ወይም ከፍተኛ የፖለቲካ ጥበብ የተሞላው ስልት በመሆኑ፣ ወይም እኛ



የማናውቃቸው ሌሎች ችግሮች ለአመራሩ ስለሚታዩት ነውን? የሚሉት ጥያቄዎች ከአሁኑ መነሳት ጀምረዋል፣ ምላሹንም በቅርቡ የምናገኘው ይሆናል።

ፍርድ ቤትና የምርጫ አስፈጻሚ አካላትን በመጠቀም ህዝብ በጠራራ ጸሃይ የተዘረፈውን መብቱን ማስከበር አልተቻለም። እንዲያውም ውጤቱ ተጨማሪ የህዝብ ድምጽ ማዘረፍ ሆኗል። ቅንጅቱና ህብረቱ ቀደም ብለው አግኝተው ከነበረው የፓርላማ ወንበር ተቀንሶ ለወያኔ ተሰጠ። ቀደም ብለው የኢትዮጵያ ደሃ አርሶ አደሮች ከረሃብና ከአፈና መውጫ ትሆናለች በማለት በጥንቃቄ ተጠቅመው ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣናትን የቀጡባትን ድምጻቸውን ተገፈው እነበረከት ስምኦን፣ እነ አባዱላ፣ ጁነዲንና ኩባንያቸው ብቻቸውን እንደገና ለውድድር ቀርበውና የምርጫ ቲያትር ሰርተው ያለምንም ሃፍረትና ይሉኝታ "ለፓርላማ ተመረጥን" አሉ። ከዚህ በተጨማሪ ወያኔ፣ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ባሸነፉባቸው እንደ አዲስ አበባ በመሳሰሉ መስተዳደሮች እና በራሱም በፓርላማው ውስጥ ከራሱ ከወያኔ ዘረፋ የተረፈውን የህዝብ ድምጽ ይዘው ቢገቡ ምንም አይነት ስራ መስራት እንዳይችሉ ለማድረግ የተለያዩ እርምጃዎችን ወሰደ። የአዲስ አበባን መስተዳድር ገቢ ክፉኛ የሚጎዱ ውሳኔዎችን ወሰነ። የከተማውን የፖሊስ ኮሚሽን በማጠፍ ወደ ፌደራል ፖሊስ አዞረ። በኦሮሚያ ክልል መስተዳደርና በአዲስ አበባ መስተዳደር መሃከል ውጥረት ሊፈጥሩ የሚችሉ ሴራዎችን ሸረበ።በሃገሪቱ ፓርላማ ውስጥም ወያኔ የህዝብን ድምጽ በመዝረፍ ባገኘው የበላይነት የፈለገውን ሲሰራ ቢውል ተቃዋሚዎች በየወሩ ደሞዛቸውን ከመልቀም ውጭ ቃል መተንፈስ የማይችሉበትን ሁኔታ አመቻቸ። በፓርላማ ውስጥ አጀንዳ ለማስያዝ ከ51 በመቶ በላይ የፓርላማው አባል ሊደግፉት እንደሚገባና በፓርላማው ውስጥ ቅንነት የሌለው ንግግር የሚያደርግ ሰው በፖሊስ ተጠፍሮ ከፓርላማው እንደሚወገድ ደነገገ።ቅንነት የሌለው የሚለውን አባባል ተርጓሚው ራሱ ወያኔ መሆኑን ለተረዳ ደግሞ ፓርላማው ተቃዋሚዎች ቃል መተንፈስ የማይችሉበት የአፈና ቦታ እንደሚሆን መገመት አያስቸግርም።

ይህ ሁሉ የተደረገው ተቃዋሚዎች በሃገር አቀፉ ፓርላማና በየክልሉ ምክር ቤት የነበረው የአሰራር ሁኔታ ከምርጫው በኋላም እንደሚቀጥል አምነው ወደ ምርጫ ውድድሩ ከገቡ በኋላ ነው:: ምርጫ ከተደረገ በኋላ እየተበተነ የነበረን ፓርላማ በመጠቀም ከምርጫ በፊት ተቃዋሚዎች እንደሚቀጥል አስበው የተወዳደሩበትን የሃገራዊ እና ክልላዊ ምክር ቤቶች የቆየ አሰራር ሁኔታ፣ የተቃዋሚዎችን የምክር ቤት መቀመጫ ቁጥር ግምት ውስጥ እያስገቡ መሰረታዊ በሆነ መንገድ መቀየር ህገወጥ ብቻ ሳይሆን ምርጫውን እራሱን ትርጉም አልባ የሚያደርግ ኢዴሞክራሲያዊ አሰራር ነው::

የወያኔ መሪዎች ከደነዘዘ ገዥ መደብ ህሊናቸው አምልጦ የወጣውን የዴሞክራሲ ቀዳዳ እየተራወጡ መድፈን መጀመራቸውን የሚያሳይ ነው::ምርጫው የወያኔን አምባገነኖች ፓርላማ እንደሌሎች ሃቀኛ ፓርላማዎች ወጉ እንዳይቀርበት ዴሞክራሲያዊ የሚያስመስለውን ካባ ለማላበስ ብቻ የተደረገ መሆኑን የሚያሳይ ነው::

የአዲስ አበባ መስተዳድር የገንዘብና የማስፈጸም አቅም እንዲህ እንደዛሬው የተዳከመ መሆኑን ህዝብ አስቀድሞ ቢያውቅ ኑሮ ለሰአታት እህልና ውሃ ሳይቀምስ ቆሞ ምርጫ ያደርግ ነበር ወይ? ተመራጮቹስ እራሳቸውን ለውድድር ያቀርቡ ነበር ወይ? በቅርቡ በፓርላማው የተደነገገው፣ ተቃዋሚ ፓርቲዎች አንዲት አጀንዳ እንኳን ማስያዝ እንዳይችሉ የሚያደርገው አፋኝ ደንብ መኖሩ ቢታወቅ እውን ተቃዋሚዎች እራሳቸው ምርጫ ውስጥ ይገቡ ነበር?

ከላይ ከተባለው በተጨማሪ በከተማና በገጠር መብታቸውን ለማስከበር በተነሱ ንጹሃንና ሰላማዊ የሃገሪቱ ዜጎች ላይ ወያኔ ግድያ፣ እስራት፣ ድብደባና እንግልት እያካሄደ እንደነበር እናውቃለን:: ይህ ግፍ ዛሬም በተባባሰ መንገድ እንደቀጠለ ነው::እንዲህ ያለው ሁኔታ በቀጠለበት ሃገር ውስጥ ነበር ቅንጅትና ህብረት በፍርድ ቤትና በምርጫ አስፈጻሚ አካላት በኩል



የህዝብን ድምጽ ለማስመለስ ሙከራ አድርገው፣ይህ አማራጭ የትም እደማያደርስ የተረዱት:: ፍርድ ቤቱም ሆነ የምርጫ ቦርዱ ዞሮ ዞሮ፣ የፈጠራቸውን ወያኔን መጋፋት የማይችሉ በመሆናቸው፣ ነጻና ገለልተኛ ፍርድና ፍትህ ከነሱ ማግኘት አልተቻለም:: እንደማይቻልም የተቃዋሚው ፓርቲ መሪዎች ህዝብና የውጭ ማህበረሰብ ሁሉም በጋራ የተረዱት ጉዳይ ሆነ:: ከዚህ በኋላ የህዝብን መብት ለማስከበር የነበረው አማራጭ አንድ ብቻ ነበር:: ይህ ብቸኛ አማራጭ ከፍርድ ቤትና ከአስመራጭ አካላት ውጭ ያሉትን ሰላማዊና ህጋዊ የትግል አቅጣጫዎች እንደ አስፈላጊነቱና እንደአዋጭነቱ እየገመገሙ ትግሉን መቀጠል ነበር:: ይህ ሳይሆን ቀርቶ አሁንም የወያኔን አምባገነንነት ባህርይና ራሱ አምባገነንነት ምን እንደሆነ በቂ ግንዛቤ ያልጨበጠ "ቅንና የዋህ" ሌላ አማራጭ በቅንጅቱና በህብረቱ ቀረበ:: ይህ አማራጭ ወያኔን ጨምሮ ሁሉንም ተቃዋሚዎች ያቀፈ ብሄራዊ የእርቅ መንግስት እንዲቋቋም ጥሪ ማድረግ ሆነ::

ይህ አማራጭ ቀደም ብሎ በፍርድ ቤትና በምርጫ አስፈጻሚ አካላት በኩል ታስቦ ከነበረው የመፍትሄ አቋም ምንም ልዩነት የለውም በሚል የገጠመው ተቃውሞ ቀላል አልነበረም:: የፖለቲካ መሪዎቹን አካሄድ ግራ ያጋባው፣ ፍላጎቱ ወያኔን ዳግም በአይኑ ማየት የማይፈልገው፣ ለዚህም እግሩ እስኪንቀጠቀጥ ድረስ በየምርጫ ጣቢያው በመቆም«ወያኔ ወግድልኝ» በማለት ድምጹን የሰጠው የሃገሪቱ ህዝብ፣ የቀረበውን የብሄራዊ እርቅ መንግስት ሰነድ ለወያኔ እድሜ ማራዘሚያ የሚጠቅም ይሆናል በሚል ስጋት ነበር የተመለከተው:: ህዝብ ይህንን ስሜቱን የሚገልጽበት መድረክ ባለማግኘቱና በአደባባይ ባለማሳየቱ የነበረውን ጥርጣሬና ተቃውሞ አሳንሶ ማየቱ ትልቅ ስህተት ይመስለኛል::

በሃገር ውስጥም ሆነ ከሃገር ውጭ በሚገኙ የቅንጅት አባላትና ደጋፊዎች አይን፣ ይህ የብሄራዊ ዕርቅ መንግስት ሃሳብ ቅንጅት የመራጩን ድምጽ ለማስከበር የገባውን የማይነቃነቅ ቃል-ኪዳን የሚቦረቡር

መስሎ የታያቸው በርካቶች መሆናቸውን ማወቁ ተገቢ ነው:: እንዲያም ሆኖ ያለንበት ሁኔታ አስቸጋሪነት፣ የአመራሩን ጭንቀት፣ የእርቅ መንግስቱ ያካተታቸው መሰረታዊ ነጥቦች በስራ ቢውሉ በአነስተኛ መስዋእትነት የህዝብን ዴሞክራሲያዊ መብት ማስከበርና ዘለቄታ ያለው የዴሞክራሲ ስርአት መገንባት የሚያስችል ይሆናል በሚል ተስፋ ብዙዎች እያንገራገሩም ቢሆን ሃሳቡን ደገፉት::

በምርጫ የተሸነፈው ወያኔ ግን የቀረበለትን የመዳኛ ተስፋ አሽቀንጥሮ በመጣል የአንድነትና የእርቅ መንግስቱን ሃሳብ «አልቀበልም፤ አሻፈረኝ፣ እስቲ ምን ታደርጉኛላችሁ» በማለት እንደሁሉም አምባገነኖች የራሱን አምባገነናዊ ምላሽ ሰጠ:: ከአምባገነን ጋር መደራደር እንደማይቻል ይህ የመጀመሪያው ትምህርት ሊሆን በተገባ ነበር:: አምባገነኖች ሁሌም ያለነሱ «ጀግና» ና «ደፋር» ያለ ስለማይመስላቸው ለሰላም ለመረጋጋትና ለሌሎችም ከፍተኛ ሰብአዊ ራእይ ሲባል የሚቀርብላቸውን ሃሳብ ሁሌም እንደፍራቻ የሚቆጥሩ መሆናቸውን ወያኔን ከመሳሰሉ በርካታ የአለማችን አምባገነኖች ታሪክ መረዳት ነበረብን:: ከአምባገነኖች ጋር የሚደረግ ድርድር ከራሳቸው ከአምባገነኖች በቅድሚያ እንዲመጣ ማስገደድ የሚችል ህዝባዊ የትግል ስልት የቀመሩ ብቻ ናቸው፤እስከዛሬ አምባገነኖችን ማንበርከክ የቻሉት:: ከዚህ ውጭ የሰላም ዘንባባ፣ የእርቅ ሃሳብ ለአምባገነኖች ማቅረብ "በእብሪት ላይ እብሪት ደርቡ" ብሎ መጋበዝ ብቻ ነው የሚሆነው::

ፍርድ ቤቱን፣ የምርጫ አስፈጻሚ አካላትን፣ የውጭ መንግስታትን በመጠቀም፣ ከዛም አልፎ ለህዝብ ድምጽ ቀማኛው ለራሱ ለወያኔ የእርቅና የሰላም ሃሳብ አቅርቦ፤ እንኳን የተጭበረበረን የህዝብ ድምጽ ቀርቶ፣ ሕዝብ በእጁ ያስገባውን ድምጽ ከዘራፊዎች መከላከል አልተቻለም:: እንደጠቀስኩትም ህዝብ በምርጫው በሃገርና በአለም ዙሪያ መሳለቂያ ያደረጋቸው ከፍተኛ የመንግስት ባለሥልጣናት ከታሪክ ቆሻሻ መጣያ የተወረወረ የሰውነት ቡቱቷቸውን እያራገፉ የወያኔ ጠመንጃና ጥይት እንጂ የህዝብ ድምጽ ትርጉም



እንደሌለው በማሳየት በህዝብ ላይ አሽካኩ:: የወያኔ መሪም እንደተለመደው «ውሾቹም ይጮሃሉ ግመሎችም ይጓዛሉ» እያለ በማን አለብኝነት አዲስ መንግስት ለማቋቋም የሚያደርገውን ዝግጅት ቀጥሏል:: ሃገራችንንና ህዝቧን በመካድ፣ በታሪካችን ታይቶ የማይታወቅ የሃገርን ደህንነትና ጥቅም የሸጠ መሪ ከምኒልክ ግቢ ተቀምጦ በበርካታ ክሮች ከሃገራዊ አርበኝነት ጋር የተሳሰሩ ልጆቿን «የኔን አምባገነን አገዛዝ ካልተቀበላችሁ፣ አንገታችሁን ደፍታችሁ፣ ወይም ተሰዳችሁ ወይም ጫካ ገብታችሁ ትኖራላችሁ» በማለት ተመጻደቀ:: እንግዲህ እዚህ ደርሰናል::

ቅንጅት ከዚህ ወዴት ይሄዳል? ለዚህ ጥያቄ እስካሁን በአደባባይ ኦፊሴሊያዊ መልስ አልተሰጠንም:: ቅንጅት ቀጥሎ ለሚወስዳቸው እርምጃዎች እንዲረዳው የተለያዩ የህብረተሰቡን ክፍሎች እያነጋገረ የተለያዩ አማራጮች መታወቅ አልጀመሩም ማለት አይደለም:: እስካሁን በቅንጅት ከተደረጉ የውይይት መድረኮች የአጀንዳ አቀራረጽና ትኩረት እንደተረዳነው ሁለት አማራጮች በግልጽ እየወጡ ነው:: <u>የመጀመሪያው አማራጭ</u> ሰፋት ባለው ሰላማዊና ህጋዊ ትግል አማካይነት የህዝብን ድምጽ ለማስከበር በፍጥነትና በቀጣይነት መንቀሳቀስ ነው:: <u>ሌላው</u> - የተገኘውን ድምጽ ይዞ ፓርላማ በመግባት ለቀጣይ ትግል መንቀሳቀስ የሚለው ነው:: እስካሁን እንደሰማነው ሁለቱም አማራጮች በህዝብ ዘንድ ደጋፊዎች ያሏቸው ናቸው:: ይሁንና የትኛው አማራጭ ነው የበለጠ ተቀባይነት ያለው ለሚለው ጥያቄ የሚሰጠው መልስ እንደ መላሹ ፍላጎት እየተጋነነ ሲቀርብ ማየት ጀምረናል::

እስካሁን እንደታዘብኩትም በጋዜጦችም ሆነ በድረ-ገጾች ላይ እንደሚነበበው ፓርላማ ገብተን እንታገል የሚሉ ግለሰቦች አመለካከታቸውን በድፍረት መግለጽ ጀምረዋል:: ከዚህ ውጭም የውጭ መንግስታት ከወያኔ ማጭበርበር የተረፈውን ድምጽ በራሱ እንደ እድገት በመቁጠር ዋንኞቹ ፓርላማ ግቡ ባዮች ሆነዋል:: ለራሳቸው ለአንድ ሰኮንድ እንኳን በትክክለኛነቱ የማያምኑበትን የምርጫ ሂደት «ተቀበሉ» እያሉን ነው::

ለጥቁር ዘር ካላቸው ንቀት በመነሳት አፍሪቃውያን የሰው ጎደሎዎች ስለሆኑ ሰባራ ዲሞክራሲም ሲበዛባቸው ነው እያሉን ነው፡፡ የኢትዮጵያ ህዝብ የዴሞክራሲ ጥማት፣ የነጻነትና የፍትህ ፍቅር በታሪካችንና በባህላችን ውስጥ ስር የሰደደ መሰረት ያላቸው መሆናቸውን ለመረዳት ፈቃደኛ አይደሉም፡፡

ዴሞክራሲ ማለት በፍትህ፣ በእኩልነት፣ በነጻነት መርሆች ላይ የተመሰረተ የፖለቲካ ሂደት መሆኑን እያወቁ፣ ለእኛ ግን በፓርላማ ከተገኘ ወንበር ቆጠራ በላይ ትርጉም የለውም እያሉን ነው፡፡ ምርጫው፣ ተቃዋሚዎች ከእዚህ በፊት ከነበራቸው የፓርላማ ወንበር ተጨማሪ ወንበሮችን በማስገኘቱ ብቻ የህዝብን ድምጽ መዘረፍ ወደ ጎን ትተው፣ የፍትህን የእኩልነት እና የነጻነትን መርህ ረግጠው ተቃዋሚዎች ፓርላማ እንዲገቡ ከፍተኛ ጫና እያደረጉ ናቸው፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ «ፓርላማ መግባት የለበትም፡፡ ትግሉ ሰላማዊና ህጋዊ በሆነ መንገድ ቀጥሎ የህዝብ ድምጽ መከበር ይገባዋል» የሚል አመለካከት አለ፡፡ በኔ ግንዛቤ የዚህ አመለካከት ባለቤቶች ሁሉንም የሃገሪቱን ግፉአን ህዝቦች ይጠቀልላል ባይ ነኝ፡፡ ይህ አመለካከት፣ በወያኔ የ14 አመት አምባገነናዊ ስርአት ተቀጥቅጠው፣ ተዋርደው ድህነታቸው፣ ጣርና አበሳቸው ገዝፎ፣ ተስፋ ቆርጠው ሲኖሩ የነበሩና የተቃዋሚዎች መምጣት ተስፋ የዘራባቸውን በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ የሃገሪቱን ደሃ ህዝቦች በሙሉ ያካትታል፡፡ ✸ይህ ህዝብ የወያኔ ግፍ ከሚቆረጥመው ቆሎ ጋር የተቀላቀለ የጠርሙስ ድቃቂ ሆኖ የሚያደማው ነው፡፡ በሚተኛበት መደብ ስር እንደ እሾህ ተተክሎ የሚያቆስለው ነው፡፡ የወያኔ እብሪትና ዘረኝነት ጉሮሮ ውስጥ እንደሚንቀለቀል እሳት የሚለበልበው ህዝብ ነው፡፡ ይህ ህዝብ ቅንጅት በሚጠራው ከፍተኛ መስዋዕትነት በሚያስከፍል ትግል ውስጥ ቢገባ ከታሰረበት የባርነትና የድህነት ሰንሰለት በስተቀር ምንም እንደማያጣ የሚያውቅ ህዝብ ነው፡፡ ደልቷቸው እንደሚኖሩት በጣት የሚቆጠሩ ኢትዮጵያዊ ወንድሞቹና የራሳቸውን ጥቅም አስቀድመው እንዳሰቡት የውጭ መንግስታት፣ ፓርላማ የመግባት ሃሳብ



አይዋጥለትም፡፡ ባገኛቸው ጠባብ አጋጣሚዎችም ይህንን በማያሻማ ቋንቋ ተናግሯል፡፡

ይሁንና ይህ ከፍተኛ ብዛት ያለው የሃገሪቱ ህዝብ ፓርላማ መግባትንና መታገልን እንደሚደግፉት ጥቂት ወንድሞቹ፣ የጋዜጦች የድረ-ገጻትና የሬድዮኖች ሃሳብን የመግለጫ መድረኮች የሉትም፡፡ የዚህን ህዝብ አመለካከት ታሪካዊ ትርጉም በሚገባ ለማቅረብ የሚደረጉ ጥረቶች አይታዩኝም፡፡

የዚህ ጽሁፍ አላማ በዚህ ጉዳይ ላይ የራሴን ገንቢ አስተዋጽኦ ለማቅረብ ነው፡፡ የራሴን የሩቅና የቅርብ ተሞክሮ፣ እንደኛ በአምባገነኖች መዳፍ ስር ወድቀው ከነበሩ የሌሎች ሃገር ህዝቦች የነጻነት ትግል ልምድ በመነሳት፣ ከምርጫው በፊት በነበሩት ጥቂት ወራት በምርጫው ወቅትና ከዚያ በኋላ ሀገር ውስጥ በመገኘት የተለያዩ የህብረተሰቡን ክፍሎች በማነጋገር ከደረስኩበት ግምገማ በመመርኮዝ በተነሳው ጉዳይ ላይ የራሴን አስተያየት አሰፍራለሁ፡፡

እስካሁን ወደ ፓርላማ ገብቶ ትግል መቀጠል በሚለው ሃሳብ ዙሪያ የቀረቡት ሃሳቦች አሳማኝና አጥጋቢ ሆነው አላገኘኋቸውም፡፡ ከዚህም በላይ ስፋትና ጥልቀት ባለው መንገድ የፓርላማ መግባትን ጠቀሜታ ዘርዝሮ ያስቀመጠ ጽሁፍ አላየሁም፡፡ እንዲህ አይነቱ ጽሁፍ ቢኖር ለተነሳው ውይይት ጠቀሜታው የጎላ ይሆን ነበር፡፡ ይህ ሆኖም የእኔ ጽሁፍ ለጊዜው የሚያተኩረው የህዝብን መብት ለማስከበር ትግሉ ሰላማዊና ህጋዊ በሆነ መንገድ በተጠናከረ መልኩ መቀጠል አለበት የሚለውን ሃሳብ በመደገፍ ይሆናል፡፡ የሃገራችን ፖለቲካ አሁን ባለበት ሁኔታ እስከቀጠለ ድረስ የኢትዮጵያ ህዝቦች በብዙ መስዋዕትነት ያገኙትን የዴሞክረሲ ምርት ከወያኔ ዘረፋ መከላከልና ወደተሻለ የእድገት ደረጃ እንዲሸጋገር ማድረግ የሚቻለው ወያኔን በሰላማዊ የህዝባዊ እምቢተኛነት ትግል ማንበርከክ ሲቻል ብቻ ነው፡፡ ለዚህ የትግል አቅጣጫ ያለን ዝግጁነት ነው፤በኢትዮጵያ የዴሞክራሲን እጣ የሚወስነው፡፡ በዚህ ላይ የጠራ አቋም ሳይያዝና

ለእንዲህ አይነቱ ትግል አስፈላጊው ዝግጅት ሳይደረግ ፓርላማ መግባትና አለመግባት የሚሉት አማራጮች በእኩልነት መቀመጥ የሚችሉ አማራጮች ሊሆኑ አይችልም።

ፓርላማ አትግቡ የሚለውን የአብዛኛውን ህዝብ አመለካከት የምደግፈው እኔም እንደ ህዝቡ ፓርላማ አለመግባት ወያኔን ለማስገደድ መደረግ ላለበት የሰላማዊና የህዝባዊ እምቢተኛነት ትግሉ አንድ አካል አድርጌ ስለማየው ብቻ ነው። ፓርላማ አለመግባት በኩርፊያ ዙሪያ ታጥሮ ብቻ ይቀራል የሚል እምነት ስለሌለኝ ነው። ፓርላማ አለመግባት በወያኔ አምባገነንነት ባህርይ ላይ የተያዘ ግልጽነት ያለው አቋም መግለጫ ነው ብዬ ስለማምን ነው። ከእንዲህ አይነቱ አምባገነን ሃይል ጋር የሚደረገው ትግል በዋንኛነት፣ የህዝባዊ እምቢተኛነትና የአልገዛም ባይነትን ትግል በማቀጣጠል እንደሆነ በማያሻማ ቋንቋ ስለሚያስቀምጥ ነው። ፓርላማ የመግባቱ ሃሳብ ግን በወያኔ መሰረታዊ ባህርይና ከወያኔ ጋር ለሚደረገው ትግል ግልጽነት የሌለውና የተምታታ መልእክት የሚያስተላልፍ ነው የሚል እምነት አለኝ።

ለምን እንዲህ አይነቱ የውይይት አጀንዳ አሁን ተከሰተ? ይህ ውይይት እንዴት ቢስተናገድ ገንቢ ውጤት ያስገኛል? ፓርላማ መግባት ወይም አለመግባት በሚለው ጥያቄ ዙሪያ ምላሻችን ምን ይሁን የሚሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ አስተያየቶቼን በሚቀጥሉት ንኡስ ርእሶች ስር ከፋፍዬ አቀርባለሁ።

ግልጽነት ያልነበረው የቅድመ ቅድመ-ምርጫ ግምገማ ።

ከግንቦት 7ቱ ምርጫ በፊት በሁለት መሰረታዊ ጉዳዮች ላይ የአመለካከት ግልጽነት አልነበረም። አንዱና ዋንኛው ወያኔ በመሰረተ ባህርዩ አምባገነን መሆኑን ከልብና ከምር አለማየት ነው። በሃገሪቱ እንዲደረግ የተወሰነው ምርጫ ከዚህ አምባገነናዊ ባህርዩ ጋር በበርካታ ክሮች የተሳሰረ መሆኑንና በእንዲህ አይነቱ



ምርጫ በመሳተፍ የወያኔ ተቃዋሚዎች የሚገጥሟቸውን ፈተናዎችና መፍትሄቻቸውን በሚገባ አንጥሮ አለማስቀመጥ ነው።

ሁለተኛው፣ በአጠቃላይ የሃገሪቱ ህዝብ ምን ያህል በወያኔ አገዛዝ እንደተማረረና እንደተንገሸገሸ፣ ከዚህ ምሬቱ ሊያወጡት ለሚነሱ የፖለቲካ ድርጅቶች ሊሰጥ ስለተዘጋጀው ድጋፍና ለመክፈል ስለሚችለው መስዋዕትነት፤ ሰላማዊና ህጋዊ በሆነ መንገድ የፖለቲካ ስርአት መቀየር ይቻላል ብሎ ማመን ስለመቻሉና ይህንን እምነቱን በተግባር ለመተርጎም ያለውን ብቃት በሚመለከት በተቃዋሚ ፓርቲዎች አካባቢ የነበረው ግንዛቤ ግልጽነት ያልነበረው መሆኑ ነው።

የወያኔን፡አምባገነንነት፤በሚገባ፡ለመገምገም አለመቻል።

በቅድሚያ ሁላችንም መረዳት ያለብን ነጥብ አለ። ስለቅንጅት ስናወሳ ቅንጅት እንደ አንድ ድርጅት በምርጫው ለመሳተፍ የወሰነው ምርጫው ጥቂት ወራት ሲቀሩት እንደሆነ ነው። በእነዚህ ጥቂት ወራት ውስጥ ለምርጫ የሚሆን በሃገሪቱ የፖለቲካ ታሪክ ታይቶ የማይታወቅ የምርጫ ማኒፌስቶ አዘጋጅቷል። ማኒፌስቶው ዝርዝር በመሆኑ የተነሳ በጋራ ተቀባይነት እንዲያገኝ የድርጅቶቹን ጊዜና ጉልበት የበላ እንደነበር መገመት አያስቸግርም። ቅንጅት በየቦታው የሚያቀርባቸውን እጩ ተወዳዳሪዎቹን ለማቅረብ የገጠመውን አስቸጋሪ ስራ ለመወጣትም ምን ያህል ግዜንና ጉልበትን እንደተሻማበት ግልጽ ነው። ሁሉም ለየራሱ ድርጅት አባላት ቅድሚያ የሚሰጥበት የፖለቲካ ባህል ጠንካራ በነበረበት ሃገር ውስጥ አራት ድርጅቶች በጋራ የተስማሙባቸውን እጩዎች በነበረው አጭር ጊዜ ውስጥ ማቅረብ ህዝብን ያስደሰተና ወያኔን ያስደነገጠ ታሪካዊ ክንዋኔ ነው። ይህ በእንዲህ እንዳለ የምርጫው ዘመቻ የተጀመረበት ሁኔታ ተደራርቦ መጣ። የምርጫውን ዘመቻ ለማካሄድ የሚሰራው ስራ ዝርዝሩ የማያልቅ ሆነ።

የገንዘብ አቅም፣ በየቦታው የሚያጋጥሙ በወያኔ የሚፈጠሩ እንቅፋቶችና ሌሎችም ችግሮች የቅንጅትን አመራር ወጥረውና ጠምደው ያዙት። የቀን ተቀን ችግሮችን እየተከታተሉ በመፍታት ስራ ተጠመደ። ለምርጫው ዝግጅት መደረግ ከተጀመረባቸው ጥቂት ቀናት በኋላ ቅንጅት ረጋ ብሎ ሁኔታዎችን አስቀድመው በተሰሉ ስልቶችና ግቦች አማካይነት የሚሰራበት ሁኔታ ነበር ለማለት አስቸጋሪ ነው። የሚፈጠሩ አዳዲስ ሁኔታዎች እየተከተሉ ምላሻቸውን መስጠት ካልሆነ በስተቀር ቅንጅት ሀኔታዎችን እራሱ በፈለገው አቅጣጫ መወሰን የሚችል አልሆነም። ቅንጅት እንደ ድርጅት ረጅም እድሜ ባለማግኘቱ ሰፋት ባለው ጥናትና ትንታኔ ላይ የቆመ የፖለቲካ ትግል እስትራተጂና ስልት ከዚህም ጋር የሚሄድ መዋቅርና አደረጃጀት፣ ሌሎችም በርካታ ዝግጅቶች ሳይኖሩት ወደ ምርጫው ውድድር እንዲገባ ተገዷል። በቅንጅትነት የተሰባሰቡት የተለያዩ ድርጅቶች አንዳቸው ካንዳቸው የበለጠ እድሜና ተመክሮ ስለነበራቸው የየራሳቸው ጥናቶችና ምርምሮች ሊኖራቸው ይችል ይሆናል። ይኖራቸዋልም። እንደ ቅንጅት ግን ሁሉም በጋራ የተስማሙበት ጉዳይ ቢኖር ሰላማዊና ህጋዊ የፖለቲካ ፓርቲ ሆኖ መንቀሳቀስን ብቻ መስሎ ይታየኛል።

ይህ ሰላማዊና ህጋዊ የፖለቲካ እንቅስቃሴ በውስጡ ያዘላቸውን፣ በተለይ ከምርጫው ጋር በተያያዙ ነጥቦች ዙሪያ ስለሚቀሰቀሱ ችግሮችና መፍትሄዎች የቀረቡ ጥናቶች አልነበሩም። እንዲህ አይነት ጥናቶች ባለመኖራቸው ከወያኔ አምባገነናዊ ባህርይ ሊፈልቁ ስለሚችሉ ችግሮች አስቀድሞ መፍትሄ አልተበጀላቸውም። ወያኔ በግሉ የሚቆጣጠረውን ወታደር፣ ደህንነት፣ ፖሊስና ሚሊሺያ እንዲሁም የምርጫ ቦርድ፣ ፍርድ ቤትና ፓርላማ፤ የመገናኛ ብዙሃንና የሃገሪቱን ሃብት በመጠቀም፣ የህዝብን ድምጽ ሰርቆ በስልጣን ለመቀጠል ጥቃቱን በቅንጅት ላይ ባነጣጠረበት ወቅት፣ የቅንጅት ምላሽ በየግዜው የሚመጣውን ጥቃት ከመከላከል፣ የሚቀርብበትን ክስ ከማስተባበል ያለፈ ስራ መስራት እንዳይችል አድርጎታል። ቅንጅት ያገኘው ከፍተኛ የህዝብ ድጋፍ



ተከላካይነትን ሳይሆን አጥቂነትን የሚጋብዝ ሆኖ ሳለ የተገኘውን ድጋፍ በአግባቡ መጠቀም አልተቻለም። ይህንን ማድረግ የሚችል የፖለቲካ ትግል ስትራተጂና ታክቲክ አስቀድሞ መንደፍ የተቻለበት ሁኔታ ባለመኖሩ ተሸናፊው ወያኔ እንደአሸናፊ፣ አሸናፊው ቅንጅት እንደተሸናፊ ሆነው፣ ወያኔን ለሰላም እንዲያስብ መማጠን፣ የወያኔ መሪዎች እዳይበረግጉና እስከዛሬ ድረስ ከፈጸሙት ወንጀል በላይ ሌላ ወንጀል እንዳይፈጽሙ ማባበል የተለመደ ሆነ። ይህን ከምርጫ ጋር የተፈጠረን ሁኔታ በመመልከት ነው፣ በወያኔ አምባገነናዊ ባህርይ ላይ ግልጥነት ያልነበረው ግንዛቤ ያስከተለው መዘዝ ያልኩት። በእኔ አመለካከት ቅንጅት ይህንን ሁኔታ በሚገባ ማጥናት የሚችሉ የአመራር አካላትና የድርጅት ደጋፊዎች አሉት የሚል እምነት አለኝ። ችግሩ ቅንጅት እነዚህንና ሌሎችንም ጥልቀት ያለው ትንተና የሚጠይቁ ስራዎች መስራት የቻለበት ፋታ ሳያገኝ በምርጫው ውስጥ መደፈቁ የፈጠረው ሁኔታ ነው።

ቅንጅት በተፈጠረበት አጭር ግዜ ውስጥ ያከናወናቸውን በርካታ ድርጊቶች ለተመለከተ በታምራዊነቱ የማይደነቅ የሚኖር አይመስለኝም። ይህም ተብሎ ግን፣ የምርጫ ወከባና የጊዜ ውጥረት በፈጠሩት ጫና አማካይነት ሳይሰራቸው የቀሩት የቤት ስራዎች ድርጅቱና ህዝብ ያገኛቸውን ድሎች እየቦረቦሩት መሆኑ መታወቅ አለበት። ከነዚህ ስራዎች መሃከል የወያኔን አምባገነናዊ ባህርይ በሚገባ ተረድቶ እንዲህ አይነቱ አምባገነን የራሱን ምስል ለማሳመር ከቁጥጥሬ ሊወጣ አይችልም በሚል ትምክህት በከፈተው የማስመሰል ምርጫ በመግባት ሊፈጠር ስለሚችለው ችግርና መፍትሄ በቂ ጥናት አለማድረግ አንዱ ነው። ዛሬ ፓርላማ «እንግባ ወይም አንግባ» የሚለው ጥያቄ አስቀድሞ በፖለቲካው ትግል ስትራተጂ ውስጥ ተካቶ ምላሹንም በቅድሚያ አግኝቶ እንደምርጫ ማኒፌስቶ ቁም ነገሮች ለህዝብ በገሃድ ቀርቦ በምርጫው ከሚወስንባቸው ጉዳዮች አንዱ ሆኖ ማለፍ በቻለ ነበር። የወያኔ አምባገነናዊ ቁጣ ቅጥ ባጣ ቁጥር እየተሰበሰቡ "ምን እናድርግ? ወዴት እንሂድ?" በሚሉ ማለቂያ

በሌላቸው የአመራር ስበሰባዎች መጠመድን ያስቀር ነበር፡፡ ወያኔ አምባገነናዊ እርምጃዎች መውሰድ ቀርቶ፣ ለመተንፈስ እንኳን የማይችልባቸውን ሁኔታዎች ቅንጅት መፍጠር አይሳነውም ነበር፡፡ ይህ ሁኔታ ያልተፈጠረው ቀደም ብዬ እንደጠቀስኩት በቅንጅት መሰረታዊ ድክመት ሳይሆን ከድርጅቱ እድሜ አነስተኛ ነት በመከተል ነው፡፡

በቅድሚያ ወያኔ አምባገነን ነውን? ለሚለው ጥያቄ መልስ ከተሰጠ በኋላ ከእንዲህ አይነት አምባገነን ሃይል ጋር ሰላማዊና ህጋዊ ትግል ማድረግ ይቻላል ወይ? የሚለው ጥያቄ የሚነሳ ይሆናል፡፡ የእዚህ ጥያቄ ምላሽ አዎንታዊ ከሆነ የትግል ስልቶቹ ምንድን ናቸው? እንዴትስ ተግባራዊ ይሆናሉ? የሚለው ጥያቄ መልስ የሚሰጥበት ይሆናል፡፡ ከዚህም ተከትሎ በየደረጃው በተግባር መፈጸም የነበረባቸው ቅድመ ዝግጅቶች የምርጫው ስራ አካል ሆነው ከምርጫው ቀደም ብለው እንዲፈጸሙ የሚገፋፋ ሁኔታ ይፈጠራል፡፡

ቅንጅት በምርጫው ወቅት ሊከሰቱ ይችላሉ ብሎ ያሰባቸውን የምርጫው ሂደት አማራጮች በሶስት መንገድ ከፋፍሎ እንደሚያያቸው ለምርጫ ሲያደርግ ከነበረው ቅስቀሳ ተረድተናል፡፡ «ኢህአዴግ ምርጫውን ፍትሃዊ በሆነ መንገድ ያሸንፋል፤ ወይም ቅንጅቶች ምርጫውን ፍትሃዊ በሆነ መንገድ እናሸንፋለን፤ ወይም ወያኔ አጭበርብሮ በስልጣን ለመቆየት ይሞክራል፡፡» ነበር የተባለው፡፡ «በመጀመሪያ ሁለቱ መንገዶች ከተሄደ ማንም ያሸንፍ ማንም ችግር አይኖረውም፡፡ ነገር ግን በማጭበርበር ስልጣን ላይ የመቆየት እርምጃ ወያኔ ወስዶ ዝም ብለን እንደማናየው መታወቅ አለበት» የሚል ቅስቀሳ ለህዝብ የሚቀርብበት ወቅት ነበር፡፡ «ይህን ማጭበርበርን ለመቃወም የሚደረገው ትግል ሰላማዊና ህጋዊ የሆኑትን የትግል አማራጮች በሙሉ መጠቀም ይሆናል» የሚል አስተያየትም በቅንጅት በኩል በስፋት ሲሰነዘር ነበር፡፡ እነዚህ አባባሎች በተለያዩ መድረኮች በተለያዩ የቅንጅት የአመራር አካላት የተነገሩ እንደሆነ አስታውሳለሁ፡፡



ከምርጫውም በኋላ በተፈጠረው ሁኔታ ቅንጅት ይህንን የትግል ስልት እንደሚከተል ከህብረቱ ጋር በተከታታይ ያወጣቸውን መግለጫዎች በመመርመር መረዳት ይቻላል፡፡ችግሩ በአንድ በኩል እንዲህ አይነት የትግል ስልቶች ለመጠቀም የሚያስገድድ ሁኔታ በተፈጠረበትና መግለጫ እየተሰጠ በነበረበት ወቅት ጭምር ከወከባ የተረፈውን እያንዳንዱን ደቂቃ በዋንኛ ነት ይህንን የትግል ስልት በስራ ለመተርጎም በሚያስችሉ ቅድመ ዝግጅቶች ላይ አለማዋል የታየበት ሁኔታ ተከስቷል፡፡ ህዝቡ በሁኔታው ተማሮ ድምጹን በሰላማዊ መንገድ ለማስከበር የሚያደርገውን የተናጠል እርምጃ ጎጂነት ከመግለጽና ወደፊት በጋራ ለሚደረገው ትግል እየተዘጋጀ እንዲጠብቅ ጥሪ ከማቅረብ ውጭ፣ለተባለው አጠቃላይ ትግል መደረግ የሚገባቸውን በርካታ ስራዎች እየተጣደፉ መስራት አልታየም፡፡ ህዝቡ ይህንን አልሰማ ብሎ በተለያዩ ወቅቶች በወሰዳቸው ሰላማዊና ህጋዊ እርምጃች የደረሰበትን ስቃይ በሚመለከት በቅንጅት የተወሰደው አቋም ቅንጅት እራሱን ከዚህ እርምጃ ወሳጆች ማራቅ እንጂ፣ ለእንዲህ አይነቱ ሁኔታ መፈጠር ተጠያቂው ወያኔ እንደሆነና ይህ ሁኔታም በተጠናከረና በተደራጀ መልኩ በቅንጅት መሪነት ወደፊት እንደሚቀጥል ተደርጎ በአጥቂነት መንፈስ የተሰጠ ምላሽ አልነበረም፡፡ በዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ላይ ወያኔ የወሰደውን እርምጃ በመኮነን ሳይሆን ቅንጅትን ከተማሪዎቹ ተቃውሞ ጋር የሚያርቁ መግለጫዎችና ቃለ ምልልሶች ነበር የሚሰጡት፡፡ የሰኔ 1 ቀን 1997ቱን የወያኔ ግፈኛ ጭፍጨፋ ለማቅረብ የተሞከረው በዚሁ መንፈስ ነበር፡፡ «እኛ በምርጫ ቦርድና በፍርድ ቤት እንሄዳለን አልን እንጂ እንዲህ አይነት ሁኔታ ይፈጠር አላልንም» በማለት ነበር ምንም አይነት ተቀባይነት ሊኖረው ከማይገባው የወያኔ ክስ እራስን ለማሸሽ ይሞከር የነበረው፡፡ ይህንን በማለት ወያኔን የመሰለ አምባገነን ማለሳለስ የሚቻል የመሰላቸው ከነበሩ ታላቅ ስህተት እንደነበረ ሊረዱት ይገባል፡፡

ከላይ የተባሉትን ነገሮች ስንመረምር ነው ቀድሞ ያልተሰሩ የቤት ስራዎቻችን እያስከተሉ ያሉትን ጉዳቶች

በሚገባ መመርመር የምንችለው:: የወያኔ አምባገነንነት በቅድሚያ በቅንጅት ውስጥ በቂ ግምገማና አቋም ተይዞበት፣ እንዲሁም ይህንን አምባገነንነት በሰላማዊና ህጋዊ መንገድ እንዴት መታገል እንደሚቻል ቅድሚያ ስምምነት ተደርሶ ቢሆን ኖሮ፣ ቅንጅት በቀጣይነት ከወሰዳቸው እርምጃዎች እራሱን ማዳን በቻለ ነበር:: ወያኔ አምባገነን እስከሆነ ድረስ በእርሱ ፍርድ ቤትና የምርጫ አስፈጻሚ አካላት በኩል ተሂዶ የተጭበረበረን ድምጽ ማስመለስ እንደማይቻል፤ የውጭ መንግስታት የራሳቸውን ጥቅም እያሰሉ የወያኔን አይን ያወጣ ጸረ-ዴሞክራሲያዊነት ተቀብለው እንደሚቀጥሉ በቀላሉ የሚታይ ይሆን ነበር::

ይህ ግንዛቤ፣ ህዝብ በአምባገነኖች የተቀማውን መብቱን በራሱ የጋራ ጥረትና መስዋዕትነት ብቻ ካልሆነ፣ በሌላ በምንም አይነት አቋራጭና ከመስዋእትነት በጸዳ መንገድ፣ ማስከበር እንደማይቻል የሚጠቁም ይሆን ነበር:: ይህ እይታ ደግሞ ዋንኛውን የትግል ስልት ሰላማዊ አመጽን (እምቢተኛነትን) የሚደግፉ ሁኔታዎችን በማዘጋጀት ለሚደረግ ርብርቦሽ ጊዜንና ጉልበትን ማዋልን ያስገድድ ነበር::

. በግዜያዊነትም ቢሆን ከላይ እስከ ዝቅተኛ ደረጃ የተዘረጉ የቅንጅት ድርጅታዊ መዋቅሮች በፍጥነት መዘርጋት፤

. በሃገሪቱ ከሚገኙ የሲቪል፣ የሙያና ሌሎችም ማህበራት ጋር ጥብቅ የትብብር ግንኙት መፍጠር፤

. በሃገርና ከሃገር ውጭ የሚገኘውን የሰው ሃይል ትግሉ በዋንኛነት የሚያስፈልገውን የገንዘብና የቁሳቁስ ድጋፎች በማያቋርጥ መልኩ ማበርከት የሚችልበትን ድርጅታዊ ሁኔታ በአስቸኳይ መፍጠር፤

. ተመሳሳይ የአመራር ሃላፊነትና ስልጣን ያላቸውን ተተኪ የአመራር እርከኖች በመፍጠር፣ ወያኔ በአመራሩ ላይ ሊወስድ የሚችላቸው የማፈን እርምጃዎች ለማምከን መዘጋጀት፤



. ከሃገር ውጭም ቢሆን የተወሰኑ የድርጅቱ አመራሮች በተጠባባቂነት ተዘጋጅተው እንዲቀመጡ ማድረግ፤

. ህዝብ ከቅንጅት አመራር ጋር በቀጥታ መመካከር የሚችልባቸው መድረኮች ቢዘጉ ህዝብን በጽሁፍና ወያኔ ሊቆጣጠራቸው በማይችሉ የሬድዮ ስርጭቶች መልእክትን ለማስተላለፍ መዘጋጀት፤

. የሃገሪቱን ኢኮኖሚና የህዝቡን የትግል ልምድና አቅም ግምት ውስጥ ያስገቡ የተለያዩ የሰላማዊ አመጽ ስልቶች መንደፍ፣ በየግዜው የሚፈጸሙትን በቅደም ተከተል አንጥሮ ማስቀመጥ፣ ለሚቀያየሩ ሁኔታዎች የሚስማሙ የትግል እርምጃዎችን አስቀድሞ ማጥናት፤ የመሳሰሉትን በጥድፊያ ማሳካትን ግንዛቤ ያስጨብጥ ነበር::

እነዚህንና ሌሎችንም ቅድመ-ዝግጅቶች በተቻለ ፍጥነትና በተገኘው አጋጣሚ በተለይ የወያኔ አምባገነንነት አይን እያወጣ በሄደባቸው ከምርጫው ማግስት ጀምሮ በነበሩት ቀናት፤ በተግባር ለማዋል ጥረት አለመደረጉ አንድ መሰረታዊ ችግር እንዳለ ያሳየናል:: ቅንጅት ሰላማዊና ህጋዊ የሚለው ትግል፣ በስራ ማቆም አድማ፣ በሰላማዊ ሰልፍ፤ ከቤት ባለመውጣት፣ የወያኔ የማምረቻ ተቋማት የሚያመርቱትን ሸቀጦችና የንግድ ድርጅቶች የሚያቀርቡትን ግልጋሎቶች ባለመግዛት፤ የወያኔ ጋዜጦችን ሬድዮ ቴሌቪዥን አለማድመጥና አለማየት፣ ለወያኔ መንግስት ምንም አይነት የግብር ክፍያ አለመክፈል፣ በማንኛውም ጉዳይ ከወያኔ መንግስት ጋር አለመተባበር፣ የመከላከያና የፖሊስ ሰራዊቱ አባላት የዘለቄታ ጥቅማቸው ከአምባገነኑ ወያኔ ጋር ሳይሆን ከህዝብና ከዴሞክራሲ ስርአት ጋር እንደሆነ አውቀው የአምባገነኖች መሳሪያ እንዳይሆኑ መቀስቀስና ሌሎችንም በርካታ እምቢተኛነትንና አልገዛም ባይነትን የሚያረጋግጡ የህጋዊና የሰላማዊ የአመጽ እርምጃዎች በመፈጸም የሚገለጽ ለመሆኑ ግልጽና የጋራ ግንዛቤ ነበረው ለማለት አያስደፍርም:: የዚህ ግንዛቤ አለመኖር እነዚህን ተግባራት ለመፈጸም በቅድሚያ መደረግ

የሚገባቸውን በርካታ ዝግጅቶች እንዳይከናወኑ አድርጓል። ይህ ሁሉ ችግር ግን የመነጨው በቅድሚያ ከቅንጅት ዕድሜ አጭርነት ነው። ከጊዜ እጥረት የተነሳ የወያኔን አምባገነንነት በሚገባ ለመገምገምና ከእንዲህ አይነቱ አምባገነን ጋር በአንድ አጋጣሚ በተፈጠረ የዴሞክራሲ ጭላንጭል ውስጥ የሚደረገው ትግል ወዴት እንደሚያመራ አስቀድሞ በሚገባ ለማጤን ካለመቻል ነው።

## የህዝቡን ምሬትና ለመስዋዕትነት ያለውን ዝግጁነት በሚገባ አለመገንዘብ

እንደማንኛውም አምባገነንና ገገር፤ ወያኔ ሁኔታ-ዎችን እንዳሉ በነባራዊነታቸው ማየት የሚችል አይደለም። የአምባገነን ህሊና ሞት እያዘነበ ሕይወት፣ ረሃብ እያወረደ ጥጋብ ስቃይ እያከናነበ ፍስሃ፣ ፋንድያ ላይ እያስተኛ ወርቅ አንጥፌአለሁ የሚል በሽተኛ ህሊና ነው። ወያኔ በህዝብና በሃገር ላይ የፈጸመውን በደል፣ ክህደትና ግፍ በረሳ ህሊና ህዝብ ይመርጠኛል ብሎ ማሰብ እንደሚችል መጠራጠር የለብንም። ከዚህ በተጨማሪ ህዝብ ከደርግ ዘመን ጀምሮ የገባበትን የፍራቻ ቀለበት ሰብሮ፣ የወያኔን የአፈና መዋቅር ሳይፈራ በአደባባይ በመውጣት በድፍረት ይጋፋኛል ብሎ ማሰብ ስለማይችል ከወያኔ ውጭ ሌሎችን የፖለቲካ ድርጅቶች ይደግፋል የሚል ቅዠት አልነበረውም። ስለዚህ በምርጫው ልሸነፍ እችላለሁ የሚል ጥርጣሬ አልነበረውም።

በቅንጅት በኩልም በተለያዩ ወቅቶች ይሰነዘሩ የነበሩ ሃሳቦች፣ በልበ ሙሉነትና እርገጠኛነት «ህዝብ ድጋፍ ይሰጠናል፤ ወያኔን ማሸነፍ እንችላለን» የሚል ነበር ለማለት አልደፍርም። በቅንጅት ውስጥ እንዲህ ብለው የተናገሩ ድርጅቶች ቢኖሩም በተናጠል እንጂ አጠቃላዩን የቅንጅትን ወይም የተቃዋሚውን ካምፕ አመለካከት የሚወክሉ አልነበሩም። እንደማናቸውም በአምባገነን ስርአት ውስጥ እንደተፈጠሩ ድርጅቶች የተቃዋሚ መሪዎች የራሳቸውንና የህዝባቸውን አቅምና



ጉልበት በሚገባ መገመት አለመቻላቸው የሚገርም አይደለም። ስርአቱ ነጻ ባለመሆኑ እንዲህ አይነቱን ግምገማ በሚገባ ማድረግ አይቻልም። አመራሩ ረዘም ላለ ጊዜ ከህዝቡ ጋር በስፋት እየተነጋገረ ሁኔታዎችን በነጻነት የሚገመግምበት እድል አያገኝም።

ከሁሉም በላይ አንዱ በአምባገነን ስርአት ውስጥ የሚኖሩ ህዝቦች መለያ፣ ስርአቱ በሚፈጥረው የማፈን ጫና የተነሳ የተቃዋሚ መሪዎችም ሆኑ ህዝቡ አቅሙን አሳንሶ እንዲያይ፣ በራሱ እንዳይተማመን የሚያደርግ በመሆኑ ቅንጅት የማሸነፍ እድሉን በሚገባ አለማስላቱ አይገርመኝም።

የምርጫው ሂደት እየገፋ ህዝብ ከፍራቻው እየተላቀቀ በሄደበት ወቅት ከመቼውም ይበልጥ ቅንጅት ሊያሸንፍ የሚችልበት እድል እንዳለ በይፋ መሪዎቹ መናገር ጀምረው እንደነበር ግልጽ ነው። ይህ አነጋገር ከተስፋ በላይ ተሻግሮ በእውነታ ሊተረጎም ይችላል ተብሎ የታመነበት ነበር ለማለት ግን ይከብደኛል። ለዚህ ማስረጃ የሚሆነው በተለያዩ ቦታዎች ቅንጅት በሚጠራቸው ስብሰባዎች ላይ የሚገኘው የህዝብ ብዛትና ህዝቡ የሚያሳየው ድፍረት ያለማቋረጥ አመራሩን ያስገርሙት እንደነበር ስለማስታውስ ነው።

ቅንጅት ለሚያዝያ 30 በመስቀል አደባባይ ጠርቶት የነበረውን ሰልፍ አንድ ቀን ቀደም ብሎ ሚያዝያ 29 ቀን ወያኔ በማስገደድና በመደለል ካዘጋጀው ሰልፍ የላቀ ሊሆን የሚችል መሆኑን የተጠራጠሩ ብዙ-ዎች ነበሩ። እንዲህ አይነቱ አመለካከት በምርጫውም ውጤት ላይ ግልጽ የሆነ አቋም መያዝ እንዳይቻል ስለሚያደርግ ቅንጅት ሲያሸንፍ አምባገነኑ ወያኔ ሊሰራቸው የሚችላቸውን ጸረ-ዴሚክራሲያዊ ችግሮች እንዴት መቋቋም ይቻላል የሚል ጥያቄ በአጽንኦት እንዲጠየቅ አያበረታታም። ይህ በመሆኑ ቅንጅት ምርጫውን ቢያሸንፍ ከወያኔ የሚደርስበትን ጥቃት ለመከላከል በቅድሚያ ማድረግ የሚገባውን ቅድመ-ዝግጅት እንዳያደርግ አድርጎታል የሚል እምነት አለኝ። በዚህ የተነሳም ቅንጅት ቀደም ብለን በጠቀስናቸው

የሰላማዊ አመጽ የትግል ስልቶች የወያኔን አምባገነንነት ለመጋፈጥ ሳይዘጋጅ፣ በየደረጃው የተፈጠረውን ቀውስ እየተከታተለ በተከላካይነት እንዲቀጥል ሆኗል።

ከዚህ በላይ የጠቀስኳቸው፣ ከምርጫው በፊት በሚገባ መደረግ የሚገባቸው ግምገማዎች መደረግ ባለመቻላቸው መዘዛቸው አሁንም አላለቀም። አሁንስ ቅንጅት የወያኔን አምባገነንነት በሚገባ ተረድቷል ወይ? ከተረዳስ ይህንን ግምት ውስጥ ያስገባ የትግል ስልት እየነደፈ ነውን? ቅንጅት አሁንስ ቢሆን የወያኔን አምባገነናዊነት ለመታገል የህዝብን ድምጽ ለማስከበር ለሚያደርገው ጥረት ከህዝብ ሊያገኝ የሚችለውን ድጋፍና ህዝብ ለመስዋዕትነት ያለውን ዝግጁነት በሚገባ መገምገም ችሏል ወይ?

## ፓርላማ መግባት እና አለመግባት፣

## የአምባገነኖችን እጅ የሚያጠናክር አጀንዳ

ፓርላማ እንግባ ወይንስ አንግባ የሚለው ክርክር አሁንም የወያኔን ምንነት በሚገባ ካለመረዳትና ይህንን አምባገነንነት ለመቋቋም ዝግጁነት ባለመኖሩ የሚነሳ ጥያቄ ይመስለኛል። ቅንጅት በቅድሚያ አሁንም መመለስ ያለበት ጥያቄ ወያኔ አምባገነን ነው?ወይንስ አይደለም? የሚለውን ነው። በእኔ እምነት ወያኔ አምባገነን ለመሆኑ መረጃ መደርደር አያስፈልገኝም። አምባገነን ብቻ ሳይሆን እንደጨለማው ዘመን መሳፍንት ምድረ-ኢትዮጵያ በጉልበት ያስገበርኩት ጉልቴ ነው ብሎ የሚያምን ነው።

በ21ኛው ክፍለ ዘመን መኖሩን እረስቶ የመንግስት ስልጣንን ከዚህ ቀደም በተለያዩ የጎሳ መሪዎች መካከል እንደሚደረግ ፉክቻ አድርጎ የሚያይ ኋላ-ቀር ሃይል ነው። «ያለፉት ነገስታት ቀጥቅጠው ሲገዙን ነበር፤ አሁን ተራው የእኛ ስለሆነ ቀጥቅጠን እንገዛችኋለን» የሚል ድርጅት ነው። ወያኔ አምባገነን መሆኑን ከተማመንን ከእንዲህ አይነቱ አምባ ገነን ጋር



የሚደረግ ማናቸውም መደራደር ከዚህ በፊት እንዳልነው ለአምባገነኑ ወያኔ እብሪት፣ በህዝብና በተቃዋሚው ሃይል ላይ ያለውን ንቀት ማጠናከሪያ ነው የሚሆነው። በሃገራችን በተፈጠረው ሁኔታ የፖለቲካ አጣብቂኝ ውስጥ የወደቀው ወያኔ ሆኖ ሳለ የድርድር ሃሳብ ማቅረብ፤ መውጫ ቀዳዳውን ማሰላሰል የነበረበት ወያኔ መሆን ሲገባው፣ የጥምር መንግስት እንዲቋቋም ጥሪ የማድረጉን እርምጃ ተቃዋሚው መውሰዱ በትግል ታክቲክ ደረጃ የሚያጠያይቅ ይመስለኛል። መለስ ዜናዊ የተቃዋሚ ተወካዮችን ሰብስቦ የውጭ ታዛቢ ባለበት ስፍራ «ወይ ፓርላማ ትገቢያለሽ ወይም አንገትሽ ደፍተሽ ትኖሪያለሽ» ብሎ ሲደነፋ የተቃዋሚ መሪዎች፣የውጭ ታዛቢው በሚገባው ቋንቋ # who the hell do you think you are?» ለመሆኑ አንተ ምንድን ሆነህ ነው? እንዲህ የምትናገረን በማለት ስብሰባውን እረግጠው ሊወጡ ያልቻሉበት ሁኔታና እንዲያውም ከዚህ ንግግር በኋላ የብሄራዊ እርቅ መንግስት ሃሳብ ለማቅረብ የተገደዱበት ሁኔታ መከሰት የቻለው ይህንን አምባገነን ግለሰብ በህዝባዊና በሰላማዊ አመጽ ማንበርከክ ይገባል፤ ይቻላልም የሚል እምነት ስላልነበራቸው ይመስለኛል። ፍላጎቱ ቢኖራቸውም እንዲህ አይነቱን ትግል ለመጀመርና ለማስፈጸም የሚችል ህዝባዊ ድጋፍ፣ ድርጅታዊ ብቃትና የአመራር ዝግጁነት መኖሩን ከመጠራጠር የተፈጸመ ይመስለኛል። ነገር ግን በሁኔታዎች አስገዳጅነት፣ ለሰላም፣ ለዴሞክራሲ፣ ለሰው ልጆች ህይወት ክቡርነት፣ ለሃገሪቱ ህዝቦች በሙሉና ለሃገሪቱ ደህንነት ሲባል በቀናነት ቅንጅቱ ከህብረቱ ጋር በመሆን ያቀረበው ጊዜያዊ የጥምር መንግስት ሃሳብ፤ ከማንም በላይ ለራሱ ለወያኔ የሚጠቅም ነበር። ይህም ሆኖ ወያኔ ብልግናና እብሪት በተሞላበት መንፈስ የቀረበለትን ከጭንቅ መውጫ መንገድ አሽቀንጥሮ ከጣለ በኋላ ቅንጅት በፍጥነት ሊማር የሚገባው ጉዳይ በምንም አይነት መንገድ ከወያኔ ጋር መደራደር እንደማይቻል፤የህዝብን ድምጽ ለማስከበር ከሰላማዊ አመጽ በስተቀር ሌላ አማራጭ እንደሌለ መገንዘብ ነበር። ይህንንም ተረድቶ በፍጥነት ይህንን የትግል አቅጣጫ በስራ ላይ ለማዋል እስከዚያ ወቅት ድረስ ያላሟላቸውን ዝግጅቶች በፍጥነት ለማሟላት ጥድፊያ

ማድረግ ነበር። ነገር ግን ይህ መሆኑ ቀርቶ ለሃገሪቱ አምባገነኖች የበለጠ የልብ ልብ የሚሰጥ ሌላ አዲስ አሳሳቢ ሃሳብ ማስተናገድ ተጀመረ። «ፓርላማ ገብተን እንታገል ወይም ፓርላማ አንግባ» የሚለውን የውይይት አጀንዳ ነው አሳሳቢ ያልኩት።

ይህንን አጀንዳ አሳሳቢ ያልኩት ያለምክንያት አይደለም። ወያኔ ለራሱ የሚጠቅም የጥምር መንግስት ሃሳብ ቀርቦለት እምቢ ባለበት ማግስት ተቃዋሚዎች «ፓርላማ እንግባ ወይም አንግባ» በሚለው ጉዳይ ላይ ውይይት እንደሚያደርጉ ሲሰማ የህዝብን መብት ረግጦ በስልጣን የሚቀጥልበት ዕድሉ ሰፊ መሆኑን የምስራች እየተነገረው እንደሆነ አድርጎ ማየቱ ነው።

«ወያኔ! ወደ አስቀመጥንልህ የጥምር መንግሰት እማትገባ ከሆነ በሰላማዊ የህዝብ አመጽ የህዝቡን ድምጽ እናስከብራለን» የሚል ቀጥተኛ መልእክት ሊተላለፍለት ይገባ ነበር።

ይህንን ከማድረግ ይልቅ «የጥምር መንግስቱ የማይዋጥልህ ከሆነ ግድ የለም አናስቸግርህም አንተው እንዳልከው በአንተ ትእዛዝና መስፈርት፤ የህዝብን ድምጽ በግድያና በግፍ ዘርፈህ ባቋቋምከው ፓርላማ ውስጥ ልንገባ እንችላለን» የሚል ትርጉም ያለው መልእክት የሚያስተላልፍ ሌላ አጀንዳ ማንሳት ባላስፈለገ ነበር። ይህ አጀንዳ በስራ ባይተረጎም እንኳን ጊዜያዊ በሆነ መልኩ ወያኔን በማበረታታት ህዝብ ለትግሉ የሚከፍለውን መስዋዕትነት ከሚገባው በላይ የሚያገዝፈው ይሆናል። ወያኔ ከተለመደው አምባገነንነቱ በመነሳት? ተቃዋሚችን ብንሰድባቸው፣ ብንደበድባቸው፣ ብናስራቸውና ብንገላቸው ምንም ሳያቅማሙ ፓርላማ ገብተው ሰጥ ለጥ ብለው ይገዛሉ የሚለውን እምነቱን የበለጠ እንዲያጠናክር የሚያደርገው ነው። ይህንን ደግሞ ከመቼውም በላይ በተግባር እያሳየን ይገኛል። ምክንያቱም የአምባገነኖች ባህርይ ከዚህ ውጭ ማሰብ እንዲችሉ አይፈቅድላቸውምና ነው።



ከዚህ ውጭም ህዝብ ተጭበርብሮ፣ ተገድሎና ታስሮ አሁንም በየከተማውና በየገጠሩ ስቃዩን እያየ፣ በሚገባ ያሸነፋቸው ሹማምንት እንደገና ተወዳድረን አሸነፍን በማለት፣ህዝብ ድምጹን ለቅንጅትና ለህብረቱ መስጠቱ በራሱ በመንግስት አካላት ፊርማ የተረጋገጠላቸውን መቀመጫ ቀምተው፣ በፓርላማው ውስጥ ደግሞ ተቃዋሚው እርባና ያለው ስራ መስራት የሚችልበት ዕድል በአዋጅ በተዘጉበት ሁኔታ ፓርላማ መግባት የሚለው ሃሳብ እንዴት ሊነሳ እንደሚችል ለብዙዎቻችን ሊገባን አልቻለም። በየጊዜው ቅንጅት የሚያማክረው፣ ከማንም በላይ በወያኔ ግፈኛ አገዛዝ ሁለንተናዊ ህይወቱ በአሳር የተሞላው አብዛኛው ህዝብ ፓርላማ መግባት የሚባል ነገር አታሰሙኝ የሚለው ሰላምን፣ እርቅን፣ መረጋጋትን ጠልቶ ሳይሆን የአምባገነኖችን ምንነትና ባህርይ ከተሞክሮው በሚገባ የተረዳ በመሆኑ ነው። ከዚህ በኋላ ወያኔን ለመሰለ እብሪተኛና አምባገነን ተጨማሪ የአገዛዝ ዘመን መጨመር ምን ማለት እንደሚሆን ስለሚያውቀው ነው።

«የትናንቷ የዴሞክራሲ ጭላንጭል የምትደፈንበትን፣ በየገጠሩ ቅንጅትን የደገፉ በሙሉ ኑሮአቸው የበለጠ ገሃነም የሚሆንበትን፣ በህዝብ የተጠላ መንግስትና መሪዎች እስካሁን ሲያካሂዱት ከነበረው በላይ የሃገርና የህዝብ ሃብት ምዝበራ የሚያካሂዱበትን፣ «እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል» በሚል መመሪያ ከአስካሁኑ የከፋ ሀገራዊ ክህደት የመፈጸም፣ ህዝብን የበለጠ በዘርና በእምነት በመከፋፈል ለጋራ ጥቅሙ በጋራ እንዳይነሳ እርስ በእርሱ እንዲተላለቅ ለማድረግ ሴራ መሸረብ እንዲችሉ ለወያኔ አምባገነኖች ተጨማሪ ዕድል መስጠት ነው፤» ብሎ ህዝብ ስለሚያምን ነው።

ከምርጫው በኋላ በወያኔ እየተወሰዱ ያሉ እርምጃች በሙሉ ይህንን የህዝብ ፍራቻ የሚያረጋግጡ እንጂ ወያኔ ሌላ ዕድል ቢያገኝ ከጥፋቱ ተምሮ ለሀገር ጥቅም በመቆም ለዴሞክራሲ ማበብ፣ ለፍትህና ለነጻነት መኖር ለመስራት መፈለጉን የሚያሳዩ አይደሉም።

ከሁሉ ነገር በላይ መታወቅ የሚገባው ወያኔን የመሰለ በድንቁርናና በታመመ ህሊና የሚንቀሳቀሱ አምባገነኖች የሞሉት ድርጅት በእንዲህ አይነት መንገድ ለማሰብና ለመንቀሳቀስ አእምሮአዊ ብቃትና ጤንነት እንደማይኖረው ነው:: ከምርጫው በኋላ የሚሰማውን ድንፋታ፣ ከፋፋይ የሆነ ዘረኛ ፕሮፖጋንዳ፣ በታክስ ቅነሳና በደሞዝ ጭማሪ ስም ከኢኮኖሚ እድገት ጋር ያልተገናኘ ድለላ፣ በከተሞች ቤቶችና መሬት ላይ እየተካሄደ ያለው ዘረፋ፣ ከሁሉም በላይ ደግሞ በገጠርና በከተማ የህዝቦችን ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች በመርገጥ በወያኔ እየተወሰዱ ያሉ እርምጃች ወያኔ ከምርጫው በኅ ነገሮችን በመቅሰም አስከዛሬ ድረስ ሲፈጽም ከነበረው የተለየ ነገር እያከናወነ እንደሆነ አይጠቁሙም:: በእንዲህ አይነቱ ሁኔታ ፓርላማ እንግባ ማለት ይህንን ግፍ ለሚፈጽም መንግስት ህጋዊ እውቅና ከመስጠት የተለየ ትርጉም አይኖረውም::

## ፓርላማ መግባት ለምን አስፈለገ?

ፓርላማ መግባት የወያኔን አምባገነናዊ መንግስት ህጋዊነት ከማረጋገጥ በስተቀር ሌላ ምንም ፋይዳ እንደማይኖረው ግልጽ ነው:: ፓርላማ በመግባት ሰላም እንዲሰፍን፣ ዴሞክራሲ ስር እንዲሰድ፣ መከፋፈል እንዲወገድና ሙስና እንዲጠፋ ለማድረግ እንደማይቻል ግልጽ ነው:: በመሆኑም ፓርላማ ለመግባት የሚቀርበውን ሃሳብ ከፍተኛ ትርጉም ባላቸው ሃገራዊና ህዝባዊ ጠቀሜታዎች ስም ማረጋገጥ አይቻልም:: ፓርላማ መግባትን የሚገፋፋ አንድም አሳማኝ ምክንያት ማቅረብ በማይቻልበት ወቅት «እንግባ» የሚለው ሃሳብ እንዴት እንደአማራጭ መስተናገድ እንደቻለ በዝርዝር የገለጸልን የለም:: እኔ በበኩሌ የወያኔን የበላይነትና ያለውን ሁኔታ ተቀብሎ ፓርላማ መግባት ስህተት ብቻ ሳይሆን፣ የረቀቁና የደቀቁ ድሎች መጎናጸፊያ መሳሪያ ነው የሚል እምነት በቅንጅት ውስጥ አለ የሚል እምነት አለኝ:: ስለፓርላማ መግባትና አለመግባት ስናወራ ተቃዋሚዎች አሸናፊነታቸው ታውቆ ስለሚገቡበት በፓርላማ ወይም የተቃዋሚ ፓርቲዎች ያቀረቡትን የጥምር መንግስት



ስራዎች ለማሳካት በሚፈጠር ፓርላማ ዙሪያ እንዳልሆነ መታወቅ አለበት:: በእነዚህ ሁኔታዎች ፓርላማ መገባት የለበትም የሚል ክርክር ካለ ስህተተኛ ይመስለኛል::

ከዚህም በተጨማሪ ፓርላማ ውስጥ መግባትን የሰላማዊ አመጽ ወይም የእምቢተኛነት ትግሉ ተቀጥላ አድርጎ ለመንቀሳቀስ ታስቦ ከሆነ ፓርላማ እንግባ የሚለው ሃሳብ በጥሞና መታየት ይኖርበታል:: እንዲህ አይነቱ አማራጭ ግን፣ በቅድሚያ ቅንጅት በወያኔ አምባገነናዊነት ላይ ግልጽ አቋም በመያዝና ከእንዲህ አይነቱ አምባገነን ጋር ለሚደረግ ትግል ዋንኛ መሳሪያው ፓርላማ ሳይሆን፣ ሰላማዊ አመጽ ብቻ እንደሆነ በማያሻማ ቋንቋ በማስቀመጥ የሚጀመር ነው:: በፓርላማው ውስጥ ምንም አይነት ትግል ማድረግ እንደማይቻል የተረዳ፣ ማንኛውም ትግል ከፓርላማ ውጭ በሚደረጉ ህዝባዊ ሰላማዊ አመጾች አማካይነት እንደሚካሄዱ ከልብ ያመነ መሆን ይኖርበታል::

ይህም ሁሉ ተብሎ፣ ከሁሉ በላይ ፓርላማ እንግባ የሚለው ሃሳብ ማለፍ ያለበት ፈተና አለ:: ይህንን የምለው ያለምክንያት አይደለም:: ቅንጅት ፓርላማ በመግባቱና ባለመግባቱ በሰላማዊና በህጋዊ መንገድ የህዝብን መብት ለማስከበር የሚያደርገውን በህዝብ እምቢተኛነት ላይ የተመሰረተ ህገ-መንግስታዊ ትግል በመጥቀምና በመጉዳት የሚኖረው ጫና ይኖራል ወይ?ፓርላማ ስለተገባ ይህንን የህዝብ እምቢተኛነት ትግል ለመጠቀም የተሻለ ዕድል መፍጠር ይቻላል ወይ? በአጭሩ፣ ከፓርላማ ውጭ ወያኔ የማያከብረውን ህገመንግስታዊ መብቶች ፓርላማ ስለተገባ ብቻ የሚያከብር ይሆናል ወይ? ፓርላማ ተገብቶም ዋንኛ የትግል ስልት ሰላማዊ የህዝብ አመጽ እስከሆነ ድረስ ወያኔ የፓርላማ አባላቱን ከፓርላማ አውጥቶ የማይወረውርበት፣ የማያስርበት፣ የማያዋክብበትና የማያንገላታበት ምን ምክንያት ይኖራል? ችግሩ በዋንኛ ነት የተሳሰረው ከምን ጋር ነው? ፓርላማ ከመግባትና ካለመግባት ጋር ነው ወይስ ከወያኔ አምባገነናዊ ባህርይ ጋር ነው? በእኔ ዕምነት ችግሩ ከወያኔ አምባገነንነት ባህርይ ጋር የተሳሰረ ነው:: ፓርላማ በመግባት ሊከበር

የሚችል፣ ባለመግባት የማይከበር የህዝብ ሰላማዊ አመጽ ህገመንግስታዊ መብት አይኖርም:: ፓርላማ መግባት ይህንን ሁኔታ የማይቀይረው እስከሆነ ድረስ ትኩረት ልንሰጠው ከሚገባን የትግል አቅጣጫና ዝግጅት የሚያዘናጋን ነው የሚሆነው:: ፓርላማ መግባት በሃገራችን እየተዳፈነ ያለውን የዴሞክራሲ ጭላንጭል እንዳይጠፋ የሚያደርግ አስተዋጽኦ ይኖረዋል የሚል ቀጥተኛ የክርክር ነጥብ ማቅረብ እስካልተቻለ ድረስ በዚህ ላይ የሚደረግ ውይይት ፋይዳ አይኖረውም:: ይህ ደግሞ የወያኔን መሰረታዊ የአምባገነንነት ባህርይ ሳያለዝቡ በቀቢጸ-ተስፋ ሳይማልሉ ማቅረብ የሚችሉት ክርክር አይመስለኝም:: የወያኔን አምባገነናዊ ባህርይ ማለዘብ ደግሞ አዘናጊ፣ ታላቅና መሰረታዊ የፖለቲካ ስህተት ነው::

ፓርላማ እንግባ የሚል ሃሳብ በቅንጅቱ ውስጥ ካለ ከላይ ላነሳናቸው አስተያየቶችና ሌሎችም ከህዝብ ለሚነሱ ጥያቄዎች በቂ ምላሽ መስጠት የሚቻልባቸው የውውይት መድረኮች ተከፍተው፣ ጉዳዩ በስነስርአት ለኢትዮጵያ ህዝብ ቀርቦለት፣ ህዝብ አምኖበት እንጂ መሪዎች ለብቻቸው ህዝብን ተክተው «እኛ ከህዝብ የተሻለ የፖለቲካ ጥበብ አለን» በሚል የተሳሳተ አመለካከት የሚወስኑት መሆን የለበትም:: ከሞላ ጎደል ሁሉም ኢትዮጵያዊ በወያኔ ፓርላማ ውስጥ መግባት አያስፈልግም በሚልበት በአሁኑ ወቅት፣ ከህዝብ ተገቢውን ይሁንታ ሳያገኙ ፓርላማ መግባት ከፍተኛ የፖለቲካ ኪሳራ እንደሚያስከትል በደንብ መታወቅ አለበት::

በዚህ ጉዳይ ላይ በሃገር ቤት የሚገኘውን ህዝብ ብቻ ሳይሆን፣ ቅንጅትን በጉልበቱ፣ በዕውቀቱና በገንዘቡ ለመደገፍ ቆርጦ የተነሳውን በመቶ ሺዎች የሚቆጠር በውጭ ሃገሮች የሚኖረውን ኢትዮጵያዊ ጭምር ማማከር ይጠይቃል:: ማንኛውም ውሳኔ በሃገር ቤቱ አመራርና በሃገር ቤቱ የህዝብ ፍላጎት ላይ የሚወሰን ቢሆንም፣ በውጭ የሚኖረውን ኢትዮጵያዊ በሚገባ ማማከርና አስተያየቱን መስማት ተገቢ ነው:: አስተያየቱ ስለማይጥመን ብቻ አሁን በቅርቡ



እንደሰማነው በውጭ ሃገር የሚኖረው ኢትዮጵያዊ ምን አገባው የሚል ዝንባሌ የወደፊቱን አደገኛ አባዜዎች የሚጠቁም ይመስለኛል:: ይህ ህዝብ ከሃገር ቤት እርቆ በመገኘቱ ብቻ ለትግሉ ሊከፍል የሚችለውን መሰዋዕትነት አሳንሶ በማየት አስተያየቱን በሚገባ አለማዳመጥ መሰረታዊ ስህተት ይሆናል:: ለአጭር ግዜ ድርጅታዊ ጠቀሜታ ብቻ ሳይሆን ለሃገራችን ትንሳኤ ሲባል በተቻለ መጠን የሃገር ቤቱንና በውጭ ሃገር ሆኖ ሃገሩንና ህዝቡን ለመርዳት ከፍተኛ ተነሳሽነት እያሳየ ያለውን ህዝብ በጋራ ተሳስረው እንዲንቀሳቀሱ ማድረግ ከፍተኛ ትርጉም እንዳለው ሁላችንም መረዳት ይኖርብናል::

ከአጠቃላይ ምክክሩ ጎን ለጎን ሰላማዊ አመጽ ለመምራት የሚያስችሉ እስካሁን ያልተሟሉ ድርጅታዊ ዝግጅቶች በፍጥነት ለማሟላት የሚደረገው እንቅስቃሴ ተጠናክሮ መቀጠል አለበት:: ዞሮ ዞሮ ፓርላማ ተገባም አልተገባም ትግሉ በመሰረቱ ህዝባዊ እምቢተኛነት ላይ የተመሰረተ እስከሆነ ድረስ ይህንን አይነቱን ትግል ለመምራት የአመለካከት ግልጽነት፣ የአመራርና ድርጅታዊ ዝግጁነት ሊኖር ያስፈልጋል:: በዚህ የትግል ስልት አማካይነት በተለያዩ ደረጃዎች ስለሚከናወኑት ተግባራት አይነትና ምንነት በማያወላዳ ቋንቋ ተዘርዝሮ መቀመጥ አለበት:: በዚህ አይነቱ የጠራ አመለካከትና ድርጅታዊ ዝግጁነት ላይ የሚነሳ የፓርላማ መግባት ጥያቄ እንደ አንድ አማራጭ ለውይይት አይቅረብ የሚል ያለ አይመስለኝም:: እስከአሁን ግን እንደሰማነው ከወቅቱ አጣዳፊ ስራችን ወጥተን ይህን አማራጭ ደግፈን የምንቆምበት ምክንያት አላገኘንም:: ይህንን ካልኩ ፓርላማ መግባት የሚለውን ሃሳብ አጀንዳ ሊያደርጉት ስለቻሉት ነጥቦች ያለኝን አስተያየት አቀርባለሁ::

ፓርላማ ስለመግባት ትልቁ ግፊት የመጣው ለሰላማዊ አመጽ የሚሆን ድርጅታዊና የአመራር ዝግጁነት በሃገራችን ስለሌለ ይመስለኛል:: እዚህ ላይ መታወቅ ያለበት ነገር፣ጉዳዩ የግለሰቦችን ፍራቻ ወይም ድፍረት በሚመለከት የሚደረግ ክርክር አለመሆኑን

ነው። ቅንጅት እራሳቸውን በመሰዋትም ቢሆን የህዝብን መብት ጥቅምና ሰላም ለማስከበር ድፍረቱ ያላቸው መሪዎች ያሉት ድርጅት ነው። የሰላማዊ አመጽ ትግል በግለሰቦች ድፍረትና ጀግንነት ላይ ብቻ የሚወሰን ቢሆን ቅንጅት ችግር አይገጥመውም ነበር። ይህ ትግል ግለሰባዊ አመራርን ሳይሆን ድርጅታዊ አመራርን፤ግለሰባዊ ጥንካሬን ሳይሆን ድርጅታዊ ጥንካሬን የሚመለከት ነው። በአንድ በኩል የወያኔን አምባገነናዊ ሃይልና ጉልበት አጋኖ ከማየት፣በሌላ በኩል ይህንን ሃይል መቋቋም የሚችል ህዝባዊ የመስዋዕትነት ጽናት፤ ድርጅታዊና የአመራር ብቃት መኖሩን ከመጠራጠር የመጣ ችግር ነው። እንዲህ አይነቱ ሁኔታ በሚገባ መገምገም ባልተቻለበት ሁኔታ በእርግጠኛነት ውሳኔ ላይ ለመድረስ አስቸጋሪ ነው። ይህም ማመንታትን፣ መጋፈጥን በማስወገድ ውሎ አድሮ በሚፈጠር ሁኔታ ተጠናክሮ መውጣትን ወይም በህዝብ ላይ የሚመጣን መአትና መከራን ማስወገድ ይቻላል የሚል ቀቢጸ-ተስፋን ማስተናገድን ያስከትላል።

የቅንጅት መሪዎች የህዝብ ድምጽ መከበር አለበት የሚል የጸና እምነት እንዳላቸው ግልጽ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ይህንን የህዝብ ድምጽ ለማስከበር ሲባል ከወያኔ ጋር የሚደረግ ፍጥጫ በህዝብና በሃገር ላይ ሊያስከትል የሚችለው አደጋ ያስፈራቸዋል።

ይህንን አደጋ ለማሳነስና በአሸናፊነት ለመወጣት ባላቸው አጠቃላይ አቅም ላይም የሚተማመኑ አይደለም። በሌላ በኩልም ችግርና አደጋ ለማስወገድ ሲባል ፓርላማ ቢገባ ግፍና በደል ተቀብሎ፣ ለህዝብ የተገባን ቃል አጥፎ ስለሚሆን በደልን ተቀብሎ ለመኖር የማይፈልግ የራሳቸውና የሚደግፏቸው ህዝብ ህሊና ይቆጠቁጣቸዋል። ፓርላማ ቢገባም እራሳቸውንም ሆነ ህዝቡን ቢሆን ከወያኔ ጥቃትና ማፌዣነት ማዳን ስለመቻላቸው እርግጠኛ አይደሉም። ከሁሉም በላይ ግን መብቱን በሰላማዊና ህጋዊ መንገድ ለማስከበር የተነሳው ህዝብ መብቱ በዚህ መንገድ እንደማይከበር ሲያውቅ፣ መብቱን በሌላ መንገድ ለማስከበር የሚንቀሳቀስበት ዕድል የበለጠ እየሰፋ እንደሚሄድ፣ እንዲህ አይነቱ



እንቅስቃሴ ከቁጥጥር ውጭ በመውጣት በህዝብና በሃገር ላይ ሊያስከትል የሚችለው አደጋ ያሳስባቸዋል። ሌላው አደገኛ ውጤት ህዝብ መብቴን ያስከብሩልኛል ብሎ የመረጣቸው ተወካዮቹ መብቱን ሊያስከብሩለት በማይችሉበት ፓርላማ ውስጥ መግባታቸውን ሲመለከት በስፋት ሊከዳቸው፣ ብቻቸውን ከህዝብ ተገንጥለው የወያኔ መቀለጃ ሆነው እንዲቀሩ ሊያደርጋቸው የሚችልበት አደጋ እንዳለም ይታያቸዋል። ከህዝብ ጋር መራራቅ ደግሞ እንደ ወያኔ ባለስልጣናት በዋርድያ እየታጀቡ ከህዝብ ተደብቀውና ተሸማቆ መኖርን የሚያስከትል አሳዛኝ እጣን ለማምጣት እንደሚችል ሳይረዱት የቀሩ አይመስለኝም። የቅንጅት መሪዎች የገቡበት የፖለቲካ አጣብቂኝ ቀላል አይደለም። በፖለቲካ ታሪክ ውስጥ በጣም ጥቂት የፖለቲካ ድርጅቶች ናቸው እንዲህ አይነቱ ፈተና ውስጥ የወደቁ።

ያም ሆነ ይህ፣ አመራር ማለት አስቸጋሪና ፈታኝ ሁኔታም ውስጥ ቢሆን የተሻለ ነው በሚለው አማራጭ ላይ ውሳኔ ሰጥቶ መምራትና የውሳኔውን መዘዝ ተቀብሎ መኖርን ወይም መጥፋትን የሚያጠቃልል ነው። አመራር ተሁኖ ከመወሰንና ከመምራት ማምለጥ አይቻልም። ይህ የማይቀር መሆኑን በማመን ነው፤ ቅንጅት ለራሱም እንደ ድርጅት ሆነ እንዲሁም ለኢትዮጵያም ህዝብ ሲል የሚወስዳቸው እርምጃዎች በሚገባ ተተንትነው በቂ ግንዛቤ በአመራሩም ሆነ በህዝቡ ተይዞባቸው መወሰን የሚኖርባቸው። የዚህን የውሳኔ ሂደት ለማገዝ ሁላችንም የቅንጅትንና የኢትዮጵያን ህዝብ በጎ የምንመኝ ሁሉ ለውሳኔ ይረዳሉ ብለን ያሰብናቸውን ሃሳቦች ያለማመንታት በድፍረት ማቅረብ የሚኖርብን። ቅንጅትም እነዚህ አስተያየቶች ከየትም ከማንም ይምጡ የድርጅቱን ጥንካሬና አንድነት ከህዝብ ጋር ያለውን ግንኙነት ለማጎልበት በቀና መንፈስ እስከተሰነዘሩ ድረስ ማዳመጥ ይኖርበታል። የዚህ ጽሁፍ አላማም በዚህ ላይ የቆመ ነው። እኔም በዚሁ መንፈስ ተነሳስቼ ነው ቅንጅት አሁን ባለው ሁኔታ ፓርላማ መግባት የለበትም የሚለውን የአብዛኛውን ህዝብ አመለካከት ትክክለኛነት

ለማስረዳት ጥረት የማደርገው::ፓርላማ መግባት የሚለው አማራጭ እየተነሳ ያለው የፖለቲካ ሁኔታው አሁን ባለበት እንዳለ ከሆነ፣ ከላይ በዘረዘርኳቸው ምክንያቶች የተነሳ ትክክለኛና ተገቢ አማራጭ ይሆናል የሚል እምነት የለኝም:: መሰረታዊ የሆነ ታሪካዊና ፖለቲካዊ ስህተት ይሆናል የሚል ስጋት አለኝ:: የዚህ ስጋት ዋንኛው ምንጭ የወያኔን አምባገነንነት በሚገባ ካለመረዳትና በእንዲህ አይነቱ አምባገነናዊ ስርአት ውስጥ ፈጽሞ ሊፈጠር የማይችልን ዴሚክራሲያዊ መፈናፈኛ እንደሚፈጠር አድርጎ ከሚመኝ የተጋነነ ተስፈኛነት የሚነሳ የተሳሳተ የፖለቲካ አመለካከት ነው፤ የሚል እምነት አለኝ::

## ሌላው አማራጭ ምንድነው?

## ፓርላማ ከመግባት ውጭ ያለው አማራጭ

በቅድሚያ ፓርላማ ከመግባት ውጭ ስላለው አማራጭ ስንነጋር አንድ ጉዳይ ግልጽ መሆን አለበት:: ፓርላማ አለመግባትን የሰላማዊ አመጽ ትግል አካል በማድረግ፣የህዝቦችን መብትና ድምጽ ማስከበር፣ ህዝብ ለዴሞክራሲ ስርአት መገንባት እስካሁን ያደረገውን ጥረት አጠናክሮ በመቀጠል ወደ ተሻለ ደረጃ ማሳደግ እንችላለን ብለን ሰለምናምን ነው:: ፓርላማ አንገባም ማለት ብቻ ሳይሆን ከፓርላማ አለመግባት ውሳኔ ጋር በምናደርጋቸው ህዝባዊ ትግሎች አምባገነኑን የወያኔ መንግስት የህዝብን ድምጽ የሚያከብርበትን አስገዳጅ ሁኔታዎች መፍጠር እንችላለን ብለን ስለምናምንም ብቻ መሆን ይኖርበታል:: ፓርላማ አለመግባት በሰላማዊ ተቃውሞ የማይደገፍ ከሆነ ትርጉሙ ለዜሮ የቀረበ ይሆናል::

በእኔ አመለካከት ሰላማዊና ህጋዊ በሆነ፣ የህዝብ እምቢተኛነት ዴሞክራሲያዊና ህገመንግስታዊ መብቶች በመጠቀም ወያኔን የመሰለ አምባገነን ቢቻል የህዝብን ፍላጎት እንዲያከብር፤ ይህንን ለማድረግ ፈቃደኛ ካልሆነ በሃገራችንና በሌሎች ሃገሮች ህዝቦች ታሪክ እንደታዩት



አምባገነኖች በሙሉ ከምድራችን ላይ ጠራርጎ ማስወገድ የሚቻልባቸው አብዛኛዎቹ ቁልፍ ሁኔታዎች የተሟሉ ናቸው፤ የሚል እምነት አለኝ::

ከእነዚህ ሁኔታዎች ዋናውና መሰረታዊ የሆነው የወያኔ መንግስት በሁሉም መንገድ በህዝብ አይን በከፍተኛ ጥላቻና ንቀት የሚታይበት ደረጃ ላይ መድረሱ ነው:: ህዝብ የወያኔን መንግስት ጸረ-ህዝብ ጸረ-ሀገር፣ ድህነትንና ውርደትን አምራች የአምባገነኖች ስብስብ አድርጎ ማየት ብቻ ሳይሆን፣ ወያኔ የመንግስቱ ሃይለማርያምን ግፈኛ ስርአት ጭራቅነት በማስፈራሪያነት እየተጠቀመ ከጫነበት የ14 አመታት ተጨማሪ ፍራቻ የተላቀቀበት ሁኔታ ውስጥ ይገኛል:: ህዝብ የሚደርስበት በደልና ግፍ ሞልቶ በመፍሰሱ ተቃዋሚ ድርጅቶች የሰጡትን አደፋፋሪ አመራር በመከተል ፍራቻውን አውልቆ ጥሏል:: «አልፈራህም፣ በቃኝ! አንተን ከጫንቃዬ ላይ ለማውረድ ማናቸውንም መስዋዕትነት ለመክፈል ዝግጁ ነኝ» በሚል ህዝብ ፊት አምባገነኖች ረጅም ዕድሜ አይኖራቸውም:: የኢትዮጵያ ህዝብም ከዳር እስከዳር ከምሁሩ እስከ ደሃው ገበሬ የ1966ቱን አብዮት ድንክዬ ባደረገ የፖለቲካ ተሳትፎና አንድነት «በቃኝ» ማለቱን በምርጫውና ከምርጫው በኋላ እስከዛሬ በተከተሉት ወራት አረጋግጧል:: ይህ የህገሬው የእምቢተኛነት ስሜት ከሃገር ውጭ አልፎ በስደት የሚኖረውን በሚሊዮኖች የሚቆጠር ኢትዮጵያዊ ቀስቅሶ በታሪካችን ታይቶ የማይታወቅ ህዝባዊነትና ሀገራዊነት የተሞላው ትግል ውስጥ እንዲገባ አድርጎታል:: ህዝብ በሃገር ውስጥ ከሚያደርገው ደፋር ትግል በተጨማሪ በውጭ ሀገሮች የሚኖረው ኢትዮጵያዊ የወያኔን አምባገነንነት በማጋለጥ፣ ተቃዋሚዎቹን በገንዘብና በቁሳቁስ በመርዳት በውጭ የሚገኘው ኢትዮጵያዊ የሚያደርገው ተሳትፎ በታሪካችን ያልታየ ነው:: የአምባገነኖች ዕድሜ ከሚያሳጥሩት መሰረታዊ ማህበራዊ ሁኔታዎች አንዱ የህዝብ ድፍረት እና ቁርጠኛነት ዋንኛው ነው::

በምርጫው ወቅትና ከምርጫው በኋላ በተከተሉት ወራት ህዝብ መብቱን ለማስከበር ሲል

ማንኛውንም መስዋእትነት ለመክፈል ዝግጁ እንደሆነ ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ ይወክሉኛል ብሎ ለመረጣቸው ድርጅቶቹ በማያሻማ ቋንቋ ሲገልጽ ከርሟል:: ከጥቂቶች በስተቀር ይህ ስሜት ባለብዙ ደሞዝ ተከፋይ ባለሙያ-ዎችን፣ ከፍተኛ የንግድና የኢንዱስትሪ ባለሃብቶችን ጨምሮ የመጨረሻው የሃገሪቱ ምስኪን ደሃ ሁሉ ያካተተ ነው የሚል እምነት አለኝ:: ይህ ስሜት በሃገር ውስጥ በነበርኩባቸው ወራት በተለያዩ መድረኮች ሲገለጽ ያየሁት ሲሆን በቅርቡም የህዝብ አስተያየት ለማዳመጥ ቅንጅት በጠራቸው ስብሰባዎች ላይ ግለቱ ሳይበርድ እየተገለጸ ያለ ቁርጠኝነት ነው:: ሰላማዊና ህጋዊ በሆነ መንገድ ከወያኔ ጋር ለሚደረገው ትግል መሟላት ካለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች አንዱ የህዝብ ዝግጁነት ነው:: ይህ የተሟላ ይመስለኛል::ሌላው ከዚህ ጋር መጠቀስ ያለበት ጉዳይ የኢትዮጵያ ህዝቦች ከሚገኙ ‐ብት መከራና ስቃይ መውጣት የሚችሉት በቅድሚያ በራሳቸው ትግልና መስዋዕትነት ብቻ እንደሆነ የተረዱበት ሁኔታ መፈጠሩ ነው:: የውጭ መንግስታት ጣልቃ ገብነት፣ ወይም በስልጣን ላይ ያለው መንግስት ከፈጣሪ ቢታረቅ ወይም አንድ ተአምራዊ ነጻ አውጪ ድንገት ዱብ ብሎ ከወያኔ አረመኔያዊ አገዛዝ ነጻ የሚወጡበት ሁኔታ ሊፈጠር ይችል ይሆናል እያሉ በምኞት አለም የሚኖሩበት ዘመን ማክተሙ ነው:: በተለይ የአውሮፓና የአሜሪካ መንግስታት ከአንድ ሃገር ህዝብ የዴሞክራሲ ፍላጎት በላይ የእነሱ አገልጋዮች የሆኑትን አምባገነኖች በአለም ዙሪያ ሲደግፉ እንደኖሩ ህዝብ ተረድቷል:: በኢትዮጵያ ውስጥም በተመሳሳይ እነዚህ መንግስታት የራሳቸውን ፍላጎትና ጥቅም አስጠባቂ ነው ብለው ከሚያስቡት የወያኔ አምባገነናዊ መንግስት ጋር በመሆን የህዝብን ፍላጎት ደፍጥጠው ለመሄድ እንደማይቸገሩ ተገንዝቧል:: ይህ ግንዛቤም ህዝብ በራሱ ጥረትና ትግል ላይ ብቻ መተማመን እንዳለበት አስረድቶታል::

በሌላ በኩልም ህዝብ የሚታገልለት ስትራቴጂያዊ አላማ ምን እንደሆነ በግልጽ ማስቀመጥና ይህንን አላማ ለማሳካት የሚያስችሉ በየደረጃው



የሚወሰዱ ታክቲካዊ እርምጃዎችን ህዝብ እንዲረዳ ማድረግ ሌላው መሟላት ያለበት ቅድመ-ሁኔታ ነው::

የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ሃይሎች ይህንን በሚገባ የሰሩ ይመስለኛል:: ህዝብ የፖለቲካ ስልጣን በዴሞክራሲያዊ ምርጫ ከህዝብ ፍላጎት የሚመነጭ መሆኑን እንዲረዳ፣ተረድቶም በስፋት ወጥቶ እንዲመርጥ አድርገውታል:: ህዝብ በዚህ ግንዛቤ ላይ ቆሞ ነው፤ «ድምጼን አላስርቅም» በማለት የወያኔን ድምጽ ዘረፋ ለመቋቋም ቆርጦ የተነሳው:: የትግሉ ግብ የህዝብን ድምጽ አስከብሮ፣ ህዝብ የስልጣን ምንጭ መሆኑን ማረጋገጥ እንደሆነ ገብቶታል::ወደዚህ ግብ ለመድረስ ተቃዋሚቹ እየተከተሉ ያለውን ታክቲክ በመረዳት ለቀረቡት የመፍትሄ ሃሳቦች ድጋፉን በተለያዩ መንገዶች ገልጧል::

በትግል ታክቲክ ደረጃም ትክክል ይሁን አይሁን ቅንጅትና ህብረቱ አሁን ሃገራችን ከምትገኝበት የፖለቲካ አጣብቂኝ እንድትወጣ በማሰብ ጊዜያዊ የጥምር መንግስት እንዲቆም ሃሳብ አቅርበዋል:: ይህ የጥምር መንግስት ተቀባይነት ቢያገኝ ሃገራችን ሰላምና መረጋጋት በሰፈነበት፣ የህዝቦች ስቃይና መከራ ባልበዛበት መንገድ ፖለቲካው ለምዕተ-አመታት ከተጣባው የአመጽ አዙሪት ለአንዴና ለመጨረሻ ግዜ ነጻ የሚወጣበትን ሁኔታ መፍጠር እንደሚችል ግልጽ ነው:: አምባገነኑ ወያኔ ግን «የምን የጥምር መንግስት» በሚል ንቀት ሃሳቡን እንዳልተቀበለው አይተናል:: በተቃዋሚው በኩል ይህ ሃሳብ ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው ተብሎ የቀረበ በመሆኑ ወያኔ ተቀበለው አልተቀበለውም ካለንበት የፖለቲካ አጣብቂኝ መውጫው መንገድ ስለሆነ ተቀባይነት እንዲያገኝ መታገል አማራጭ የሌለው ጉዳይ ነው:: በፖለቲካ ትግልም ለአንድ ሁኔታ ትክክለኛ መፍትሄ ይሆናል ተብሎ የቀረበ መፍትሄ ሁኔታው ሳይቀየር የሚቀየርበት ምክንያት የለም:: በበኩሌ ተቃዋሚዎች ወያኔ እንደማይቀበለው እየጠረጠሩ ያቀረቡት የመፍትሄ ሃሳብ ስለሆነ ወያኔ አልቀበለውም ስላለ የመፍትሄ ሃሳቡን ትክክለኛነት የሚጠራጠሩበት ምክንያት አይታየኝም:: በመሆኑም ሁኔታዎች

ተቀይረው ሌላ መፍትሄ እስካላስፈለጋቸው ድረስ ተቃዋሚዎች ባቀረቡት የጥምር መንግስት ሃሳብ ላይ ጸንተው መቀጠል ይኖርባቸዋል:: ከዚህ በተጨማሪም ይህ የጥምር መንግስት ሃሳብ በህዝብ ዘንድ መጀመሪያ ገጥሞት የነበረውን ተቃውሞና ጥርጣሬ በማለፍ ከሞላ ጎደል ተቃዋሚውን የሚደግፉ የህብረተሰብ ክፍሎችን ሙሉ ድጋፍ ያገኘ ነው:: ይህ ሃቅ ህብረተሰቡን የፖለቲካ ግቡ ግልጽነት ባለው አጀንዳ ዙሪያ እንዲሰባሰብና እንዲታገል ለማድረግ ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው:: ተቃዋሚዎች ሃገራዊና ህዝባዊ ቀናነት ባለው መንፈስ ያቀረቡለትን የጥምር መንግስት ሃሳብ እንዳለ መቀበል ወይም በጠቅላላው ስልጣኑን ለአሸናፊዎቹ ፓርቲዎች ከማስረከብ ውጭ ሌላ አማራጭ እንደሌለው ለአምባገነኑ ወያኔ በሚገባው ቋንቋ ግልጽ አድርጎ ማስቀመጥ ያስችላል:: የአላማና የታክቲክ ግልጽነት የህዝብን አትኩሮት በመሳብ፣ ህዝብ ያለውን አቅም በሙሉ አስተባብሮ ከተፈለገው ግብ ለመድረስ ጥረት እንዲያደርግ የሚያግዝ ነው:: ከዚህ በላይ የጠቀስኩት የአላማ ግልጽነት፣ በህዝቡም ሆነ በተቃዋሚ ፓርቲ-ዎቹም መሃል አለ የሚል እምነት አለኝ::

ሌላው ከዚህ ጋር በሚገባ ሊፈተሽ የሚገባው ነጥብ ከላይ ያነሳናቸውን ሁኔታዎች መሟላትን የተገነዘበ፣በዚህ ግንዘቤም ላይ ተመስርቶ ወቅቱ የሚጠይቀውን አመራር ለመስጠት ዝግጁነት ያለው አመራርና ድርጅታዊ አቅም አለ ወይ? የሚለው ጥያቄ ነው:: ቀደም ብዬ እንደጠቀስኩት ትልቁ ችግር ያለው እዚህ ላይ ይመስለኛል::

የቅንጅትን የፖለቲካ ውሳኔ አስቸጋሪ ያደረገውም ይህ እውነታ ይመስለኛል:: ቅንጅት እንደድርጅት እንዲህ አይነቱን ዝግጅት ለማድረግ የሚችልበት ሁኔታ ባለማግኘቱ ሌሎች ሁኔታዎች ተሟልተው በሚገኙበት ባሁኑ ወቅት ሰላማዊና ህጋዊ የህዝብ እምቢተኛነትን በመጠቀም የፖለቲካ ግቡን ለመምታት እንቅስቃሴ ሲያደርግ አይታይም:: ቀደም ብለን እንደጠቀስነው የራሱንም፣ የድርጅቱንም ሆነ የህዝቡንም የዴሞክራሲያዊ ፍላጎት ፈጽሞ ማሟለት የማይችለውን



ፓርላማ የመግባት አማራጭ እንደ አንድ አማራጭ ማስተናገድ የጀመረው በእዚህ ምክንያት ሳይሆን አይቀርም የሚል ግምት አለኝ:: ይህ ፓርላማ የመግባት አማራጭ ግን የትም እንደማያደርስ ቀደም ብለን ያየነው ጉዳይ ነው::ያለው ምርጫ በድርጅታዊ ዝግጁነት ማነስ መወሰድ የሚገባውን ትክክለኛ የትግል አቅጣጫ ማጠፍ ሳይሆን ይህንን አቅጣጫ በስራ ላይ ለማዋል የሚያስፈልጉትን የጎደሉ ዝግጅቶች በከፍተኛ ጥረትና መስዋዕትነት በፍጥነት በማሟላት፣ ወቅቱ የሚጠይቀውን አመራር ለመስጠት መጣደፍ ነው:: የወቅቱ ትግል፣ ወያኔ ተገዶም ይሁን ወዶ የህዝብ ድምጽ የሚከበርበትን ሁኔታ እንዲቀበል ማድረግ ነው:: የዚህ ትግል የመጨረሻው ዝቅተኛ አላማ የቀረበውን የጥምር መንግስት ሃሳብ ወያኔ እንዲቀበል ከማስገደድ በታች የማይወርድ መሆን አለበት:: ይህ ትግል መሰረታዊ መነሻው የህዝብ ደምጽ የተከበረበት ፓርላማ ለመፍጠር ስለሆነ እንዲህ አይቱን ትግል የህዝብ ድምጽ በማጭበርበር ወያኔ በፍጹማዊ አምባገነንነት በመሰረተው ፓርላማ ውስጥ ገብቶ ሊከናወን እንደሚችል አድርገው የሚያስቡ ካሉ የአምባገነኖችን መሰረታዊ ባህርይ ያልተረዱ ናቸው:: ከህዝብ ከፍተኛ ተቃውሞ ያለበት ፓርላማ የመግባት ሃሳብ ተግባራዊ ቢሆን፣ በሃገር ውስጥና ከሃገር ውጭ ህዝብ ለተቃዋሚ ፓርቲዎች የሰጠው ድጋፍ አንዳች ነፋስ ያመጣው ይመስልብን ይሆን ብሎ ሊጠፋ የሚችልበት አደጋ ከፍተኛ መሆኑን በሚገባ መረዳት ያስፈልጋል:: የሃገራችንን ህዝቦች እጣ አስፈሪና ጨለማ የሞላው የሚያደርገው መሆኑን መረዳት ይኖርብናል:: ሌላው ቢቀር ከወያኔ ፓርላማ ባለመግባት ህዝብ በመሪዎቹ ላይ ያለው እምነት ሳይጎድል ወደፊት በሚገባ በመደራጀትና በመዘጋጀት ለግዜው የገጠመውን እንቅፋት ማለፍ እንደሚችል በራሱ ተማምኖ ለትግል ዝግጁ ሆኖ እንዲቀጥል የሚያስችለው ይሆናል::

በመጨረሻም ያለንበትን ሁኔታና መከተል የሚገባንን የትግል ስልት ለመወሰን ችግር እየፈጠረብን ያለው ጉዳይ የወያኔን የአፈና መዋቅር ጥንካሬ በሚገባ ለመገምገም አለመቻል እንደሆነ ይገባኛል:: ዞሮ ዞሮ

መከተል የሚገባንን የትግል አቅጣጫ በዋነኛነት የሚወስነው የህዝቡና የመሪ ድርጅቶቹ ዝግጁነት እንጂ የወያኔ የአፈና መዋቅር ጥንካሬ አይደለም:: ከዘረኛው ወያኔ የበለጠ ከፍተኛ ጥንካሬ የነበራቸው አምባገነን መንግስታት በተባበረው የህዝቦች እምቢተኝነት ፊት ውልቅልቃቸው ሲወጣ አይተናል::

ወያኔ ተቃዋሚውንና ህዝብን ለማስፈራራት የማያካሂደው ፕሮፓጋንዳ የለም:: «ኢንተርሃምወይ ሆኜ እፈጃችኋለሁ ከማለት አንስቶ አርስ በርሳችሁ እንድትፋጁ፣ አገሪቷም ውልቅልቋ እንድትወጣ ማድረግ እችላለሁ» እስከማለት ሄዷል:: ከመቸውም የባሰ ዘረኛ ቅስቀሳና ድርጊት ባሁኑ ወቅት እየተፈጸመ ያለው ለዚህ ነው:: በሬድዮና በቴሌቪዥን በተቃዋሚ ድርጅቶችና መሪዎች ላይ የሚካሄደው ስድ ፕሮፓጋንዳ የዚሁ የማስፈራራት አላማው አካል ነው::

ከዚህ ውጭ ግን ወያኔ የሃገሪቱን የጦር ሃይል፣ የፖሊስና የደህንነት መዋቀር በመጠቀም የህዝብን ሰላማዊ ትግል ለማፈን የሚችልበት አቅሙ በሀገራችንና በሌሎች ሃገሮች ከነበሩት አምባገነን መንግስታት በጣም የደከም መሆኑ መታወቅ አለበት::

በተደጋጋሚ ከፖሊሱም፣ ከሰራዊቱም ሆነ ከደህንነቱ መሃል በወያኔ ላይ ከፍተኛ ተቃውሞ እንዳላቸው የገለጹልንና በተግባር ያሳዩንም አባላት ብዙ ናቸው:: ወደፊትም ቢሆን ወያኔ ዘረኛ በሆነ መንገድ ለማካሄድ ለሚያስበው እኩይ እቅድ ተባባሪ እንደማይሆኑ እስከአሁንም የተፈጸመው ግፍና በደል የሚያቃጥላቸው መሆኑን የነገሩንም ሞልተዋል:: በተለያዩ ብሄሮች ተወካይነትና መሪነት ስም ለወያኔው ንጉሠ ነገሥት ያደሩ እንደራሴዎች በተለያዩ መድረኮች የመሪያቸውን አምባገነናዊ ጩኸት እንደበቀቀን ሲያስተጋቡ ስንሰማ፣ በስራቸው ታፍኖ ያለው ካድሬና ሰራዊት የእነዚህን ጉደኞች ጸረ-ህዝብና ጸረ-ሃገራዊነት የማያውቅ፣ ዝም ብሎ የሚከተላቸው አድርገን መገመት የለብንም:: በሃገራችን ታሪክ ተሰምቶ በማይታወቅ ደረጃ በህዝብ የተጠላ መንግስትና ባለስልጣናቱ በህዝብ



መሃከል በሚኖሩ የህዝቡን ብሶት በሚያዳምጡ ችግሩንና ስቃዩን በሚጋሩ ወታደሮችና ፖሊሶች ይደገፋሉ ብሎ በማሰብ የወያኔን የአፈና ጉልበት አጋንኖ ማየት ስህተት ይመስለኛል:: እንዲህ አይነቱም የሁኔታዎች ግምገማ ላይ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች በመረጃ ላይ የተደገፈ ጥንቃቄ የተሞላው ጥናት ማድረግ ይገባቸዋል:: ይህ ጉዳይ በህዝባዊ እምቢተኛነት የትግል ስልት አማካይነት የሚደረግን እንቅስቃሴ በማበረታታት ወይም በማዳከም የራሱን ጫና ማሳደር የሚችል በመሆኑ በቀላሉ መታለፍ የለበትም::በበኩሌ ግን የወያኔ ቀፎነት በሞራል ሰርጥ ብቻ ሳይሆን፣ የህዝብን ትግል ለመጨፍለቅ የሚያስችል ፖለቲካዊም ሆነ ወታደራዊ አቅም የሌለው በመሆኑም ይገለጻል ባይ ነኝ::

ያለምንም መስዋዕትነት ሰላማዊ የህዝብ እምቢተኛነት ትግል ካሰብነው ግብ ያደርስናል የሚል እምነት የለኝም:: እንዲህ አይነቱ የትግል ስልት ግን በአነስተኛ ኪሳራ የዴሚክራሲያዊ ስርአት ማምጫው ብቸኛ መንገድ ነው:: በሃገራችን ይህንን ትግል ለማድረግ የሚያስችል የተመቻቸ ሁኔታ አለ:: ተቃዋሚ-ች ይህንን ሁኔታ በሚገባ ለመጠቀም የሚጎድሏቸውን ዝግጅቶች በፍጥነት አሟልተው አመራሩን መስጠት ይጠበቅባቸዋል:: ከዚህ ውጭ ያለው አማራጭ የህዝብን የነጻነት ቀን የሚያርቅ ብቻ ሳይሆን ሃገራችንና ህዝቦቿ የሚከፍሉትን መስዋዕትነት ከሚገባው በላይ የሚያገዝፍ ይሆናል::

ጥንካሬ:ለቅንጅትና:ለኢትዮጵያ

ዴሞክራሲያዊ ሃይሎች በሙሉ!! !!

ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!

"ማን ይናገር? የነበረ ማን ያርዳ? የቀበረ" እንዲሉ ነው የአንዳርጋቸውን ጽሁፍ ያቀረብኩት:: እኔ በሩቅ ከማውቃቸው፣ ያውም ስማቸውን እንኳን በማልለየው ሰዎች አስተያየት ከመሰንዘር እንዲህ ቁልጭ አርጎ የሚያውቃቸው ቢናገር

ይሻላል::አንዳርጋቸው ወገናዊ ሆኖ አልጻፈም ተቃዋሚ ሃይሎችንም ድክመታቸውንና ስህተታቸውን ከመናገር አልተቆጠበም:: ለሁሉም ድርሻ ድርሻውን አስረክቧል::

ቅንጅት ሁሉም ነገር በአመራሩ እየተወሰነ አባላቱ የታዥከላቸውን የሚውጡ ሳይሆኑ፣ እራሳቸው በሚመለከታቸው ጉዳይ ላይ ተሰብስበው፣ ሃሳባቸውን አቅርበው ተከራክረው ወይ አምነው አለያም አሳምነው፣ ወደ ውሳኔ ይሄዳሉ:: ይህ ነው ዴሞክራሲያዊ አሰራር:: እያንዳንዱ ያቀረበውን ሃሳብ ካላንዳች ተጽእኖ ወይም ተቃውሞ፤ በአመራሩም ምንም አይነት ጫና ሳይደረግበት እገመገማለሁ ብሎ ሳይፈራ፣ የሚያሸማቅቁ አነጋገሮች ሳይሰነዘሩበት በነጻ ይወያያል፤ ግለሰባዊ መብቱን ያስከብራል::

ቅንጅት ከሕዝቡ፣ ከአባላቱ፣ ከደጋፊዎቹና ከላእላይ ምክር ቤት አባላቱ ጋር ካደረገው ስብሰባና ከተገኘው ምላሽ በመነሳት ከመስከረም 25/98 ጀምሮ ባሉት ቀናት የስብሰባዎችን ውጤት ተግባራዊ ለማድረግ ስብሰባውን መርህ በሆነው ሰላማዊ ትግል መንፈስ ቀጠለ::

ስብሰባዎቹም በላእላይ ምክር ቤት አባላት፤ በተወካዮች ምክር ቤት ተመራጮች ተካሄዱ:: በተከታታይ ቀናት የተነሱት የውይይት ርእሶች ፓርላማ መግባትና አለመግባት፤ ከገዢው ፓርቲ ጋር ስለተጀመረው ድርድርና ስለተከሰተው ችግር የቅንጅት ሥራ አስፈጻሚ በድርድሩ ሊካተቱ ስለሚገባቸው ነጥቦች ለሁለት ቀናት ከተወያየ በኋላ የደረሰበት ውሳኔ ዴሞክራሲ ቀርቶ ምንም የዴሞክራሲ ጠረን በማይሸትበት ፓርላማ መግባት ወንበሩ ባዶ እንዳይሆን የወንበር ሽፋን ከመሆን ያለፈ ተግባር ስለማይከናወንበት አለመግባቱ ይመረጣል:: ከሕዝቡ በቀረቡ 8 ነጥቦች መነሻ፤ ጠ/ሚኒስትሩ "ያለምንም ገደብ በምንም ጉዳይ ላይ ለመወያየት ዝግጁ ነን" በማለታቸው ያ ቃል የሚፈርስና የመወያያ ነጥቦች ለገዢው ፓርቲ በሚስማማ መልኩ የሚነደፉ ከሆነ፤ "አትግቡ" ብሏልና



የባለድምጹን ሕዝብ ውሳኔ ለማክበር እንገደዳለን በማለት ተወሰነ::

በኢህአዴግና በቅንጅት፣ ወይም በሌሎች ተቃዋሚ ድርጅቶች መሃል ልዩነት ቢኖር የአመለካከት እንጂ የአዛዥና ታዛዥ፤ የበላይና የበታች መሆን አልነበረበትም:: የሚታየው ዕውነታ ግን የተለየ ነው:: ኢህአዴግ እራሱን እንደ ፓርቲም እንደ መንግሥትም ሆኖ ነው የሚያቀርበው:: ቀደም ሲል እንደገለፅኩት ኢህአዴግ እንደ ፓርቲ ምረጡኝ እያለ ይከራከራል፣ እንደመንግሥት ደሞ ያዛል::እንደ ፓርቲ እምቢ ይላል፤ እንደ መንግሥት ደሞ «ዋ!» በማለት ስለሚራመድ ድርድሩን ከማቋረጥ የተሻለ መፍትሔ አልነበረም::

## ወደ ድምሳሴ ቅንጅት

### ጥቅምት 22/98

ጥቅምት 22/98 ጠዋት ጸጥ ብሎ ያደረው አየር ተለወጠ:: በርቀት የብሶት ድምጾች የምሬት ዜማዎች መሰማት ያዙ:: አልፎ አልፎና እየቆየ የጥይት ድምጽ ሲያፏጭ ዝማሬዎችና የብሶት ድምጾች ወደ እሪታና ዋይታ እየተለወጡ ማስተጋባት ያዙ:: ወዲየው የጥይቱ ድምጽ ረጋ ሲል ያው የቅድሙ አይነት የብሶት የምሬት ድምጽ ይመለሳል::

የነገ ተተኪ መሪዎች፣ የሃገር ተረካቢ ዜጎች፣ ኢትዮጵያችንን "አንለቅም" ብለው በየተራ ከሚነሱ መሪ-ዎች ራስ ወዳድነትና ግድ የለሽነት መዳፍ፣ ከዘመናት የድህነት አረንቋዋ ውስጥ እንድትወጣ፣ ሕዝቡዋም በላዩ ላይ እንደመርገምት ተከምሮ የሰራ አካላቱን ከሚበላው የድህነት ተስፋ የሚገላገልበትን መንገድ ፍለጋ ነው እሪታቸው:: ዋይታው በአንድ ቦታ የተወሰነ ሳይሆን በየአቅጣጫው የተነዛ ነበር:: ሕዝቡ ገዢው ፓርቲ ባጸደቀው ሕገመንግሥት ባሰፈረው መብት በመመራት መሰረት ነበር ፍላጎቱን ለመንግሥት ለመግለጽ የወጣው::

የጠዋት ጸሐይ እየፈካች ስትሄድ ግን ሁኔታዎች እየጨለሙ መታየት ጀመሩ:: ያ ያመንነው ባለመሳርያ አይዞህ በማለት ፈንታ አነጣጥሮ መጣልን፣ ሕገመንግሥታዊ መብትን በማክበር ፈንታ መንፈግን መረጠ:: ያ የወጣት ስብስብ የሚያየውን መቀበል፣ የሕገመንግሥቱን መመርያ መጠራጠር ያዘ:: ያም ሆኖ ከተ ነሳለት አላማ ከፊት ለፊቱ መሳሪያ በደገነ ሃይል በመደናገጥና በፍርሃት አላፈገፈገም:: እውነትን ይዞ የተነሳ በመሆኑ ለአላማው በጽናት ቆሞ ማስፈጸምን መረጠ:: «እኛ ወገኖችህ እንጂ ጠላት አይደለንም፣ ያንተ ተግባር የሃገርና የሕዝብን መብት ማስጠበቅ እንጂ የሕዝብን መብት መጣስና መርገጥ አይደለም» በሚል መንፈስ የወደረውን የጦር መሳርያ ዘወር እንዲያደርግ ቢማጸኑትም እሱ ግን የተሰጠውን የአነጣጥረህ ምታ! ተልዕኮ፣ ጸታ፣ እድሜ፣ ሳይለይ ተግባራዊ በማድረግ ገና አድገው ያልጨረሱትን ዜጎች ረፈረፋቸው::

«ያመኑት ፈረስ.. .. .. » እንዲሉ እምነት ጠፋ:: ሕገመንግሥቱ በጦር መሳሪያ ተሸረሸረ:: የአገር ድንበርንና ሕዝብን ለመጠበቅ ተብሎ የተዋቀረው ሃይል በራሱ ሕዝብ ሕይወት ላይ ፈረደ:: ያ ከተደገና መሳርያ ውስጥ ይዘንብ የነበረ ጥይት ተላላፊ፣ መንገደኛ፣ ጠንካራ፣ ደካማ፣ ማንንም ከምንም ሳይለይ በሚንቀሳቀስ ነገር ላይ ሁሉ አነጣጥሮ ሞት እየተፋ ንጹሃንን በየአውራ ጎዳናው ላይ ደፋ::

ምርጫ 97 ሲጀመር « ያለምንም እንከን » በሚል ቃለ መሃላ የተሰጠው መብት ሁሉ እንዳልነበር፣ የተጠበቀው ብርሃን እንዳይወጣ ታገደ:: የለመለመ ተስፋ አንግተው የምርጫውን እውነታ ለመፈለግ የወጡት፣ ላይመለሱ ሕይወታቸውን አጡ:: በየቦታው ወላድ ልጄን እያለች ለመጮህ ድምጽ አጣች:: ልታምነው የማትችለውን ስታይ አይኑዋን ማመን እያቃታት፣ የማይሰማ እሪታ ሞከረችና ትንፋሽ አጠራት አፍዋ ተከፈተ እንጂ ላንቃዋ መጮህ አቃተው:: የምር መሆኑን፣ ልጅዋ ባይሆንም የወደቀው ታዳጊ የነገ ተስፋ መሆኑን፣ የሱዋም ልጅ ገና ባታየውም እንደወደቀው ታዳጊ ወድቆ እንደሚሆን እያሰበች፣ ቀስ በቀስ የጠፋው



ድምጿ ከተከፈተው አፍና ከተዘጋው ላንቃ ውስጥ እየወጣ አካባቢውን አናጋው:: የአንድ ሰው ይመስል የነበረው እሪታ የብዙዎች እየሆነ በአንድ ቦታ ይመስል የነበረው በአራቱም ማእዘናት ተቀጣጠለ፣ እንደገደል ማሚቶ ተቀባበለ:: ሲነጋ ጸጥ ረጭ ብሎ የነበረው ንጹህ አየር በጥይት ባሩድ አየሩ ተናጋ:: ለመኪና መመላለሻ የተሰራው አውራ ጎዳና የታዳጊ ወጣቶች አስከሬን መከመርያ ለውሃ ገርፍ የተሰራው ቦይ የወገን ደም መፍሰሻ ሆነ::

የወላድ አይን ጉድ አየ:: ወንድም በጥይት የወደቀ ወንድሙን "ወይ የናቴ ልጅ" ብሎ ሊያነሳው ሲያጎነብስ፣ ወንድሙ ሬሳ ላይ በወገኑ ጥይት ተደፋ:: ቆስሎ የወደቀው "እባክህ እናቴ ጋ ውሰደኝ፣ ሃኪም ቤት ትወስደኛለች" የሚለው ሕጻን በአነጣጥሮ ተኩዋሹ ወገኑ ዝም እንዲል የማጣሪያ ተኩስ ተተኩሶበት ወደ እናቱ ሳይሆን ወደ ዘልአለማዊ ቤቱ ሄደ::

ያም ሆኖ ያ የወጣት ስብስብ «ሰላማዊ ሰልፍ በሕገመንግሥቱ የተሰጠኝ የዜግነት መብቴ ነው » ቢል:« የምርጫ ድምጼን ለማስከበር በመውጣቴ ወንጀለኛ አትበለኝ » ቢልና የሚሰማው ቢያጣ በተቻለው እራሱን ከጥይት ከአነጣጣሪ ተኩዋሽ እየተከላከለ ድምጹን ከፍ አድርጎ ተቃውሞውን በሰላማዊና በዴሞክራሲያዊ መንገድ ለማስከበረ ሞከረ:: ጥይቱ እየበረታ፣ እየበረከተ፣ ከአቅም በላይ እየሆነ ሲሄድ ወጣቱ እየተከበበ ተያዘ:: ገሚሱ ያመረረ፣የማይመለስ፣መግባባት ሊኖር የማይችልበት ሁኔታ መሆኑን ሲረዳና ተስፋው ሲጨልም፣ ሕገ መንግሥታዊ መብቱ በመሳሪያ ሲቀማ አፈገፈገ::

በጎዳናዎች ላይ ይህን መሰሉ ጭፍን ሁኔታ ሲካሄድ፣ በአንዳንድ የቅንጅት አመራሮች፣ የነጻው ፕሬስ አባላት፣ የሕዝባዊ ድርጅት አባላት መኖሪያ ቤቶችና ቢሮዎች አካባቢ ደግሞ የታጠቀ ጦር ተመድቦ በመዘዋወር እያነቀ በመኪና መጫንና ወደ ማእከላዊ ማጉዋጉዋዙን ተያያዘው:: በቅድሚያ የአዲስ አበባ ከንቲባ ተመራጭ ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ወደቤቱ

ከሚወስደው መንገድ ላይ፣ በደገኑ ባለጦር መሳሪያ ወታደሮች ተገዶ ከነመኪናው ወደ ማእከላዊ፣ የቅንጅት ሊቀ መንበር ኢንጅነር ሃይሉ ሻውልም፣ ሌሎችም ከየቤታቸው ወደ ማእከላዊ ተወሰዱ::

እኔ ቤቴ ቁጭ ብዬ ማን እንደተያዘ በስልክ እከታተላለሁ:: ያገኙ ሃይል ወደኔ ቤት እየቀረበ መጣ:: የሳእላይ ምክር ቤት አባል ነኝና ለኔም አጃቢ እንደሚመጣልኝ እያሰብኩ ከቤተሰቤ ጋር ስለዚሁ ሕገወጥነት ጉዳይ በማውራት ላይ ሳለሁ ተራዬ ደረሰና እኔም ወደ ማእከላዊ:: ቤቴ ከማእከላዊ ብዙም ባይርቅ የሄድንበት መንገድ ግን ረዘም ያለ ሰአት ወስዷል:: በቀጥታው መንገድ አልነበረምና የምንሄደው "ጡጫና አርግጫ አይቀርልኝም" እያልኩ ለመቀበል ተዘጋጅቼ እያለሁ፣ ምንም ሳይደርስብኝ ማእከላዊ ደረስን::

እንደደረስኩ ይዘውኝ የሄዱት ለሚመለከታቸው አስረከቡኝና አንድ ቢሮ ውስጥ ገባሁ:: አንድ ፖሊስ ብቻ በሩ ላይ ግድግዳውን ተደግፎ ቆሟል:: ጠባቂ መሆኑ ነው አልኩ ለራሴ:: ትንሽ ቆይቶ አንድ ሌላ ጠይም፣ ቀጭን ፖሊስ መጣ:: የፖሊስ ቆመጥ ይዟል:: ገና እንደገባ ሲያየኝ ደሙ ይንተከተክ ጀመር:: «ወይ ጥጋብ! ምን ሆንን ነው የሚሉት?» አለና ዱላውን በንዴት እየወዘወዘ ትኩር ብሎ ከንፈሩን እየነከሰ እስኪበቃው አየኝና «እህስ የኛ የማስታወቂያ ሚኒስትር እንዲያው ይቺ ቅንጅት አሮጊት ብቻ ነው የምትሰበስብ?» አለ:: ደሞ ዱላውን ወዝወዝ ወዝወዝ አደረገ:: አይኔ እጁ ላይ ነው:: ድንገት አናቴን ለማለት ቢሰነዝር ትከሻዬን ለመስጠት በጥንቃቄ ጠበቅሁ:: ይፎክራል:፣ "ሕገመንግሥቱን ለመናድ? ሕገመንግሥታዊ ሥርአቱን ለማፍረስ? እ?" አለ፣ ልክ የተነገረውን የሰማውን:: ወዲያው ግልፍ እንዳለው አይነት፣ «ምነው ደከመህ እንዴ? ገና ምኑ ተያዘና? ሥልጣን እኮ እንዲህ በቀላሉ አይገኝም:: እኛ እኮ ስንት መከራ በልተን ነው ያገኘነው:: ስንቱን ዳገትና ቁልቁለት ወጥተንና ወርደን፣ በስንቱ በረሃ ተቃጥለን፣ በብርድ ተጠብሰን ነው ለዚህ የደረስነው:: በከተማ በመኪና እየተንቀባረርን አይደለም:: እና፣ ምኑም ሳይጀመር



ደከመህ?ወጣ ብሎ ትንሽ በረሃውን ዳገት ቁልቁለቱን መሞከር ነው:: እንዲሁ በሃይል ለማፍረስ?"....... ብዙ ነው የወተወተው:: አንድ ነገር እቀበልለታለሁ:: እውነቱን ነው! ጋራ ሸንተረሩን፣ ዳገት ቁልቁለቱን፣ ግለት ቅዝቃዜውንና ሌላም አስቸጋሪ ሁኔታዎችን ማለፉን አዎን እቀበላለሁ:: ያ ማለት ግን በሥልጣን ላይ እስከዝንተ ዓለም ድረስ ለመኖር ሳይሆን፣ አብረን ተባብረን ከጣልነው መንግሥት በከፋ መልኩ ሕዝብን ለመርገጥና ለመግዛት አይደለም:: ሕዝብ በነጻነትና በዴሞክራሲ ፍትሓዊ የሆነ ምርጫ እንዳያካሂድ፣ ወይም ምርጫን በማጭበርበር ስልጣን ላይ ለመቆየት፣ ያም ካልሆነ መብቱን ለማስከበር የወጣን ሰላማዊ ሕዝብ በጠበንጃ በማሽማቀቅና በመረሸን ለማስገደድ እንዳልሆነ ግን ብነግረው ደስ ባለኝ ነበር:: ግን የሰውዬውን ሁኔታና እኔ ያለሁበትን በማገናዘብ ዝም ማለትን መረጥኩ:: መልስ ብሰጠው የሚቀጥለው ግንኙነታችን የቃላት ሳይሆን የጉልበት ስለሚሆን "እረፍ! ተው!" አልኩት፣ እራሴን:: መልስ እንደማልሰጠው አውቆ ጥሎኝ ሄደ::

አንድ ረጋ ያለ ፖሊስ መጣና "ንብረትህን ልረከብህ ነው" ብሎኝ የኪስ ቦርሳዬን፣ ቀበቶዬን፣ የጫማ ማሰርያዬን በደረሰኝ አስረክቤ ተመልሼ ተቀመጥኩ::ወዲያው ያ ፎካሪው ተመልሶ መጣና፣ "አሁንም አለህ" በሚል አመለካከት እያየኝ «ደሞ በዘር ልታጠፉን? ግድ የለም፣ ልክ ትገባላችሁ! ፓርቲውን መቃወም ትችላላችሁ፣ በዘር ስትመጡ ግን ዝም ብለን አንመለከትም:: አንተ በቀደም ገብተህ አልወጣህም? ለምን አርፈህ አትቀመጥም? ለምን አታርፍም?» እያለ ዱላውን እየወዘወዘ በፉከራው አስለቀኝ:: የመጣው ይምጣ አይነት «ለምን አትተወኝም? የምጠየቅበት ጉዳይ ካለ በስነስርአት እጠየቃለሁ ያንተና የኔ መነጋገር ዋጋ የሚኖረው አይመስለኝም:: እስካሁን ያወራሃው አንዱም አልገባኝም:: ባለፈው ታስረህ ነበር ላልከው ያለምንም ጥፋቴ በናንተው ትእዛዝና ፍላጎት የሌለ ወንጀል ፈጥራችሁ ነው ያሰራችሁኝ:: ደሞ ስለፓርቲው አያገባኝም አትበለኝ፤ የፓርቲ አባል ያልሆነ እንደዚህ በምሬት አይወነጅለንም» በማለቴና እውነት ያለው ነገር

በማንሳቴ «ምነው አይበቃህም?» ሲል ዝም አልኩ። ስሜቴን ገልጫለሁ።

ያ ረጋ ያለው፣ እቃዬን የተረከበኝ ፖሊስ አንድ ሰው አስከትሎ መጣና እኔንም ተረካከቡኝ። የተረከበኝ ወደ ውስጥ ይዞኝ ገብቶ አንድ ክፍል ከፍቶ አስገባኝ። በክፍሉ ውስጥ ማንም ምንም የለም። ፖሊሱ ደሞ ከውጭ ዘግቶት ስለሄደ የምጠይቀውም ሰው የለም። በቃ ቆሜ ነው የማድረው። ካለኝ የጤንነት ችግር የተነሳ እዚህ ስሚንቶ ላይ ተኝቼ አድሬ ነገ ሰው አልሆንም፣ እያልኩ በሃሳብ ላይ እያለሁ በሩ ተከፈተና ያው ያመጣኝ ፖሊስ «ቤተሰብ ያመጣልህ ነው» ብሎ የተጠቀለለ እስሊፒንግ ባግ፣የምግብ ሰሃን፣ጋቢና የማእከላዊውን ፍራሽ ጥሎልኝ ሄደ። ቢሰማኝም ባይሰማኝም «እግዜር ይስጥልኝ» አልኩ። ጥቂት ቆይቶ ተመለሰና በበሩ ላይ ያለችውን ፍርግርግ መስኮት መሳይ ክፍተት በጋዜጣ ዘጋውና ሄደ። ጭለማ ስለነበር "ምን እንዳላይ ወይስ ማን እንዳያየኝ ብሎ ነው?" ብዬ ገርሞኝ ነበር። በኋላ ምክንያቱን ተረዳሁ፣ ከፊት ለፊት ያለውን እስረኛ አጮልቄ እንዳላይ ነው።

ያንን የመጣልኝን ስልፒንግ ባግ ማእከላዊ ፍራሽ ላይ ዘርግቼ ጋቢውን ለበስኩና በመቀመጥ ትንሽ ምግብ ቀምሼ ቡናዬን ተያያዝኩት። ስለ ማእከላዊ በወሬ የማውቀው ብዙ ችግር ስለነበር መጥተው ወስደው ፍዳዬን ያስቆጥሩኛል በሚል ጥርጣሬ መጠበቅ ያዝኩ። ማንም ዝር አይልም። ምናልባት እንቅልፍ እስኪያደክመኝ ይሆናል የሚጠብቁት ስለዚህ እስቲ ትንሽ ልቆይ እያልኩ ጨዋታዬን ከቡናዬ ጋር ቀጠልኩ። እኩለ ሌሊት አለፈና ድምጽ ሰማሁ። እኔ ካለሁበት ቤት በታች በር ተከፍቶ ሰው ገባ። ንግግራቸው ይሰማኛል። በሩ ወዲያው ተቆለፈ፤ የውጪውም በር ሲዘጋ ሰማሁ። አይ ለነገ ቢያሳድሩኝ ነው ምናልባት ሁላችንም ተጠናቀን እስክንገባ ድረስ ይጠብቁ ይሆናል ብዬ ጋቢዬን እንደለበስኩ ውስጥ ገብቼ እንቅልፍ ሸለብ እንዳደረገኝ የሚንክሻክሽ ድምጽ ሰማሁ። ቀስ ብዬ ፊቴን አውጥቼ ሳይ የፈጣሪ ያለህ! ከ10 በላይ የሚሆኑ ወጠምሻ ወጠምሻ አይጦች፤ እንደሰለጠነ ወታደር ተከታትለው



በገቡበት የመዝጊያው ክፍተት ወጡ። መመለሳቸው አይቀርም ብዬ እዚያው ያገኘሁትን የውሃ ፕላስቲክ ሰብስቤ በበሩ ስር ጠቀጠቅሁት። ይበሉት ይሆን? እያልኩ ከሀሳቤ ጋር ስሟገት ከሌሊቱ 10 ሰአት አለፈና ተኛሁ። እንቅልፍ አይባልም በየ15 ደቂቃው እነቃለሁ። መጨረሻው ላይ ከተኛሁበት የነቃሁት የክፍሌ በር ተከፍቶ ለሽንት ውጣ ስባል ነው። ሽንት ቤቱ ሳየው በጣም ጨነቀኝ፣ ሰሃን የለውምና ወርዶ ቁጭ ማለትን ይጠይቃል። እኔ ደሞ ወገቤ በሽተኛ ስለሆነ ታች ወርዶ መነሳቱ ጭንቅ ነው። አይቀር ነገር ሆነና የግዴን በጭንቅ ወርጄ፣ በጭንቅ ተነሳሁና ወገቤ በጣም አሰቃየኝ። ስለዚህም ምግብ መቀነስ አለብኝ። ሌላ አማራጭ የለውም።

ማታ ማታ ለውሃ ሽንት በመኝታ ቤታችን ባልዲ ስላለን ሌላውን ጣጣ በጊዜ በር ሳይዘጋ ማጠናቀቅ ግዴታ ነው ቀንም ቢሆን እስከተወሰነ ቀን ድረስ በሩ ሙሉ ቀን ይዘጋ ስለነበር መጠቀሚያዬ ባልዲው ነበር። በማግስቱ ጠዋት እንደገና ወደ ሽንት ቤት ስሄድ አንድ ቂጡ የተቀደደ ባልዲ አየሁና ጠባቂ ፖሊሴን ችግሬን ነግሬያቸው፣ አስፈቅጄ አስገባሁትና በካናቴራ ጠርዙን ሸፍኜ የሽንት ቤት መቀመጫ ሰርቼ በመጠኑም ቢሆን ረዳኝ። በቃ የመጀመሪያው የማእከላዊ ንብረቴ ያ ባልዲ ሆነ።

በሁለተኛውም ቀን ያ የፈራሁት ነገር አልደረሰብኝም ሌሊቱን ጠበቅሁ፣ እስከ እኩለ ሌሊት ድረስ አዳምጬ ተኛቼ አደርኩ። ትናንት በውሃ ፕላስቲክ የተከላከልኳቸው ዓይጦች ምን ያህል እንዳስቸገሩኝ ጠዋት በሩን ከፍተው ወደሽንት ቤት ለወሰደኝ ተረኛ ስነግረው፣ ለበር መጠቅጠቂያ የሚሆን የብርድ ልብስ ቁራጭም አገኘሁ። የባልዲው ተጨማሪ ንብረቴ እሱ ነበር። ጠዋት የሌሊት ሽንት ልደፋ ባልዲውን ይዤ ስወጣ የመሽተት ባህሪ ስለነበረው ቢሰራ ብዬ የጥርስ ሳሙና በጥብጬ ባልዲውን ካጠብኩ በኋላ ከውሃ ጋር ባልዲው ውስጥ ጨመርኩት፣ ለጊዜው ሽታው ጠፋ። ደሞ አድሬ ማታ ማየት ነው አልኩ።

ከሽንት ቤት ስመለስ ከፊት ለፊት የመምህራን ማህበሩን ካሳሁንን አየሁት (ስሙ ካሳሁን መሆኑን፣

ከመምህራን ማህበር መምጣቱን በኋላ ነው ያወቅሁት)፣ ቀድሞ ስላማላውቀው ማን እንደሆን አልለየሁትም ነበር:: በኛ ጉዳይ ይሁን አይሁን አላወቅሁም እንዲያው ሰላም ተባባልን::ከኔ በላይ ባሉት ክፍሎች ውስጥ በርካታ ታሳሪዎች አሉ፣ እነሱ አውቀውኝ ሰላም ብለውኛል እንጂ እኔ አለየኋቸውም:: ከኔ ወደታች ባለው ክፍልም ሰዎች አሉ፣ ግን እነማን እንደሆኑ አላወቅሁም::

በሁለተኛው ቀን ከተማው መረጋጋት ስለሌለው መንቀሳቀስ ችግር ፈጥሮ ስለነበር ቤተሰብ አልመጣም::ቤተሰብ ካልመጣ ደሞ ምግብም አይመጣምና የማእከላዊን ምግብ መመገብ ብቻ ነው ያለው አማራጭ:: ከእስር ቤቱ የቀረበልኝን ቁርስ በላሁ፣ ሻይም ጠጣሁ:: ከቤት የመጣ ምንም ነገር የለም፣ እንዲያውም የሌሎች ታሳሪዎችም ስንቅ አልመጣም፣ ሲጠሩም አልሰማሁም:: ትንሽ ቆይቶ ረፋዱ ላይ ውጣ ተባልኩ:: ፖሊስ መጣና «ቁልፍ ይዘሃል?» አለኝ « የምን ቁልፍ?» « የቤትህን» « እንዴ ቤተሰቦቼ እኮ ቤት ናቸው፣ እነሱ ጋ ነው» አልኩትና እንግዲያው ና እንሂድ ብቻ ብሎኝ ወዴት እንደሆነ ሳይነግረኝ አስወጣኝ:: ይዞኝ ሄደ:: ከመኪና ማቆሚያው ጋ ስንደርስ ፖሊሶች ቀድመው አንድ መኪና ውስጥ ገቡና የቤቴን አድራሻ ጠይቀውኝ እኔንም መኪናው ውስጥ አስገብተው ወደ ቤቴ መንገድ ቀጠልን:: የምንሄደው ወደ ቤት መሆኑን የቤቴን አድራሻ ስለጠየቁ ጠረጠርኩ እንጂ፣ እነሱ እዚህ ቦታ ነው የምንሄደው የምንሄድበትም ምክንያት እንዲህ ነው አላሉኝም::

የሩፋኤልን አቅጣጫ ይዘን ስንሄድ አልፎ አልፎ ተኩስ የጩኸት ድምጽ ይሰማል:: ፖሊሶቹ የተረጋጉ አይደሉም፣ ተኩስ በተሰማ ቁጥር የመደናገጥ ስሜት ይታይባቸዋል:: ደርሰን ወደኔ ግቢ ከገባን በኋላ በጣም በርካታ ጥይት ተተኮሰ ጩኸቱም በጣም በዛ:: መኪና ውስጥ ቁጭ እንዳልኩ ነኝ፣ ቤተሰቤ ወጥቶ በረንዳ ላይ ነው:: ልጆቼና ባለቤቴ "ሰላምታ እንስጠው ወይ?" ብለው ጠይቀው ሰላምታ ተለዋወጥን ተሳሳምን:: ቁርስ እንዳልበላሁ ገምተው አስፈቅደው ቁርስ አመጡልኝ፣ በላሁ::



አብረውኝ ከመጡት አንደኛው ሲቪል የለበሰው «ጋሽ ደበበ! ሰዎች እስኪመጡ እየጠበቅን ነው፣ የመጣነው አንዳንድ የሚያስፈልጉንን ማስረጃዎች ፈትሸን ለመውሰድ ነው ለዚያም የፍርድ ቤት ትእዛዝ አለን» ብሎ አሳየኝ:: የፍርድ ቤት ትእዛዝስ ባይኖረው ምን እንዳልሆን ነው?

ተኩሱ እየበረከተ፣ ጩኸቱ እየናረ ነው:: አንድ አካባቢውን ለመቃኘት የወጣ አባላቸው ተመልሶ ሲመጣ፣ አንድ አውቶቡስ እንደተመታና መንገዱ ሁሉ በድንጋይ እንደተዘጋ ሲናገር ሰማሁት:: የሚመጡት ሰ-ዎች ምን ያህል ጊዜ እንደሚወስድባቸው ማወቅ አልተቻለም:: በየቦታው ሁኔታው ተመሳሳይ ነው:: በየቦታው መንገዱ ተዘግቷል በየቦታው ይተኮሳል:: በየቦታው ጩኸት ነው:: አሁንም የሚጠበቁት አልመጡም:: የምሳ ሰአት ደረሰ፤ ቤተሰቤ ሁላችንም ምሳ እንድንበላ ቢጋብዝም እኔ መብላት እንደምችል ነግረውኝ ወደ ቤት አስገቡኝ:: እነሱ ቤት ቢገቡም ምግብ ግን አንበላም አሉ:: የተቻለኝን ያህል ቤተሰቤም አቅሙ እስከፈቀደ ለመነ አሻፈረን አሉ:: ለኔ ምሳ ቀረበልኝ ቡናም ተጣደ:: ምሳ በልቼ ከጨረስኩ በኋላ ቡና ላይ የቡና ቁርስ ዳቦ ተቆርሶ ሲመጣ ሁላችንም የቡና ቁርስ ወሰድን:: ዳቦውን እምቢ አላሉም:: እንደባሕል ወጋችንማ ቢሆን ምሳውንም ቢበሉ የሚያስከፋ ነገር አልነበረውም:: ባህላችን ያልሆነ፤ከሕዝብ ጋር ምግብ በላህ ግምገማ መጥቶብን ነው እንጂ!!

ለፖሊሶቹ ችግሬን በማስረዳት ወደ መኪና ከመመለስ ቤት ውስጥ ምንጣፉ ላይ በጀርባዬ እንድተኛ አስፈቅጄ ፈቃድ ስላገኘሁ ጋቢ ለብሼ በጀርባዬ ተኛሁ:: ከቀኑ 9 ሰአት ተኩል ሲሆን የመንገዱ ሁኔታ በረድ ስላለ እየመጡ እንደሆነ ስልክ ደውለው ተናገሩ:: በፖሊሶቹ በኩል ሁለት ሃሳብ መጣ:: አንደኛው ልንጨርስ ስለማንችል ነገ እንምጣ ሲል፡ ከፊሉ ደግሞ "እንጨርሳለን፣ አሁኑኑ እንቀጥል፣ ነገ ሌላ ሥራ አለብን" ተባብለው ዛሬውኑ ፍተሻውን ሊጨርሱ ተስማሙ::

ቡናው እንዳከተመ፣ ይጠበቁ የነበሩት መጡና ተፈራርመው ብርበራውን ቀጠሉ:: የሚፈልጉት ለክሱ

ማጠናከርያ የሚሆን ማስረጃ ነው:: መጀመርያ ኮምፒውተሩን ጫኑ፤ ለጥቆ የቪዲዮ ክሮች ሲዲዎች የድምጽ ካሴቶች፤ የቅንጅት አርማ ያለባቸውም የሌለባቸውንም:: በየክፍሉ እየገቡ መሳቢያና ቁምሳጥን ውስጥ ያለውን ሁሉ በርብረው የሚፈልጉትን ይዘው ከማታው 12 ሰአት ሲሆን የሚያስፈልገኝን ልብስ እንድይዝ ፈቅደውልኝ ወደ ማእከላዊ ተመለስኩ:: ማእከላዊም የያዝኩት ተፈትሾ ወደ ተመደብኩበት ክፍሌ ገባሁ::

በማግስቱ ጠዋትም እንደተለመደው ለመጸዳዳት ውጣ ተብዬ ወጣሁ::ጣጣዬን ጨርሼ ወደክፍሌ ስመለስ የገባሁበት ክፍል ቀደም ሲል ሌሎች የከረሙበትና ጨርሶ ተጠርጎ የማያውቅ አይነት ስለነበር ተረኛውን ፖሊስ መጥረጊያ እንዲሰጠኝ ስጠየቀው፣ ቤተሰብ ስንቅ ካመጣ በኋላና ቁርስ ከበላሁ በኋላ ክፍሉን እንዳጥበው ፈቀደልኝ:: ያቺን ክፍል መጥረጊያ የሚባል ነገር ከነካት ዘመናት የተቆጠሩ ይመስለኛል::ሜዳው ላይ የፈሰሰው ነገር ሁሉ ጥላሸት መስሎ ደርቋል::አቧራውማ አይነሳ::ፖሊሱ እግዜርይስጠውና በባልዲ ውሃ ሰጥቶኝ መጥረጊያውን እያራስኩ አጠብኩት::ይሻላል::ያንን የማእከላዊ ፍራህ አውጥቼ ጸሐይላይ አሰጣሁት::ይህን አጠናቅቄ ትንህ አረፍ እንዳልኩ ሰአቱ ደርሶ ስንቅ መምጣት ጀመረና ወዲያው የኔ ስም ተጠራ የሚመለስ እቃ አምጣ ብለው የመጣልኝን ስንቅ ሰጡኝ:: እኔም ወደ ቤት የምልከውን ሰጠሁና የመጣውን ትኩስ ቁርስና ሻይ አስተናገድኩት፤ ብቻዬን:: ከቁርስ በኋላ የማጥራት አጠባ ለማድረግ ውሃ ከመታጠቢያ ቤት እንዳመላልስ ፈቃድ በማግኘቴ በማልፍበት አካባቢ እነማን እንዳሉ ለማወቅ ረድቶኛል::

ቆሻሻውን ሁሉ በአንድ ላይ አጠራቅሜ በፌስታል በማሰር መጣያው ታች ወደ ዋናው በር ስለነበር እዚያ ልደፋ ስሄድ ነው ከኔ ቀጥሎ ባለው ክፍል ውስጥ አቶ ገብረጻድቅና ኮሎኔል ታምሩ ጉልላት መኖራቸውን ያወቅሁት::የሹልክታ ሰላምታ ሰጠኋቸው:: ከነሱ ፊት ለፊት ስለሺ አንዳርጌ ጋዜጠኞችና አስቻለው ከተማ አሉ:: እነሱንም የሹሉክታ ሰላምታ ሰጥቼ አለፍኩ::

የባልዲው የሙከራ ምርምሬ ሰርቷል:: ባልዲው አንዳች ሽታ አልነበረውም:: ይህን ዘዴ ለሌሎችም



ነግሬያቸው ተጠቅመንበት ተሳክቷል:: በዚህች ክፍል ውስጥ አንድ ብቻዬን ለበርካታ ቀናት ነው ያሳለፍኩት:: ውጪ መውጣት የሚባል ነገር ስለሌለ በዚያው ክፍል ውስጥ ትንሽ ትንሽ እንቅስቃሴ አደርጋለሁ:: አንዳንድ ፖሊሶች የሚመክሩኝም ቁጭ አትበል እንቅስቃሴ አድርግ የሚል ነበር::ሌላው ጊዜ ማሳለፊያ እንደበፊቱ አሁንም በሻማ ሙቀት ትኋን ከግድግዳው ስንጣቂ ውስጥ በማስወጣት መግደል ነው::

ቀናት ካለፉ በኋላ አንድ ቀን ማታ በሬ ተከፈተ:: ምን እንደመጣ አላወቅሁምና ትንሽ ደነገጥኩ፤ወዲያው ከፖሊሱ ኋላ በሌላ ፖሊስ ታጅቦ አንድ ሰው ገባና በሩ ተቆለፈ:: የገባው ሰው ፖሊስ ይሁን እስረኛ ማወቅ አልቻልኩም በጣም ጭልጭል የሚል ብርሃን ነበር ያለው:: ሰውየው ወዳለሁበት ጠጋ አለና «ይቅርታ ጭለማ ስለሆነ መለየት አልቻልኩም ነበር፣ አቶ ደበበ ነህ እንዴ? ዳንኤል በቀለ እባላለሁ» አለኝ፤ «ፖሊስ ወይ የነሱ ሰላይ መስለኸኝ ነበር፣ አንተ ነህ እንዴ?» አልኩ:: ስለዳንኤል አንድ ጊዜ ደህንነቶች በደበደቡት ወቅት ሰምቻለሁ፣ መልኩንም በጋዜጣ ላይ አይቼዋለሁ እንጂ፣ ከዚህ ያለፈ ትውውቅ አልነበረንም:: ለነገሩ እሱና እኔ ሳናውቀው በአንድ አካባቢ በአንድ ሰሞን ነበር የሰደፍ ጉሽሚያ የደረሰብን::እሱም ቤተሰብ ሊጠይቅ አዲሱ ገበያ መጥቶ መኪና ውስጥ እንዳለ በሩ ላይ፤ እኔም ወደቤቴ ልገባ ስል ከሩፋኤል በታች ቤቴ በራፍ ላይ ነው አደጋው የደረሰብን::

ዳንኤል መሆኑን ካወቅሁ በኋላ መኝታውን ተረዳድተን አዘጋጀንና እራት በልተን ትንሽ ወሬ ያዝን::ዳንኤል ላለፉት ጥቂት ቀናት በፖሊስ ጣቢያ እንደከረመና ዛሬ ወደዚህ እንደተዛወረ ነግሮኝ እኔም በዚሁ በማእከላዊ መቆየቴን አጫውቼው ተኛን:: ዳንኤል ከነበረበት ፖሊስ ጣቢያ በብዙ መልኩ ይህ ቦታ የተሻለ እንደሆነ ነገሮኛል:: ፖሊስ ጣቢያ የቦታ ጥበት አለ፤የንጽህና ችግር አለ፤ የውሃ ችግር አለ::

ስለ ዳንኤል የሰማሁት የምርጫ ታዛቢ ሆኖ ይሰራ እንደነበርና በአክሽን ኤይድ ውስጥ ሃላፊ እንደሆነ ነው:: «ለመሆኑ ምን አደረግህ ነው የሚሉህ?» አልኩት::

እኔም በግልፅ አላወቅሁትም፣ ገና የክሱን ቻርጅ ሳይ ነው የማውቀው፤ አሁን ግን ከቅንጅት ጋር አብረሃል ለቅንጅት ወግነሃል ነው የሚሉኝ:: እኔ ግን ለማንም አልወገንኩም:: ወግኜም ከሆነ ለፍትሕ፣ ለነጻነት፣ ለሕዝብ፣ ለዴሞክራሲና ለሰብአዊ መብት መከበር ከሁሉም በፊት ግን ምርጫው ፍትሃዊና ነጻ እንዲሆን በተሰጠው መመሪያና የምርጫ ቦርድ ባወጣው መሰረት እንዲሄድ ለማድረግ ብቻ ነው:: ወገናዊነት ካሳየሁና ማሳየት ያለብኝም አስፈላጊ ሲሆን ለወከለኝ መስሪያ ቤት ለአክሽን ኤይድ እንጂ ለሌላ ለማንም ሊሆን አይችልም:: አክሽን ኤድ ደሞ ምርጫ ውስጥ የለበትም፣ ተወዳዳሪም አይደል፣ ፓርቲም አይደል፣ ይልቅስ ገንዘቡን አውጥቶ ለምርጫው በታዛቢነት የሚሳተፍ ነጻና ገለልተኝ ድርጅት ነው:: የሚገርመው እኔን ብቻ ሳይሆን ከኔ ጋር አብሮ ለተመሳሳይ ተግባር የቆመውንና አብሮኝ በተመሳሳይ መንገድ ሲታዘብ የነበረውን ጓደኛዬን የባለቤቴን ወንድም ነፃነትንም አስረውታል:: እሱም በግል ድርጅት ውስጥ የሚሰራ የሕግ ባለሙያ ነው የሚሰራበትም ለፍትሕ የቆመ አትራፊ ያልሆነ ድርጅት ነው:: ከሌሎች ታዛቢዎች ተለይተን ለምን ተጠያቂ እንደሆንን አልገባኝም::

ነጻነትም ባለፈው ምሽት መጥቶ ከፊት ለፊታችን አንድ ቁጥር ውስጥ ከእነ ስለሺ ጋር ተደባልቋል:: አላውቀውም ገና አላየሁትም፣ ምናልባት ነገ ጠዋት ወደ መጸዳጃ ስንሄድ እየው ይሆናል:: ዛሬ ጠዋት ግን ዳንኤል አይቶታል መግባቱንም በዚህ ነው ያረጋገጥነው:: ጠዋት የተለመደውን ካደረግን በኋላ የቤተሰብ መምጫ ስለደረሰ ተመላሽ እቃችንን አዘጋጅተን ስማችንን እናዳምጥ ጀመር:: ብዙም ሳይቆይ ስንቃችን መጣልንና አዳሪውን እቃ ይዘው ሄዱ:: ቁርስ በመብላት ላይ እንዳለን ፖሊሱ ዳንኤልን "ወደ ቢሮህና ቤትህ ስለምንሄድ ተዘጋጅ" አለው::

ዳንኤል አልገባውምና ከእኔ ቤት ብርበራ በመነሳት የሚሆነውን አስረዳሁት:: አንዳንድ ጊዜ ይደረጋል ሲባል የሰማሁትንና አሁንም በኛ ላይ ሊያደርጉት ይችላሉ ብዬ ያሰብኩትን፣ ማለትም በጥንቃቄ የየአንዳንዱን ሰው እንቅስቃሴ የሚከታተል ሰው እንዲኖር፤ ይህም ከውጭ መጥቶ ከሚጣልና



የማታውቀው ወንጀል መለጠፊያ እንዳትሆን ተጠንቀቅ አልኩት:: ዳንኤል ሰማኝ እንጂ ያመነኝ አልመሰለኝምና ላስረዳው ሞከርኩ:: በመጨረሻ ላይ ግን ለመግባባት በቅተናል::

ቀደም ሲል የመጣው ፖሊስ መጥቶ ዳንኤልን ይዞት ሲወጣ "በርታ፣ አይዞህ" ብየው ለጊዜው ተለያየን:: ዳንኤል ከወጣ በኋላ ብቻዬን ሆኜ ቡና እየጠጣሁ፣ ሲጋራዬን እያጨስኩ "እነዳንኤል ለምን ተከሰሱ?" የሚል ሃሳብ ውስጥ ገባሁ:: ቆይ እነዚህ ሰ-ዎች የቅንጅት አባላት አይደሉም፤ ገለልተኛ ከሆነ ድርጅት ነው ምርጫውን ለመታዘብ የመጡት፤ ቀደም ሲል ቅንጅት ባዘጋጀው ውይይት ላይ ተሳትፈው የቅንጅት ተመራጮች ወደ ፓርላማ እንዲገቡ ነው አጥብቀው የመከሩት ለታዛበዎች ሴሚናርና ስልጠና ሰጠተዋል፣ እና ለምን ታሰሩ? ጥላቻ ለምን አሳደሩባቸው?" ይህን ማወቅ ፈለግሁ:: አሁን ያለሁት እስር ቤት ስለሆነ ከቦታ ቦታ" ከሰው ሰው ተዘዋውሬና ጠይቄ ማጣራት አልችልም::ከዳንኤል ጋር መነጋገርና በግልጽ መወያየት አለብኝ አልኩ ለራሴ::

ይህን በዚህ ቋጨሁና ወደ መጽሐፍ ንባብ ገባሁ:: ከጥቂት ንባብ በኋላ ወደ ትኋን ገደላ ገብቼ ያም ሲደክመኝ ትንሽ ጋደም ልበል ብዬ ጀርባዬን አሳረፍኩ:: እንቅልፍ ወሰደኝ:: ተኝቼ ህልምም አይታየኝ፣ ቅዠትም አላጋጠመኝም:: ድንገት በሬ ተከፈተና አራት ጥቋቁር ልብስ የለበሱና ሁለት የሲቪል ልብስ የለበሱ እንግዶች ገቡ:: ባለጥቁር ልብሶቹ የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ባለስልጣናት ናቸው:: አንዱ ሲቪል መንግሥት ካቋቋመው የሰብአዊ መብት ድርጅት የመጡ ዶ/ር አምባሳደር ካሣ ገ/ሕይወት፣ ሌላው ደሞ ፓስተር ዳንኤል ናቸው::

ለምን እንደመጡ ጨርሶ አልገባኝም:: ሁሉም በተደጋጋሚ መንገድ ላይ ሰዎች በሰላማዊ መንገድ መብታችን ይከበር ባሉ በጥይት ሲቆሉ አንድም ቃል ያልወጣቸው፣ ዛሬ ለእስር ስለተዳረግን ቡራኬ ሊሰጡ መምጣታቸው በጣም የሚያስገርም ቀልድ ሆኖ ነው ያገኘሁት:: እንዴት አድርገው ነው እነዚህ ሰዎች ለሞተ ሳያዝኑ ለቆሰለ ሳይጸጸቱ፤ የተጣላን ለማስታረቅ ያልተንቀሳቀሱ፤ ሕዝብ መብቴን ባለ ሲገደል፣ ሲደበደብ

ከሕዝብ ጎን ያልቆሙ፤ አሁን ምን ሆን ብለው ነው እታሰርኩበት ድረስ የመጡት? ምናልባት ስለምገደል የመጨረሻ ፍላጎቴን ለማወቅ ይሆን? አይ ቀልድ?!

"ፋሺስት ኢጣልያ ኢትዮጵያን በወረረ ጊዜ የሮማው ጳጳስ ጦሩን "ሂድ ውረር፤ ግደል፤ አጥፋ" ብለው ባርከው እንደላኩት አይነት ነው? እያልኩ ትኩር ብዬ አይቻቸው እንደቆሙ ተመልሼ ተኛሁ:: አላሳለሙኝም፣ እኔም አልተሳለምኩም፤ ባለመሳለሜ የማጣው አንዳች ነገር የለምና:: ለፈጣሪ ጸሎቴንና ልመናዬን በነሱ በኩል ከምልክ እኔው በቀጥታ ብጠይቀው የበለጠ ይሰማኛል ብዬ አመንኩ:: እነሱም ወዲያው ወጥተው ወደሚቀጥለው ክፍል ሄዱ::

የእነዚህ ሰዎች መምጣት እስከአሁንም ያስገርመኛል:: ቀሳውስት በዓለም ላይ በተለያዩ ሃገራት ሕይወታቸውን ለፍትህ፣ ለነጻነት፣ ለሕዝብ መብት እንደሰጡ አልሰሙም ወይስ እነሱ የገዢው መንግሥት ደጋፊነታቸው በልጦባቸው ነው ሕዝብን ሃገርን ችላ ያሉት? እኔ ብቻ ሳልሆን አብዛኞቻችን ይህን ስሜት እንጋራለንና በአብዛኛው ቦታ ለቡራኬያቸው ምስጋና ሳይሆን ውግዘት እንደሚያጋጥማቸው እርግጠኛ ነኝ::

ያን እለት መጥተው ከክፊሌ ውስጥ ሲቆሙ አንድ ነገር ልላቸው አስቤ፣ ህሊናዬ "እምቢ" ብሎኝ ተውኩት ልላቸው ያሰብኩት «ሰማችሁ እናንተ! የፈጣሪ አገልጋዮች ያልሆናችሁ ለመንፈሳዊው ሳይሆን ለሥጋዊ፣ ለሰማያዊው ሳይሆን ለምድራዊው ጥቅም የቆማችሁ! እኔ ለናንተ አፈርኩ፤ እኔ ለናንተ ተሳቀቅሁ፤ እኔ ለናንተ ተሸማቀቅሁ:: ለመሆኑ አሁን እዚህ መምጣታችሁ ምን ለመጨመር ወይ ለመቀነስ ነው? ታውቃላችሁ ምን እንደሚሰማኝ? በናንተ ደካማነት ልቤ ፈጣሪን "ክዳው፣ ክዳው" አለኝ:: በናንተ ቸልታ ፈጣሪን "አውግዝ፣ አውግዝ" አለኝ:: በናንተ ግዴለሽነት ማተቤን "በጥስ በጥስ" አለኝ:: ሳልጠራችሁ ሳልፈልጋችሁ ሳልመጣባችሁ ከታሰርኩበት መጥታችሁ «በሠራ ሃጢአት እግዚአብሔር ይፍታህ» ልትሉኝና ያለሃጢአቴ ሃጢአተኛ በማድረግ ለአቃቤ ሕግ ምስክርነት ልትሰጡብኝ ነው? በሉ ወደ መጣችሁበት ሂዱልኝ አርፌ ልታሰርበት:: እናንተም ፈጣሪን አትለምኑልኝ



በናንተ ልመና ጽድቅና ምሕረት ሳይሆን መከራና ስቃይ ገነት መውረስ ሳይሆን ዘለዓለማዊ ነበልባል እሳት እንዳይመጣብኝ እሰጋለሁ ውጡ! ብዬ ላምባርቅባቸው ዳድቶኝ ጥቅሙ አልታይህ ስላለኝ ነው ተጠቅልዬ የተኛ ሁት::

በምሳ ሰአትም ዳኒ አልመጣምና እስኪመጣ ብዬ ወደ መጽሐፍ ንባቤ ገባሁ:: እንዲህ አይነት አጋጣሚ ሲመጣና ሳይታሰብ ሲያፋጥጥ ግራ ከማጋባትም አልፎ ያልተጠበቀ ድርጊትም ውስጥ ያስገባል:: ሁኔታቸው ሃሳቤን በታተነው:: ዝም ብሎ ደጋግሞ የሚመጣብኝ «ለምን መጡ? ለሞቱት ለተቀጠቀጡት አንድም ቃል ያልወጣቸው፤ የሃይማኖት አባቶች ነን የሚሉ፤ ምንም ይሁን ምን ሕይወታቸውና ልጆቻቸውን፣ እህት ወንድሞቻቸውን ላጡ ምንም ስሜታቸው ያልተነካ፤ ሌላው ሁሉ ቢቀር ፍጡራን ናቸውና በአምሳሉ የተፈጠሩ ሲሞቱ ምንም ለማለት ህሊናቸው ያልተነሳሱት እነዚህ ሰዎች አሁን ለምን? የሚሉት ጥያቄዎች መልስ ላላገኝላቸው በጠበጡኝ:: አላስነበብ አሉኝ::

ዝም ብዬ ተነስቼ የክፍሌን በር አንኳኳሁና ፖሊሱ ሲመጣ እባክህ መጥረጊያ አቀብለኝ፣ ቤቱን ልጥረገው ብየው መጥረጊያ አመጣልኝና ዝም ብዬ ቤቱን መጥረግ ያዝኩ:: ወለሉን ግድግዳውን ጣራውን ሁሉንም በመጥረጊያ ጠረግሁት:: ልክ እነዚያን ድንገት የመጡትን ሰዎች ጠርጌ ያስወጣኋቸው ያህል ተሰማኝ:: ታዲያ ሳላውቀው ደከመኝ፤ ላብ ይዞኛል:: መጥረጊያውን ጥግ አስደግፌ ፍራሼ ላይ ተዘረርኩና እንቅልፍ ወሰደኝ::

መሽቷል፤ አሁንም ዳኒ አልመጣም:: ደሞ አልራበኝም:: ቁጭ ብዬ ከመጽሀፍ ይልቅ አንድ አሮጌ ጋዜጣ አንስቼ ማንበብ ያዝኩ:: ምን እንዳነበብኩ ትዝ አይለኝም፣ ዝም ብዬ ነው የማነበው:: ከጥቂት ጊዜ በኋላ በሩ ተከፈተና ዳኒ ገባ:: የተዳከመ የተራብ ይመስላል:: ሰላምታ ከተለዋወጥን በኋላ ውሎው እንዴት እንደነበረ ነገረኝ:: ችግር እንዳልነበረ የሚገምት መሆኑን፣ በተለይ በመኖሪያ ቤቱ በሄዱበት ጊዜ ብቻውን እንደነበርና ሊከታተል የሚችል ሰው አለመኖሩን፣ ግን የፈረመባቸው ወረቀቶች ምንም

ተንኮል ያልነበረባቸው መሆኑን ነገረኝ:: ቢሮ ደህና ነበር:: የቢሮው ሰዎች ሁሉ ስለነበሩ ይጠባበቁ ነበር አለኝ::

እራት እየበላን ስለመጡት ያልተጋበዙ እንግዶች ነገርኩት:: ከመሃላቸው ፓስተር ዳንኤልን እንደሚያውቀው ነገረኝ:: የሌሎቹን ስም ስለማላውቀው እገሌ ማለት አልቻልኩም:: «ምን ፈለጉ?» ነበር የሱም ጥያቄ:: አይ እኔ ለማናገርም ፈቃደኛ አለመሆኔን ተመልሼ በመተኛት ነው ያሳየሁት ብዬው ወደ እራታችን ዞርን:: ሁለታችንም ተርበን ኖሯል:: እራት በልተን፣ ቡና እየጠጣን ዳንኤልን ለምን እነሱ ተለይተው ለእስር እንደበቁ የሚጠረጥረው ነገር ካለ ጠየቅሁት:: ዳንኤል «እንዲህ ነው ምክንያቱ ይሄ ነው ማለት ያስቸግረኛል:: እኔ ሊሆን ይችላል ከማለት ውጪ እውነቱ የት እንዳለ አላውቅም፤ ደሞ ከሽመልስ ጋር እኮ በሚገባ እንተዋወቃለን:: በብዙ ጉዳዮች ላይ ቁጭ ብለን የምንወያይ ነበርን:: እንግሊዝ ሃገር ትምህርት ላይ ባለሁበት ወቅት እንኳን መጥቶ ደውሎልኝ ተገናኝተን ተነጋግረን ነበር፤ እርግጥ በዚያን ጊዜ በተነሳው ነጥብ ላይ ልዩነት ነበረን ያ ግን ለዚህ ያደርሰኛል፣ ያስከስሰኛል አልልም:: ምክንያቱም ያን ጊዜ ያደረግነው የምሁር ምክክር እንጂ ፖለቲካዊ አልነበረም» ነው ያለኝ::

ከዚህ ያለፈ ነገረኝ ማለት አልፈልግሁም፣ ልክም አልመሰለኝምና እዚሁ ላይ ተውኩት:: አንድ ቀን እንዲሁ የመጣልኝን ነገር ለዳኒ አነሳሁበት «ለመሆኑ ለንደን ተገናኝታችሁ ከተነጋገራችሁ በኋላ አልተገናኛችሁም? ማለት ለንደንም ሃገር ውስጥም?» አልኩት «አይ ተገናኝተናል ግን ግንኙነታችን እንደቀድሞው አልነበረም ቀዝቀዝ ያለ ነበር በሱ በኩል» ሲለኝ «ለምን ይመስልሃል አልኩት» "ምንነቱንማ ከሱ በስተቀር ማን ያውቃል በኔ በኩል አንዳችም ቅሬታ የለኝም» ነው የዳኒ መልስ:: «ለመሆኑ ለንደን ስለምን ነበር ንግግራችሁ? መነሳት የሌለበት ጉዳይ ከሆነ ተወው» ስለው «አይ ችግር የለውም፤ ያን ጊዜ የተነጋገርነው ሲሰራበት በነበረው ፕሬስ አዋጅ ላይ ነበር:: የሰራውን ሰጥቶኝ ካነበብኩት በኋላ በርካታ ነጥቦችን አንስቼ ቀድሞ ከነበረው አዋጅ የባሰ አሳሪ እንደሆነና ለሃገራችን የማይጠቅመው ወጥቶ ጠቃሚ በሆነው መተካት



እንዳለበት ነበር ውይይታችን:: የዴሞክራሲ ሥርአት ለመገንባት ይሄኛው የሚያስኬድ አለመሆኑን በግልጽ ተነጋገርን:: ይህ ምናልባት ቅሬታ ፈጥሮ ከሆነ ያን ጊዜም፣ ዛሬም፣ ወደፊትም የማምንበት በመሆኑ ምንም የሚያጸጽተኝ አይደለም:: ይሄም ቢሆን በግሉ ጠይቶኝ በግለሰብ ደረጃ የሰጠሁት አስተያየት ነው:: ከተመቸው መቀበል ካልተመቸው መተው ነው እንጂ የሚያጣላ ሊሆን አይችልም» አለኝ:: እውነቱን ነው ይህ ሊያስከስስ አይችልም፤ምናልባት ያንን የመጋፋት፤አታውቅም እንደማለት፤ ለዴሞክራሲ ግንባታ አልቆምክም የሚል ትርጉም ከመስጠት ካልሆነ በስተቀር::

ሁለታችን ብቻ እንዲሁ አንድ ክፍል ይዘን ከቆየን በኋላ የቅንጅት ቢሮ ሠራተኛ የሆነው የመቶ ዓለቃ ዓለማየሁ የኔነህ አንድ ማታ በፖሊስ አጃቢነት መጥቶ ክፍላችን ገባ:: ክፍሉ ጨለም ያለ በመሆኑ ከውጭ የመጣ ሰው፤ ውስጥ ያለነውን መለየት ያስቸግረዋል:: ዓለማየሁ እንደገባ ክፍሉ መሃል ላይ ቆሞ እነማን እንደሆንን ለማየት እየሞከረ ነው::ትንሽ መደናገጥ ይታይበታል:: ዓለማየሁ ሰዎች በሚያዙበት ወቅት ተደብቆ ከርሞ በኋላ ቤተሰቡ ላይ በደረሰ ችግር እጁን ሰጥቶ ለቤተሰቡ ሰላም ይሰጣል በሚል ወደ ማእከላዊ መጥቶ ለመታሰር የፈቀደ ነው:: ወዲያው እኔን ለየኝ «ምነው ጋሽ ደቤ፣ እኔ ነኝ ብትለኝ?» ብሎ አጠገቤ ቀርቦ ከተሳሳምን በኋላ ዳንኤል ጋር አስተዋወቅሁት:: «ተመስጌን» አለ ዓለማየሁ:: ወዲያው እራት አቀረብንለትና ከበላና ቡና ከጠጣ በኋላ ሁኔታውን አጫወተን:: «ውጪ በነበረበት ጊዜ በየቀኑ ቦታ ይለዋውጥ እንደነበርና ያድርባቸው የነበሩ ሰዎችን ችግር ውስጥ እንደከተተ፣ እነሱ ግን ደንታ እንዳልነበራቸው፤ ከውጪው ኑሮ መታሰሩ የተሻለ እንደሆነና ከመገላመጥና በር በተከፈተ ቁጥር ከመሳቀቅ መታሰሩ ይሻላል» አለን:: እንደመጣ እግቢው ውስጥ አቆይተው እቃውን ተረክበው ወደ ክፍል አመጡት እንጂ፣ ቃሉን እንዳልተቀበሉት፤ ለቤተሰቡ ወዲህ ሲመጣ እንዳስታወቃቸው፤ ተጨዋውተን አነጣጥፎ ተኛ ን::

ዓለማየሁ በደሴም ክስ ተመስርቶበት በዚያ የተነሳ እዚያ በመመላለስ ቀጠሮ ላይ ያለ ሰው

ነው።አሁን ደሞ በተመሳሳይ እዚህ ሊከሰስ ማእከላዊ ገብቷል።ምናልባትም ለብዙ ጊዜ ከታሰረ በኋላ በሌላ ቦታ የተከሰሰ ስለሆነ ክሱን እዚያው ይጨርስ ሊባልም ይችላል፤ እስከዚያው ግን ተወደደም ተጠላም ማእከላዊ ገብቷል።

ዓለማየሁ ከመጣ ከጥቂት ቀናት በኋላ ሀዳር ማለቂያ ላይ በቀን 20 ደቂቃ ፀሐይ መሞቅ ውጪ ወጥቶ ፀሀይ ላይ እንድንቀመጥ ተፈቀደልን። ትልቅ ደስታ ተፈጠረ፤ በአካባቢያችን መተያየትም ቻልን። ትንሽ ቆይቶ ደሞ የክፍላችን በር መዘጋት ቀረና ክፍቱን ይውል ጀመር። ያም ሆኖ ከሚፈቀደው 20 ደቂቃ ውጭ ከቤት መውጣት አይቻልም። ግን ለመጸዳጃ ቤት፣ ገላ ለመታጠብ፣ ቆሻሻ ለማፍሰስ፣ ልብስ ለማጠብ መውጣት ይቻላል። በዚህ ሰበብ እየተገናኘን መነጋገር፣ ሃሳብ መለዋወጥ፣ በየግል የሰማነውን መነጋገር ጀመርን። ቁጥጥሩ ብዙም አይደለም፣ እየተለማመድን ሄድን መሰለኝ ከበፊቱ የተሻለ እየሆነ ነው። አንዳንዶቹ እንዲያውም ከኛ ጋር ተዝናንተው ያወሩ፣ የምንፈልገውን እቃ ይገዙልን ጀመር። ምናልባት እሺ ቢሉን ብለን የመጫወቻ ካርታ እንዲገዙልን ስንጠይቅ ገዙልን። ማምሻ ተገኘ። መጽሐፍ ማንበብ ሲደክመን ለለውጥ ካርታ መልካም ነው።

እዚያ ካለው አንደኛው ክፍል ጨርሶ አይከፈትም። ወደመጸዳጃ ስናልፍ ብቻ የድምጽ ሰላምታ እንለዋወጣለን።አንድ ቀን አንዲት ወረቀት በውርወራ ላኩልን። ወረቀቱ ማንነታቸውን የሚገልጽና በሙስና ስም ሩዋንዳ ከዘመተው ገንዘብ ጋር በተያያዘ የታሰሩ መሆናቸውን የሚገልጽ ስለነበር ያ ወረቀት ወጣና በጋዜጣ ላይ ታተመ። በዚህም የተነሳ ሰዎቹን በጨለማ ካሉበት ቦታ አውጥተው ወደ ሌላ ወሰዷቸው። ከነበሩበት ቦታ ድምጻቸው ሲጠፋ ጉዳዩን የምናውቀው በጣም ተደናግጥን ይዛወሩ፣ ይገደሉ ማወቅ ባለመቻላችን በጣም አዘንን። ለማጣራት ሞክረን በሕይወት መኖራቸውን ብቻ ማወቅ ቻልን።

በሮቻችን ክፍት እንዲውሉ ከተፈቀደ ከሳምንት በኋላ መለዋወጥና መደማመር ተጀመረና ኢንጅነር ኃይሉ ሻውልና አቶ አሥራት ጣሴን፤ ከኛ ወደታች ያለው አቶ ገብረጻድቅ ክፍል፤ ዓለማየሁን ከኛ ወደሌላ



ክፍል ወሰዱትና፤ ዶ/ር ታዬምስን፤ አቶ አሰፋን፤ አቶ አንተነህን፤ አቶ በድሩን ወደኛ ክፍል አመጧቸውና ቁጥራችን ከሶስት ወደ ስድስት ከፍ አለ። ሙሉ ቀን ውጪ እንደልባችን መዋልም ቻልን።

አሁን እንደልብ መገናኘት፣ አብረን መጫወት ከክፍል ክፍል ሄደን ማውራት፣ መቻላችን ሁኔታውን የበለጠ አመቺ አደረገው። ቀን ቀን ተሰባስበን በማውራትና በመወያየት አመሻሽ ላይ ደግሞ ሬዲዮ በማዳመጥ፣ ወደየክፍላችንም ከገባን በኋላ የሬዲዮ ፕሮግራም ካለ ያንን ማዳመጥ፣ ከሌለም ሰአቱ እስኪደርስ ካርታ መጫወት እራት መብላት ከዚያ በሕብረት ጨዋታም ውይይትም ማድረግና መተኛት ሆነ።

አንድ ቀን እንዲሁ እያወራን ሳለ ዳንኤል የተሻለ ሃሳብ አመጣ። "ለምን በሕይወታችን ያሳለፍነውን ወቅት በመነጋገር አንዳችን ስለአንዳችን እንድናውቅ አናደርግም?" አለ። ጥሩ ሃሳብ በመሆኑ ሁላችንም ያለችንን ትናንሽ ታሪክ በማውራት፣ አንድ ሰው አንድ ቀን ቢይዝ ከነትረካውና ጥያቄና መልሱ ስድስት ቀናት ያልፋል በሚል፣ በበነገታው በዳንኤል እንዲጀመርና በየተራ እንድንቀጥል ተስማማን። በዚህ ማታውን፣ ቀኑንም ከሌሎች ጋር በምናደርገው ግንኙነት፣ ካርታ ጨዋታ ጋዜጣም ከተገኘ ማንበብና በሌላም ሌላም ማሰለፉን ቀጠልን

በማእከላዊ በጣም የተለያዩ ሰዎች በየጠዋቱ ለቀን ውሎ ያጋጥሙናል። አንዳንዶቹ እንኳን ማናገር ሲያዩንም ደማቸው ይንተከተካል፤አንዳንዶቹ ለማናገር እየፈለጉ ግን ግምገማቸውን በመፍራት በጥቅሻ ብቻ ነው ማንኛውም ነገር የሚያልቀው። አንዳንዶቹ ግን ወኔው ያላቸውና ለግምገማም በቂ መልስ አለን ብለው የሚያምኑት በስርአትና በወጉ ያነጋግሩናል። ማእከላዊ የገባነውም የታሰርነውም አለምንም በቂ ምክንያት ቅንጅት በማሸነፉና ብርቱካን እንዳለችው "መንፈሱ" ሃገሩን ስላዳረሰው እንጂ፣ ለዚህ የሚያበቃ አንዳችም ወንጀል አልፈጸምንም። "የመውጫችን ጊዜ ብዙ አይዘገይም" የሚል እምነት ነበረኝ። ቀኑን ቀን እየወለደው አንዳችም ምርመራ ወይ ቃል መቀበል ሳይካሄድ፣ ከወር በላይ ቆየን። ምርመራው ሲጀመርም

በቀን ከሁለት ሰው በላይ አያስተናግዱም ነበር:: "ህጋዊ የሚመስል ህገወጥ ድርጊት" ብየዋለሁ::

ያም ሆነ ይህ፤ቀኑ ቀንን እየወለደ ጥቂት ነው ተብሎ የታሰበው እየጨመረ፣ ወር አልፎ ሁለተኛው ተገባዶ በዝነኛው የጊዜ ቀጠሮ እለት ወደ ፍርድ ቤት ሄድን::

ማእከላዊ ከገባን እለት ጀምሮ በቦታው ሁኔታና በተለያየ ምክንያት ህክምና ለሚያስፈልገን ሰዎች ያገኘ ነው ነገር ቢኖር እዚያው ባሉ የመጀመሪያ ደረጃ ህክምና መገልገል ብቻ ነበር:: በዚህ ህክምና የሚገኘው የማስታገሻ፤ የራስ ምታት፤ የአይን ጠብታ እንጂ ሌላ ከዚህ ለዘለለ በሽታ የሚገኝ እርዳታ የለም:: በተደጋጋሚ የጤንነት ችግር እንዳለብኝ ብናገርና ህክምና ብጠይቅም የማግኘቱ ነገር ከንቱ ልፋት ሆነ::

ከስንት ጥያቄና ማስረዳት በኋላ፣ እንደምንም ወደ ፖሊስ ሆስፒታል የመሄድ እድል አገኘሁና በቀጠሮ ሄድኩ::ፖሊስ ሆስፒታል ስደርስ በሆስፒታል ያሉት ሠራተኞችም፣ ሊታከሙ የመጡትም፣ ጥበቃ ላይ ያሉትም፣ ሃኪሞቹም፣ ነርሶቹም ሁሉም መግለጽ በሚያስቸግር መልኩ ያላቸውን ፍቅር ፊራ ተባ እያሉ አሳዩኝ:: የቅድሚያ ምርመራ በሚደረግበት በካርድ ማውጫው በሄድኩበት ቦታ ሁሉ ቅድሚያ እየሰጡኝ ያላቸውን አክብሮትና ፍቅር አሳይተውኝ ተጨማሪ ብርታት ሆነኝ::

በቅድሚያ ተመላላሾች ወደሚታዩበት ሃኪም ዶ/ር ግርማ ዘንድ ቀርቤ አስፈላጊው ምርመራ ከተደረገልኝ በኋላ ለቀዶ ጥገና ለሳምንት ቀጠሮ ተሰጠኝና ወደ ማእከላዊ ተመለስኩ:: ከዚያ በኋላ ግን በቀጠሮዬ ተመልሼ ለመሄድ በፍጹም አስቸጋሪ ሆነ:: በየቀኑ ሰበብ እየተፈጠረ ቀጠሮዬ ሁሉ ይተላለፋል:: "ለምን?" ብዬ ስጠይቅ "ከሆስፒታል ተደውሎ ነው" ይባላል:: እኔ ደሞ ባለኝ መንገድ ሳጣራ ሀኪም ቤቱ አልወጣውም::

ጉዳዩን በዚያ ላሉት የጤና ረዳቶች ባስረዳም "አሁን ለጊዜው ለስኳርና ለደም ብዛት ብቻ ቅድሚያ ስጡ ተብለናል፣ ያንተንም ስም አብረን እያስመዘገብን ነው:: ችግርህንም ለበላይ ነግረን እየጠበቅን ነው" ተባልኩ:: ኽርኒያ ይዞኛል፣ እብጠቱ እየጨመረ ነው::



የቆየው በሽታዬም ውጪ እያለሁ አስፈላጊውን ክትትል ሳደርግበት የነበረው፣ አሁን እያስቸገረኝ ነው:: በተደጋጋሚ ለሚመለከታቸው ሁሉ አቤት ብልም ምንም መፍትሔ ሳላገኘሁምና በቀጠሮው ዕለት ለፍርድ ቤቱ አቤት ብል እንደሚሻል ተረዳሁ::

ዛሬ የጊዜ ቀጠሮ ደርሶ ፍርድ ቤት የምንሄድበት ቀን ነው:: ለአቤቱታ ተዘጋጅቻለሁ:: ዛሬም የዋስ መብት እንዲፈቀድልን ለመጠየቅ ተዘጋጅተናል:: አቃቤ ህግ መቼም ያው እንደተለመደው ገና ያልተፈረደብንን ሰዎች "የለየላቸው ወንጀለኞች፣ አድመኞች፣ የሃገር ጠላቶች" እያለ ያልሆነውን ወይም በፍርድ ቤቱ ያልተወሰነ ስም እየሰጠን እንዳሻው ሲፈነጭብን ሃይ የሚል አልነበረም::

ሰአቱ የፍርድ ቤቱ መሰየሚያ ሳይሆን የኛ ወደ ፍርድ ቤት መሄጃና እንደተለመደው ብርድ ላይ መኪና ውስጥ መቀመጫ ደረሰና ከየክፍላችን በየተራ እየወጣን ወደ የተመደበልን መኪና ገባን:: በጣም የሚገርመው መኪና ውስጥ አታውሩ የሚለው ትእዛዝ ነው:: ሰው እንዴት እየተዋወቀ ያውም በአንድ አይነት ክስ ተመስርቶበት ጎን ለጎን በአንድ መኪና ውስጥ ተቀምጦ አትነጋገሩ ይባላል? እንዴትስ ይህን ማድረግ ይቻላል? ይህን በማድረጋችን የመጣውን ለመቀበል መነጋገራችንን ቀጠልን:: ዝም በሉ ያለንም አጃቢያችን የሚያደርገው ስላጣ እየተመናጨቀ «ምናለ ብንከባበር? ለምን ስርአት አይኖርም» እያለ የሚናገረው ለኛ ቢሆንም ግን ፊቱን አዙሮ ነው የሚያጉረመርመው::

እሱም እያጉረመረመ፣ እኛም በዛሬው ቀጠሮ ምን ሊሆን እንደሚችል እያወራን ፍርድ ቤት ደረስን:: ዳኞችም አቃቢያን ህጎችም ስላልመጡ መኪና ውስጥ እንጠብቃለን:: ቤተሰብም ቀድሞ መጥቶ እየተፈተሸ ይገባል:: ታዛቢዎችና ጋዜጠኞችም እየገቡ ናቸው:: አንዳንድ የውጭ ጋዜጠኞች እኛን ፎቶግራፍ ለማንሳት ቢፈልጉም አልተፈቀደላቸውም:: አንዳንዶቹ ስንወጣ ጠብቀው ለማንሳት በግቢው ውስጥ ይንቆራጠጣሉ:: ፖሊሶች ደሞ ስለገባቸው ወደ ውስጥ እንዲገቡ ያዛሉ:: ይህ ደሞ ባለፉትም የፍርድ ቤት ቀጠሮዎች ያየነው ነውና አልገረመንም::

ድንገት ቤተሰብ ራቅ ብሎ እንዲጠብቅ፣ የኛም አጃቢዎች ፖሊሶችን ካሰማሩ በኋላ ወደ የመኪናው

እየመጡ እንድንወርድና ወደ ውስጥ እንድንገባ አዘዙ:: ወጥተን መንገድ ጀመርን:: አንዳንድ በዘዴ ወደ ውስጥ ያልገቡ የውጭ ጋዜጠኞች እየተሯሯጡ መጥተው ፎቶግራፍ ማንሳት ሲጀምሩ፣ እኛም ያንን ፖሊስም፣ መንግሥትም የማይወደውን የጣት ምልክት እያወጣን ስንነሳ ፖሊሶቹ ጋዜጠኞቹን በመመለስ እንድንገባ አደረጉ:: ወደ አዳራሹ ስንገባ ቤተሰቦች ቆመው ይጠብቃሉ፤ ተገቢውን ሰላምታ ከሰጠን በኋላ በየቦታችን ተቀመጥን:: ከቤተሰብ ጋር በምልክት እንነጋገራለን፤ ፖሊስ ያንንም ይከለክላል:: ለኛ ጥብቅና ለመቆም የወሰኑ ከመቶ በላይ ጠበቆች በፈቃደኝነት የተሰለፉ ቢሆንም ዛሬ ግን ከቦታውም ጥበት፣ ከጉዳዩም ገና አለመጀመር የመጡት ከ15 በላይ የሚሆኑ ጠበቆች ናቸው:: ሁላችንም ስንጠብቅ ዳኞች ገብተው ተሰየሙ፤ አቃቢያነ ህጎች የሉም:: በነሱ አለመምጣት ሊቀጠር ነው ብለን ስናስብ መጡ::

በጣም የሚገርመው ነገር እንደ ወጉ ቀድመው መግባት የነበረባቸው አቃቢያነ ህጎች ሆኖ ሳለ፣ የተገላቢጦሽ ዳኞች ከተሰየሙ በኋላ ገቡ:: ዳኛው ሊገስጹና ማሳሰቢያ ሊሰጡ ሲገባ ምንም አላሉም:: አቃቤዎችም «ጌታዋን የተማመነች በግ ላቷን ውጪ ታሳድራለች» ነውና ይቅርታ ቀርቶ ትንሽ የይሉኝታ ነገር እንኳን ሳያሳዩ ምንም ስህተት እንዳልተፈጸመ ገብተው ተቀመጡ:: የከሳሽ ተከሳሽ መምጣት ከተረጋገጠ በኋላ እኔ እጄን አወጣሁ:: «ምንድን ነው?» አሉ ዳኛው አቶ አዲል አህመድ:: እኔም በህክምና በኩል ስለአለብኝ ችግርና ሃኪም ቤትም ለመሄድ አለመቻሌን አቤት አልኩ::«ክቡር ፍርድ ቤት ታምሜ ሃኪምም ቀጠሮ ሰጥቶኝ ያ ሊከበርልኝ ባለመቻሉ በበሽታው በመሰቃየት ላይ ነኝ::ለፍርዱም ቢሆን ጤናማ ካልሆንኩ የሚወሰንብኝን መፈጸም ያስቸግር የለም እንዴ እና ይታዘዝልኝ» አልኩ:: ዳኛውም የህክምና መብቴ እንዲከበርና በአስቸኳይ እንድታከም፣ እስካሁንም የተከለከለበት ምክንያት እንዲገለጽ አዘዙ::

ወዲያው የፍርድ ሂደቱ ቀጠለና አቃቤ ሕግ ማስረጃውን አሰባስቦ የጨረሰ በመሆኑ ቀጠሮ እንዲሰጥና የክሱን ሰነድ እንዲያቀርብ፣ ይህም ከክሱ ውስብስብነት የተነሳ ጊዜ ስለሚፈጅ ይህ ታሳቢ ሆኖ እንዲቀጠርለት



ጠየቀ ፍርድ ቤቱም በዚሁ ላይ ቀጠሮ ሊሰጥ ሲል ከኛ ጠበቆች መሃል የዋስ መብት እንዲታይልን ጥያቄ አቀረቡ:: ገና ዳኛው ሳይናገሩ፣ የኛም ጠበቃ ተናግረው ሳይጨርሱ፣ አቃቤ ሕግ እንደጥይት ከተቀመጠበት ተተኩሶ በመነሳት ተቃውሞውን አቀረበ:: አቃቤ ህግ ይህን ሲያቀርብ ለኛ የዋስ መብት ቢሰጥና በዋስ ብንወጣ ዓለም የሚያልፍ ሃገር የሚጠፋ አስመስሎ ነው ያቀረበው::

## ወደ ቃሊቲ

በዚህም የእለቱ «የፍርድ ሂደት» ተጠናቆ ከፍርድ ቤቱ ወጥተን ወደ መኪናችን ስንገባ የኢቲቪ ካሜራ አነጣጥሮ ሲጠብቅ ካሜራውም አንሺውም የማይወዱትን፣ ለቴሌቪዥን ጣቢያውም የማይስማማውን ያንን ዝነኛ የምርጫ ጣታችንን ስናወጣበት ካሜራው ታጠፈ:: ሌሎች በአብዛኛው የውጭ ጋዜጠኞች ግን ያንኑ በደስታ ያነሱት ነበር::

ሕክምናና መኖ ወደሚገኝበት ወደ ቃሊቲ የምንሄድበት ዕለት ተወስኖ ስለነበር ወደ ፍርድ ቤት ስንሄድ ማእከላዊን ተሰናብተን፣ ኮተታችንን ጭነን ነበርና የፍርድ ቤቱ ሥርአት እንዳለቀ ክሱን በንባብ ሰምተን ጥፋተኛ ነሽ/ነህ አይደለሁምን ለመመለስ ቀጠሮ ተሰጥቶን ወደ ቃሊቲ ወረድን::

በጣም የሚገርመው ከማእከላዊ እቃችንን ይዘን እንድንወጣ ሲያደርጉን ወዴት እንደሚወስዱን በግልጽ ያውቁታል:: እኛ ደግሞ ቤተሰቦቻችችን የሚባለውን ለመስማት ፍርድ ቤት ስለነበሩ በበነጋው ስንቅ ሊያመጡልን እንዲችሉ ወዴት እንደምንዛወር እንዲነግሩን ብንጠይቅ፣ የምናገኘው ተደጋጋሚ መልስ "መኖና ሕክምና ወደሚገኝበት" የሚል ብቻ ሆነ::የት ነው ይሄ መኖና ህክምና የሚገኝበት ሚስጥር የሆነ ቦታ? እነሱ ሚስጥር አድርገው የያዙት መሆኑንና ይህ ደግሞ ለቤተሰብ ስንቅ ማቅረብ ስለሚቸግር ለፍርድ ቤቱ እንዲነገረን ብንጠይቅም፣ ለፍርድ ቤቱ የተሰጠውም መልስ "ካሉት ማረሚያ ቤቶች ቦታ ያለበት ነው የምንወስዳቸው:: ለዚያ ደግሞ ከሁሉም መልስ እየጠበቅን ነው" ተባለና በዚሁ ተዘግቶ፣ የፍርድ ቤቱም ስነስርአት ተጠናቆ፣ ወደየመኪናችን ገብተን በሚስጥር ወደተያዘው ቦታ ተንቀሳቀስን::

ወዲያው ባደረግነው ግንኙነት ለቤተሰብ የገባንበት ቦታ የሚነገርበት መንገድ ተቀናጀ። በየጉራንጉሩ አቆራርጠን፣ በቦሌ ቀለበት መንገድ ገብተን ቃሊቲ ሆነ የመኖና ሕክምና መገኛው። የማእከላዊ አጋቾቻችን ለቃሊቲ አሳሪዎቻችን እንደእቃ ቆጥረው አስረከቡን። ቃሊቲን የማውቀው ድሮ ወደ ናዝሬት ስንወርድ በሚሸተው የምግብ ጠረንና፤በምግብ ፋብሪካነቱ ስለነበር መኖ በዚህ ቦታ ለመገኘቱ ጥርጣሬ አልነበረም። በፍርድ ቤቱም ዳኞች በፖሊስም ሲነገር የነበረው «መኖ» እየተባለ ስለነበር ምናልባት የከብት ምግብ ይሆን እያልኩ ሳላስብ አልቀረሁም።

እኛም እቃቻችንም ከመጣንበት መኪና ላይ ካወረድን በኋላ ተረካቢና አስረካቢ በስም ዝርዝራችን መሰረት ተረካክበውን አስረካቢዎች ለተረካቢዎች ሰጥተውን ሄዱ። በስም እየተጠራን ተለየን። ጋዜጠኞች ለብቻ ተወሰዱ። ሴቶች የቅንጅት አባላት ወደሴቶች ክፍል፣ ሌሎች የቅንጅት አባላትና ደጋፊዎች፤ እና የሲቪክ ማሕበራት አባላት በአንድነት ከቀይ ሽብር ተፋራጆች ጋር ተቀላቀልን። ምሽት እየተጠጋ ነበርና በፍጥነት እንደገና ስም እየተጠራ ወደየተመደብንበት ክፍል እቃችንን እንድናስገባ ተነግሮን እንደታዘዝነው አደረግን። ሁሉም የቀይ ሽብር ተፋራጆች ናቸው። የደርግ አባላት፤ የደህንነት ሠራተኞች፤ የዓየር ሓይል አባላት፤ ካድሬዎች፤ አስተዳዳሪዎች፤ የኢሕአፓ አባላት እና ሌሎቹም አሉ።

እኔ የደረሰኝ በአብዛኛው ካድሬዎች የነበሩ፤ አንዳንድ የቀበሌ አባላት፤ የአብዮት ጥበቃ አባላት ያሉበት ክፍል ነው። ከእኔም ጋር አቶ በድሩ አደምን ኮሎኔል ታምሩንና የመምህራን ማሕበሩን ካሳሁንን የክፍሉ ሃላፊ ተረክቦን አልጋችንን ሰጠን። ሶስታችንም የቆጥ (የላይኛው ) አልጋ ነው የደረሰን። በክፍሉ ውስጥ ያሉት አልጋዎች በሙሉ ተደራራቢ ናቸው።የታችኛው አልጋ ሁሉም ተይዟል፤ ሲለቀቅም የሚሰጠው ቀደምት ለሆነ ወይም የጤና ችግር ላለበት ነው።

ከኔ ስር የሚተኛው የሰሜን ተወላጅ በመቀሌ አካባቢ ካድሬና የአብዮት ጠባቂ ሹም ሆኖ ይሠራ የነበረ ነው።አልጋውን ሊለቅልኝ ሃሳብ ቢኖረውም ከፍተኛ የአስም በሽታ ያለበት በመሆኑ ሃሳቡን



አልተቀበልኩትም። አብዛኛው ሰው የታችኛውን አልጋ ለመስጠት ፈቃደኛ ነበር፤ለእኔ ደሞ ከቆይታቸውም፣ ከጤናቸውም፣ ከእድሜም አኳያ ፈጽሞ ፈቃደኛ አልሆንኩምና ምደባው ጸና።

ማታውን ከመቆጠራችን በፊት እራት ከማእከላዊ ይዘን የመጣነውን በልተን ለማታው ቆጠራ ወደየክፍላችን ተሰባሰብን። ከብዙዎቹ ጋር አልተገናኘ ንም። እራት በልተን ቆጠራ ስንጠብቅ አንዳንዶች ቀድሞ የሚያውቁንና የምናውቃቸው ቀረብ እያሉን ከእስረኛው መሃል አንዳንድ ወሬ አቀባዮች እንዳሉና መጠንቀቅ እንዳለብን አሳሰቡን። ዋነኛው ጉዳይ የምናወራውን ማወቅና ሚስጥራችንን መያዝ መቻል ነው። በቴሌቪዥን ስአት አስተያየት ከመስጠት መቆጠብ፣ መንግሥት ላይ አፍራሽ የሆነ አስተያየት አለማሰማት እንደሚገባ ተነገረን። በተቻለ ማን ምን እንደሆነና ተግባሩንም ቢሆን በመጠኑ አስተዋውቀውናል። እኔ የነገሩኝን አመስግኜ ስቀበል፣ የነገሩኝንም ቢሆን በዚያው ልክ መጠርጠሬን አልረሳሁም። ሁሉንም በመቆየትና በማየት እንደምለየው ከዚያም አልፎ የሰማሁትን በጣም ከማውቃቸውና ገና ካላገኘኋቸው ማጣራት እንደምችል ወሰንኩ።

የቆጠራው ሰአት ደረሰ እየተቆጠርን ገባን። ከማእከላዊው የሚለይበት

- ከቆጠራ በኋላ መኝታ ክፍሉ አለመዘጋቱ፣
- ሽንት በባልዲ ሳይሆን በሰለጠነ መልክ ወደ መጸዳጃ ክፍል ሄዶ መጠቀም መቻሉ፣
- ወደ ክፍል ከተገባ በኋላ የበር ክፈቱልኝ ጩኸት አለመኖሩ፣
- በየክፍሉ ሲጋራ አለመጨሱ እያንዳንዱ ሰው ሬዲዮኑን የሚያዳምጠው በጆሮ ማዳመጫው ብቻ መሆኑና ሌሎችም።

ክፍሉም ቢሆን ከማእከላዊ የተጣበበ መኝታ በጣም የተሻለ ነው። እርግጥ እዚህም ቤቷ ከአቅሟ በላይ ውጣለች ግን እንደማእከላዊው እስክትፈነዳ አይደለም። በዚህ ላይ አልጋዎቹ ክፍሉን ሳያጣብቡና መተላለፊያም ሳይዘጉ ስለተቀመጡ፣ የመጣበብ ስሜት የለውም።

ዛሬ የመጀመርያ ቀን ስለሆነ እንደገባሁ አልጋዬ ላይ ወጥቼ ለመተኛት ነበር እቅዴ:: አልሰራም የቤቱ ሃላፊ እኛን ለመቀበል ቡና፣ ሻይ፣ ቀሺር፣ ሰሰላሳ፣ አምቦ አዘጋጅተው ኖሮ ዳቦ በመቁረስና አብረውን በታሰሩት የመንፈስ አባት ቡራኬ ተሰጥቶ «ወደዚህ ቦታ እንኳን ደህና መጣችሁ ባይባልም፣ ደስ ብሎናል::ደስታችን በመታሰራችሁ ሳይሆን በሕይወት ስላገኘናችሁ ነው:: የምንመኘው ከዚህ ቶሎ መውጣታችሁን ነው::» በማለት ቡና፣ ሻይ አሉን:: ሻይ ቡናችንን እየተጋበዝን የዜና ሰአት ደረሰና በእለቱ የነበረው የፍርድ ቤት ዜና በቴሌቪዥን ቀረበ:: በአቃቤ ሕግ ክስ መሰረት የዋስ መብት እንደተከለከልንና ዝነኛውን መኖና ህክምና ወደምናገኝበት ቦታ እንድንዛወር መታዘዙን ገለጠ::

በቴሌቪዥን የተባለውን ሰማን እንጂ ማንም ምንም አስተያየትም ሆነ ትችት አልሰጠም:: የቀረበውን ቡና እየጠጣሁ ዜናው በሚሰማበት ጊዜ ሰረቅ እያደረጉ ሲያዩኝ እኔም ሰረቅ እያደረግሁ አይ ነበርና ወሬ አቀባባይ የተባሉት እንማን ሊሆኑ እንደሚችሉ ለማወቅ ትንሽም ቢሆን ጥረት አድርጌ ነበር፣ ብዙም አልቀናኝም:: የቡናው ግብዣ እየተካሄደ በነበረበት ወቅት አንዳንድ ባጠገቤ ተቀምጠው የነበሩትን ቀስ እያልኩ ከታሠሩ ስንት ጊዜያቸው እንደሆነ ስጠይቅ አነስተኛው 10 ዓመት ነው:: ተስፋው አልተበጠሰም፤ ነጻ ሆኜ አለያም ፍርዴን ጨርሼ እወጣለሁ የሚል ተስፋ ይዞ ቀኑን የሚገፋ ነው::

ስንገባ ግቢውን በደንብ አላየሁትም ነበር:: መጸዳጃው የት እንደሆነ አውቄዋለሁ፣ የቀረውን ግን ገና ጠዋት ነው የማየው:: ስለዚህም ወደ ጣራ አልጋዬ ላይ መሰላሌን እረግጬ ወጣሁና ለእንቅልፍ ማምጫ መጽሐፍ እያነበብኩ ጋደም እንዳልኩ ሁሉም ተኛ፤ እኔና አንድ መጽሐፍ ቅዱስ የሚያነብ ሰው ብቻ ቀረን:: እኔም ልብ ወለዴን፣ እሱም መጽሐፍ ቅዱሱን እያነበብን ቆየንና እኔ ሳልቀድመው አልቀርም ተኛሁ::

ወደ ንጋት አካባቢ ላይ ሽንት ያዘኝና ወደ መታጠቢያ ቤት ስሔድ ከበሩ ላይ በሩቅ የማውቀውን አየር መንገድ ጸረ አይሮፕላን ጠላፊ ሆኖ ይሠራ የነበረ ሰው አገኘሁት:: ሰላምታ ተለዋውጠን ያን ጊዜ ገና ማጨስ አላቆምኩም ነበርና የመጣሁበትን ጉዳይ



ከጨረስኩ በኋላ፣ አብረን ጥግ ይዘን ሲጃራችንን እያጨስን አወራን:: በተደጋጋሚ አብረን እንደበረርን አስታወሰኝ፣ አንድ ሁለቱን አስታውሳለሁ:: ሲጋራችንን ጨርሰን አንዳንድ ማስጠንቀቂያዎችን ሰጥቶኝ ጠዋት እንገናኛለን ተባብለን ተለያየን::

ወደ መኝታ ክፍሌ ስመለስ ሁሉም በመነሳት ላይ ነው:: ጠዋትም ቆጠራ አለ፣ የፈለገ መኝታው ላይ ሆኖ ይቆጠራል፣ ያልፈለገ ውጪ ወጥቶ ተቆጥሮ ወደ ቁርሱ ሊሄድ ይችላል:: ለቁርስ ዳቦና ሻይ ከማረሚያ ቤቱ ይሰጣል፣ ክበብም አለ፣ እኛ እያንዳንዳችን አንዳንድ ደረቅ ምግብ ለቁርስ የሚሆን ይዘን መጥተናል:: እኔ ባለሁበት መደዳ እነጋሼ መስፍን (ፕሮፌሰር) ስላሉ ለቁርስ የሚሆነውን አዘጋጅቼ ከቆጠራ በኋላ ለመቀላቀልና ለመብላት ተዘጋጀሁ:: የቤቱ ሃላፊ ወረፋ ሳይበዛ ታጠብ አለኝና ምክሩን ተቀብዬ ልታጠብ ስሄድ፣ በመታጠብያ ቦታው ላይ የሚታጠቡና ተራ የሚጠብቁ በርካታ ሰዎች አሉ:: ከማውቃቸው ውስጥ ሻምበል ፍቅረሥላሴን፤ ሻለቃ ፍስሐ ደስታን፤ ገሠሠ ወልደ ኪዳንን፤ ለገሰ አሰፋውን፤ ኮሎኔል ተስፋዬ ወልደስላሴን፤ ናዝሬት የማውቀውን ኑሪን፤ አገኘኋቸው:: ፍቅርና ትህትና በተመላበት ሁኔታ ሰላም ተባብለን ተሳሳምን:: «ለመታጠብ ለእንግዳ ቅድሚያ ስጡ» አለ፣ አንድ ሰውና ቅድሚያ ተሰጠኝ፤ ትንሽ ልግደረደር ስሞክር «ግድ የለም አይደገምም፣ የዛሬውን ግን ተጠቀምበት» አሉኝና ታጥቤ ወደ ቁርሴ ሄድኩ:: እነጋሼ መስፍን የመጨረሻው ቤት ውስጥ ማለትም ከመታጠቢያ ቤት ስንመለስ የምናገኘው የመጀመሪያው ቤት ስለሆነ ስደርስ ለካ እነሱ ቀድመው ተጣጥበው ተዘጋጅተዋል:: ከጋሽ መስፍን ጋር የነበሩት አባይነህ ብርሃኑ፤ ስለሺ ጠና፣ ካሳሁን ከበደ ሙሉነህ ኢዮኤል ነበሩና ተቀላቅዬ ቁርስ በልተን፣ ሻይ አንድ ሰው የሁላችንንም አምጥቶልን ነበርና ጠጣን:: ያን ያመጣልን ሰው ለዘለቄታው እዛ እስካለን ድረስ አገልግሎት ሊሰጠን፤ ማለትም የበላን የጠጣንበትን እቃ እንዲያጥብልን፤ ምሳና እራት እንዲያቀርብልን ቀጠርነው::

ቁርስ ከበላን በኋላ ማታ በአንዳንድ ምክንያት ሳናስገባው ከውጭ ያደረ ንብረታችንን እንድናስገባ

ስለተፈቀደልን፣ ወጥተን እየመረጥን የየራሳችንን ይዘን ገባን።ያን ቦታ ካስያዝን በኋላ ቃሊቲ መግባታችን በተባባሪዎቻችን የማእከላዊ ሰዎች ለቤተሰባችን እንደሚነገር ስላረጋገጥን የሚመለሰውን ምግብ የመጣበትን እቃችንን ማዘጋጀት ያዝን። ማእከላዊ እያለን፤ ዳንኤል በቀለ፤ ዶ/ር ታዴዎስ፤ አሰፋ ሃብተወልድ፤ አንተነህ ሙሉጌታ፣ እኔ አብረን ስለነበርን የምግብ ተራ ለማውጣት ተገናኘን። ይህ አዲስ የመጣ ሃሳብ ነውና የግድ ከነጋሼ መስፍን ቡድን ወጥቼ ወደዚህኛው መግባት ነበረብኝ። ተገናኝተን ስንነጋገር በያለንበት አቅጣጫና መኝታ ቤት ብንቀናጅ ይሻላል የሚል ሃሳብ ቢመጣም "ግድ የለም እንደስምምነታችንና እንደምርጫችን ይሁን" ተብሎ፤ ደ/ር በፈቃዱ፤ አቶ ብሩክ፤ ዳንኤል፤ አንዱዓለም፣ ዓለማየሁ፣ ኢንጅነር ግዛቸው፤ አንተነህ፤ ነጻነት፣ እኔ አንድ ላይ ተጣመርን። የምግብ ማምጫም ፕሮግራም አውጥተን ለቤተሰብ ለማሳወቅ ሳምንቱን ተከፋፍለን፣ ቅዳሜና እሁድን ሳይጨምር አንድ ቤተሰብ በሳምንት አንድ ቀን ብቻ እንዲያመጣ ተወሰነ።

ይህን እንደጨረስን ግቢውን ሳይ። በሩ ላይ አንድ ቢሮ ከነድምጽ ማጉያው፣ ከዚያ ጋር ተያይዘው የታራሚዎቹ አስተዳደር ተብለው የተመረጡት ቢሮዎች አሉ። ከሱ ቀጥሎ የዚያ ዞን ሃላፊዎች ያሉበት ሲሆን። ሁለት ወጣቶች አሉ። እነሱ ሳይፈቅዱ አንድም ነገር አይፈጸምም። ሕጉ የተጻፈ ባይሆንም እነሱ ለዚያ ዞን የሚያወጡት መመርያ እንደአስፈላጊነቱ በየቀኑ የሚነደፍ ነው። ከነሱ ክፍል ቀጥሎ አንድ የደም ብዛትና የስኳር መጠን የሚለካበት ክፍል፣ ከዚያ አጠገብ መኝታ ቤትና መጻሕፍት ቤት ነው እነብርሃኑ እዚህ ክፍል ውስጥ ሲሆን፣ ከዚያ ባጠገብ ሻይ ዳቦ እንጀራና ወጥ የሚታደልበትና ከሱ ፊት ለፊት ክበቡ አለ። በስተጀርባ ደሞ ልብስ ሰፊዎች፤ የቆዳ ውጤት ሰሪዎች ሰፈር፤ የምግብ ማቀዝቀዣና ማሞቂያ ክፍል ነው እኛም የመመገቢያ ቦታችንን እዚሁ አጠገብ አደረግን። ከሱ አግድም የነብሩክ መኝታ ከዚያ ለጥቆ የነግዛቸው፣ ከኀኑ መጸዳጃው ነው። ወደላይ ሲል የነጋሼ መስፍን፣ አባይነህ፣ ሙሉነህ፣ ስለሺ፣ ገብረጻድቅ፣ ቀጥሎ እኔ ያለሁበት፣ ከኀሬቤት ዶ/ር



በፈቃዱ፣ ከፍ ሲል ነጻነት፣ ከኀኑ እነ ሻለቃ ጌታቸው፣ ዶ/ር ያዕቆብ፣ ዳሩ ላይ እነ ኢንጅነር ኃይሉ ሻውል ናቸው።

እነ ብርሃኑ ካሉበት ቤት በረንዳ ላይ የካርታ የዶሚኖ የቼዝ፤ የተለያዩ ጨዋታች ይካሄዳሉ። ቢንጎም በፕሮግራም የሚካሄደው በዚሁ ቦታ ነው። ቤተሰብ ምግብ ሲያመጣ እቃችንን ወደ በሩ የሚወስዱ የተወሰኑ ሰዎች አሉ። እነሱ እቃዎቻችንን የሚያነሱበት የተወሰነ ቦታ ስለአለ እቃዎቻችንን ወስደን እዚያ አድርገን ቡና ለማለት ወደክበብ ስንገባ ጋባዡ በዛ። መጠጣት የምንችለው የተወሰነ ቢሆንም፣ ሁሉም ኩፖን በያይነቱ እየገዛ የግድ ይሰጠናል። ኩፖኑ ከቡና ሻይ ጀምሮ እስከ ጭማቂና አምቦ ውሃ ያስጠጣል። አንድ ጊዜ ስቆጥረው 38 ኩፖን ነበረኝና እኔም ከምሳ በኋላና ከራት በኋላ ግብረአበሮቼን እጋብዝበት ነበር።

እዚህ ግቢ ውስጥ ድሮ ደርግ በስልጣን ላይ በነበረበት ጊዜ አንዳንድ እንደ እግዚአብሔር የሚታዩና እንደ እግዚአብሔር የሚያዩዋቸው ሰዎች በአንድነት፣ በአንድ ዓይነት አኗኗር አሉ። የገበሬ ማሕበር ካድሬ የነበረው ጓድ ለገሰ አስፋው ከማለት በስተቀር። እንኳን አብሮ አንድ ላይ ፊቱን ሊታጠብ በመልክም አይተዋወቁም ነበር። "ጓድ ፍቅረስላሴ፣ ጓድ ፍስሐ ደስታ" ሲባል በሬዲዮ ከመስማትና በጋዜጣ ሲነበብ ከመስማት አልፎ፣ አንድ ላይ አንድ ሱቅ ውስጥ ገብቶ ለመግዛት መቻል ቀርቶ፣ አስቦትም አያውቅም ነበር። አሁን ግን ሁሉም እስረኛ ሆነው አንድ ላይ ናቸው።

በዚሁ እለት አንደኛ የፍርድ ቤቱ ቦታ ከርቀቱ የተነሳ ከደህንነትም አኳያ እንዲቀየርና እስር ቤቱ ባለበት አካባቢ እንዲዛወር /ወደ ቃሊቲ ተወስደን ስለነበር/ ይህንንም ለማዘጋጀት ቀን እንዲጨመርለት እንዲፈቀድለት በመጠየቁ ጥያቄዎች በሙሉ በሚቀጥለው ብይን እንደሚሰጥባቸው ተወስኖ ለአቃቤ ሕግ በሚያመች መልኩ ተቀጠረ። በሚቀጥለው ቀጠሮ የተከሳሾች ስም ዝርዝርና የክስ ቻርጅ ለያንዳንዱ ተከሳሽ ተሰጠ።በዚሁ እለት ከኛ ጋር በኛው ክስ አይነት የተከሰሰው የ14 ዓመቱ ልጅ ጉዳይ የሆስፒታል መረጃና የክርስትና ወረቀት ቀረበ። ፍርድ ቤቱም ለዚህ አስፈላጊውን ማጣራት አድርገን ውሳኔ ለመስጠት ብሎ

ለ16/6/98 ተቀጠረ:: በዚህ ጊዜ ዶ/ር ብርሃኑ የተዘጋጀውን አቤቱታ ለማቅረብ ጠይቆ ማንበብ ሲጀምር ዳኛው አልሰማህም ብሎ ከለከለው:: ዶ/ር ብርሃኑ ቀጥሎ ጨዋነት በተላበሰ መልኩ «የተከበረው ፍርድ ቤት» ሲል «አላዳምጥም ተቀመጥ» በማለት የመደመጥ መብቱን ገፈፉት:: ያም ሆኖ ተስፋ ባለመቁረጥ «ክቡር ፍርድ ቤት፣ አቤቱታ አለን» ሲል አሁንም በፈላጭ ቆራጭ ስሜትና በማን አለብኝ የበላይነት «አልሰማም አርፈህ ተቀመጥ፤ አልፈቀድኩልህም አላዳምጥም!» ሲሉ ነው ሁላችንም በፍርድ ቤቱ ላይ የነበረንን ትንሽ በጣም ትንሽ አመኔታ ጨርሶ ያጣነው:: ሁላችንም «እንዴት ነው ነገሩ» አልን ዳኛው አሁንም ጥላቻቸው፤ ንቀታቸው፤ ከበፊቱ በከፋ መልኩ «እናንተ እንደፈለጋችሁት አይደለም እናዳምጥም በቃ» ብለው ሲደመድሙ ዶ/ር ብርሃኑም «ይህማ ከሆነ እኛም በዚህ ፍርድ ቤት አንዳችም ከዚህ ፍርድ ቤት ምንም ፍትሕ አንጠብቅም» ሲል፣ ዳኛው "እናንተ ፈልጋችሁ ሳይሆን Compulsorry jurisidiction ነው" በማለት ሲመልስ፣ ብርሃኑም «እኛ ደግሞ ከዚህ ፍርድ ቤት ምንም ፍትሕ አንጠብቅም» በማለቱ ዳኛ አዲል ተናዶ ሲወጣ ሲነሳ ሕዝቡና እኛም ተከሳሾች አጨበጨብን፣ ፉጨትም ተሰማ:: ዳኛ አዲልም ንዴታቸውን ይዘው ወጡ፣ እኛም ወደ ቃሊቲ ቤተሰብም ወደ ቤት::

በተከታዩ ቀጠሮ በ16/6/98 በዚህም እለት ከቃሊቲ ቀደም ብለን ነበር የወጣነው:: እኛና ቤተሰብ ቀድመን ደርሰናል ቤተሰብ እየተፈተሸ በመግባት ላይ ነው:: ዳኞች መምጣታቸውን መኪና ውስጥ ሆነን አይተናል አቃቢያነ ሕጎች ግን ገና አልመጡም:: የፍርድ ቤቱ የሥነስርአት ፖሊስ ብቅ እያለ ያያል፣ ተመልሶ ወደ ውስጥ ይገባል:: ከጥቂት ጥበቃ በኋላ አቃቢያን ሕጎች ያለአንዳች ይሉኝታ ሹም አቃቤን አስቀድመው ገቡ ወዲያው መግባታቸው ለዳኞቹ ተነገረና ፍርድ ቤቱ ተሰየመ::በተለመደው የፍርድ ቤት ሥነስርአት መሰረት ዳኞች ሲሰየሙ ተነስተን ቆመን ተቀመጡ ስንባል ተቀመጥን:: «ዳኛ» አዲል የከሳሽ ተከሳሾችን መቅረብ አለመቅረብ ጠይቀው ሁሉም መቅረባቸው ተረጋገጠላቸው:: ወዲያው የእምነት ክህደት ቃል መጠየቅ ተጀመረ::



ኢን/ር ኃይሉ ሻውል «ይህ ክስ የፈጠራ ክስ ነው:: ወንጀል አልፈጸምንም»አሉ:: ን/ር መስፍን ካሁለት ደቂቃ ይፈቀድልኝ ብለው ንግግር ሲጀምሩ ዳኛ ው አቋረጣቸው:: ዳንኤል፤ ነጻነት፤ ካሳሁን በጠበቃ-ቻቸው አማካይነት ተቃውሞ አቀረቡ:: ሌሎች ተከሳሾች ስማቸው ሲጠራ በመነሳት በጃቸው አፋቸውን በመያዝና ፊታቸውን በማዞር፣ አለያም ተነስተው ድምፅ አልባ መልስ ሰጡ:: ዳኛውም «ዝምታን እንደ ጥፋተኛ አይደለሁም እንቀበለዋለን፣ ሕጉም የሚደነግገው ይህንኑ ነው» በማለት የኛ ጉዳይ ተዘጋና ወደ ሕጻን ብንያም ጉዳይ ዞረ:: የብንያምን ጉዳይ ለማጣራት ለቤተክርስቲያኑ ለተጻፈው ደብዳቤ በተሰጠው መልስ «ብንያም ክርስትና ተነሳ በተባለበት እለት የክርስትና ስርአት እንዳልነበረ አስተዳዳሪውም እንዳልነበሩ፤ ቄሱም የቅስና ሹመት አግኝተው አልተገኙም» ተብሎ ብንያም ከፖሊስ ጣቢያ ወደ ማረሚያ ቤት እንዲዛወርና ለሚቀጥለው ቀጠሮ ጠበቃ አነጋግሮ እንዲቀርብ ለ22/6/98 ተቀጠረ::

# ኑሮ በቃሊቲ

ከገባንበት እለት አንስቶ ልዩ ፍቅር፤ አክብሮት፤ ትህትና ነበር ያሳዩን:: ለሁሉም ነገር ለኛ ቅድሚያ መስጠትን ይመርጣሉ::

በዚህ ዞን ማንም ሰው ሬዲዮኑን ከጆሮ ማዳመጫ ውጪ መስማት አይችልም::ክልክል ነው::ሁሉም የሚመርጠውን ሬዲዮ ጣቢያ በግለኝነት ያዳምጣል::በየክፍሉ ያለው ቴሌቪዥን የሚከፈትበት የድምጽ መጠን የተወሰነ ነው ሳይጮህም ለማዳመጥ ሳያስቸግርም::የወል የሆኑ ፕሮግራሞች እንደ ኳስ ጨዋታ ፊልም ለሁሉም ይስማማሉና ችግር የለባቸውም ስለዚህም ከአራት ሰአት በኋላ ያለው የዘወትር ፕሮግራም በጣም ዝቅተኛ በሆነ ድምጽ ይከፈታል:: በቦታ ርቀት ማዳመጥ የሚያስቸግረው ወንበሩን ይዞ ከሌለውም ባዶውን ወንበር አስጠግቶ ያዳምጣል::ሁሉም የተስማማበት ህግ:: ለሁሉም እኩል የሚሰራ ህግ ነው::

ይህ መመርያ እንደገባን ነው የተነገረን፤እኛም ይህንኑ ተቀብለን ተግባራዊ አደረግን።

ሁሉም እግሩን ለማፍታታት በግቢው ውስጥ በእኩል ደረጃ ይንቀሳቀሳል፣ ማንም ቢመጣ መሽቆጥቆጥ ጨርሶ አይታሰብም እየተሻሹ ማለፍ መተላለፍ ነው። ሰላምታ መለዋወጥ፣ መጠያየቅ፣ ስለቤተሰብ ማንሳት የተለመደ ነው ግን መከባበር እንጂ መፈራራት ጨርሶ ተረስቷል። አሁን የሚፈራው። የሚያሸቆጠቁጠው፣ ማእረጉ የማይታወቅ፣ ምንነቱ ያልተለየ እንዲያው ዝም ብሎ የዞኑ ሃላፊ ተብሎ የተቀመጠው ነው ሲፈልግ የሚፈቅድ፣ ሲሻው የሚከለክል፣ አንድ ወጥ የሆነ መመሪያ የሌለው ነው።

የቤተሰብ ምግብ መቀበያ በመድረሱ አምጪዎቹ አምጥተው ስም እየተጠራ መስጠት ሲጀምር፣ የኛም ተጠራና ሄደን እየተቀበልን በየቤቱ ታደለ። ወዲያው የዞን ሃላፊዎች አልፎ አልፎ እየጠሩ የዞኑን ህግና ስርአት ነገሩን። የሰማነው ላልሰሙት እንድንናገር ተደረገ። የስኳር በሽታ ያለባቸው ለገብስ ዳቦ ተመዘገቡ።

የምግብ አቅራቢ ተራ አውጥተን ስለነበር የእለቱ ምግብ አቅራቢዎች ሥራቸውን ጀመሩ የመጣው ምግብ ትኩስ ስለሆነ ማሞቅ አላስፈለገም። ብቻ ከመጣው ውስጥ ለቁርስ፣ ምሳ፣ እራት የሚሆነውን እየመረጡ ማስቀመጥና የምሳውን ማቅረብ ነው። ሁላችንም ማእከላዊ እያለን ቤተሰብ ያመጣልንን የምግብ መብያ ሰሃን ይዘን ስለመጣን ችግር አልገጠመንም፣ በኩባያም በኩል ቢሆን ያው ነው። ለነገሩ፣ የማረሚያ ቤቱም የእስረኞች ኮሚቴ ይሰጣል። ምሳ ደርሶ ተሰባስበን በየምድባችን በላንና ቡና ታዞ ተጠጣ። በኛ ቡድን ውስጥ የምግብ አቀራረብና ዝግጅት ባለሙያዎቹ ዳኒና አንተነህ ናቸው። ነጻነትና እኔም ምንም አንልም።

ከምሳ በኋላ ሁሉም ትንሽ ተንቀሳቅሶ በኋላ እረፍት ለማድረግ ወደየቤቱ ገባ። እኔ ወደ ክፍሌ ገብቼ ጋደም ልል ስል ሁለት የእድሜ ባለጸጋ የሆኑ አንዱ የጎጃምና አንደኛው የጎንደር ሰው፣ ጠጋ ብለው ያናግሩኝ ስለነበር እንቅልፉ ቀርቶ በረንዳ ላይ ወጥተን ወሬያችን ቀጠልን። ከጎጃም የመጡትን ሁሉም አቶላምጦ የሚጠራቸው የመቶ በማለት ነውና እኔም በዚያው ጠራኋቸው ሲያወሩ አፍ ያስከፍታሉ። «ቀደም ሲል



በደርግ ጊዜ በሽፍትነት የሚቀርበኝ አልነበረም፣ እውነቴን ነው ያላስፈሳሁት ዳገት የለም!» አሉ። ተሳስተው እንደሁ ብዬ «ያልፈሳንበት ዳገት» ማለት ነው? ስላቸው « ሃሰት! እኔ አስፈሳዋለሁ እንጂ፣ ደሞ ዳገት ሊያስፈሳኝ?» አሉ።

18 ዐመት አመክሮ ተቀንሶ ፍርዳቸውን ሊጨርሱ ጥቂት ነው የቀራቸው። ቤተሰቦቻቸው የት እንዳሉ አያውቁም ነበርና አይጠየቋቸውም። በአጋጣሚ አንድ ሰው አግኝተው ልከው፣ ልጃቸው ያለ ንብረታቸውን ሽጦ ሊጠይቃቸው አዲስ አበባ መጥቶ ከተመለሰ በኋላ የደረሰበት አልታወቀም። "ምናልባት ባላገር ስለሆነ፣ ገንዘብም ስለሌለው፣ መሳፈሪያውንም ተሰርቆ አንድ ቦታ ወድቆ ወይም ቦዘኔ ተብሎ አንዱጋ ታስሮ ይሆናል" ብለው ይሰጋሉ። ከመቶ ጋር በጣም ተቀራረብን። የጎንደሩም አቶ ጥላሁን የሚባሉት የቀበሌ ጠባቂ ሆነው ሰዎች ሊገደሉ ሲሄዱ አይተዋል ተብለው እንደታሰሩ ነው የነገሩኝ። አቶ ጥላሁን ግጥምም ይጽፋሉና አንብብልኝ እያሉ አሳይተውኛል።

ሁለቱም ጨዋታ ስለሚያውቁ በጣም ተወዳጀን። ስለ ሁኔታው ሲያወሩኝ በመጀመሪያው ሰሞን ሽንት ቤት ሰው ሁሉ ከተኛ በኋላ እንደሚጠቀሙ የመቶ ነገሩኝ። "ለምን? ደንብ ነው?" ስላቸው፣ "አይደልም! ነገሩ ወዲህ ነው" አሉና ታሪኩን ነገሩኝ። "አንድ ቀን መጸዳጃ ቤት ቁጭ ብዬ ስጸዳዳ አንድ የቀድሞ ትልቅ ባለስልጣን ከጎኔ ካለው መጸዳጃ ተቀምጠው እንደሰው ሲሆኑ ሰማሁና አዘንኩ፤ እነሱም እንደኛ! ብዬ ከዚያ ቀን በኋላ ያንን ላለመስማት ሰው ሁሉ ከተኛ በኋላ ነው የምጠቀመው" አሉኝ። "እንደሰው ሲሆን ምን ማለት ነው? ሰው አይደለም እንዴ?" ስል "ሰውማ ነው፣ ግን እንደኔና እንዳንተ የሚፈሳ አይመስለኝም ነበር። አሁን አሁን ነው ጊዜ እያለፈ ስልጣኑ እያለቀ ሲሄድ ሰው ሆኑ እንጂ በፊት ደርጎች ሆነው እንዲህ እንደኛ የሚያደርጉ አይመስለኝም ነበር" አሉኝ። ላሳምናቸው ብሞክርም "አይተሃል? እንደኛ ሲያደርጉ ሰምተህ ታውቃለህ?» በሚል በማላውቀው ፈተና ጣሉኝ። በኋላ ስቆይ የዚህ አይነት አመለካከት የነበራቸው የመቶ ብቻ

እንዳልነበሩ ተገንዝቤያለሁ::ይህ ስሜት እስካሁንም ድረስ ከአንዳንዶቹ ውስጥ ገና ሙልጭ ብሎ አልወጣም::

የቀይ ሽብር ተፋራጆች ያሉበት ዞን በራሳቸው በታሳሪዎች ጥረትና ድካም በሚገባ የለማ ነው:: በሌሎች ዞኖች የሌሉ በርካታ መገልገያዎች አሉት:: አንድ ታሳሪ እዚያ ገብቶ የዚያ ዞን አባል ሲሆን በሕብረት ሱቁ እንዲጠቀም፣ የክበብ አባል እንዲሆን፣ በችግሩ እንዲረዳ፣ ሲባል አባል ለመሆን የሚከፍለው አለ:: ይህ ደግሞ ለማትረፍ ተብሎ የተቋቋመ ሳይሆን ታሳሪውን ለመጥቀም እንደሆነ በቆይታዬ ተገንዝቤአለሁ::

ይህ ማሕበር ፍሪጆች አዘጋጅቶ የታሳሪው ምግብ እንዳይበላሽ ያስቀምጣል ለስላሳ፣ ወተትና መሰሎችን ያቀዘቅዛል፣ የምግብ ማሞቂያም ስላለ ታሳሪው የሚሞቅ ካለው ይገለገላል:: ማሕበሩ የሚሰጠው ግልጋሎት የታሳሪውን ሕይወት የተሻለ አድርጎለታል፣ እኛም በቆይታችን ተጠቃሚዎች ነበርን::

እስር ቤት የገባ ሰው በቅድሚያ መጠንቀቅ ያለበት ጤንነቱን በተመለከተ ነው:: ይህ ደሞ ሃኪም ቤት በመሄድ ብቻ ሳይሆን በተገኘው አጋጣሚ በመጠቀም ትንሽ እንቅስቃሴ ካልተደረገ በስተቀር ተሳስሮ ከመቀመጥም አልፎ ለተለያዩ በሽታዎችም መጋለጥ አለ:: በዚህ ባለንበት ዞን በቂ የመንቀሳቀሻ ቦታ ስለአለ ቀዳሚ ታሳሪዎች በሌሊት በመነሳት ወደ ሰውነት እንቅስቃሴ ስለሚሰማሩ እኛም በመቀላቀል የየአቅማችንን ማድረግ ያዝን:: እንቅስቃሴውን የሚመሩት የዓየር ሃይል አባላት የነበሩትና በእስር ላይ የቆዩት ኮሎኔል ሰሎሞንና ሻምበል ክፍሌ ናቸው:: ጥሩ የሰውነት እንቅስቃሴ ማሰራትና መስራት ስለሚችሉ ተከታዮች አብዝተዋል:: ይህን ለጥቂት ቀናት ከሰራን በኋላ ግቢ ኃላፊዎች ድንገት አንድ ቀን ብልጭ አለባቸውና በህብረት ጂምናስቲክ መስራት አትችሉም በማለት ለአሰሪዎቹ ማስጠንቀቂያ ሰጡ:: ማስጠንቀቂያው ዝም ብሎ "ብታርፍ ይሻልሃል" አይነት ተብሎ የሚታለፍ ሳይሆን፣ ወደ ጨለማ ቤት መጣልን ሊያስከትል፣ አለያም ወደ ከፋና መተኛት ወደማይቻልበት የተጣበበ ዞን መቀየርም ስለሚያስከትል ትእዛዛቸው ተግባራዊ ሆነ:: ማስጠንቀቂያው በዚህ ብቻ



ሳያበቃ ክፍሌ ይሰጥ የነበረውን የጸጉር ማስተካከል አገልግሎትም እንዲያቆም ተወስኖበት የሚያገኘው ትንሽ ገቢም እንዲቋረጥ ሆነ::

በሳምንት ሁለት ቀናት ቅዳሜና ዕሁድ ታሳሪ ከቤተሰቡ ጋር ይገናኛል:: ሌላው ታሳሪ ጠዋት ከሶስት እስከ ስድስት ከቀትር በኋላ ከ7 ተኩል እስከ ዘጠኝ ከቤተሰቡ ጋር በበቂ ሲገናኝ፣ እኛ ግን በተለየ ፕሮግራም ከቀትር በኋላ ለአንድ ሰአት ከ9 እስከ 10 ነበር:: ይሄውም በዛ ተብሎ ቢያንስ ከ15 ደቂቃ ያላነሰ በየሰበቡ ይቀነስብናል:: ወደ መገናኛው ስንሄድ ከሩቅ ለምናያቸው ቤተሰቦቻችን ለሰላምታ የቅንጅት የምርጫ ምልክት የሆነውን ጣት ስናሳይና ቤተሰብም በተመሳሳይ መልስ ሲሰጥ፣ ፖሊስ ያን ቤተሰብ እያዳፋ ያስወጣዋል፣ ወይም ሌላ ቀን ሲመጣ ጥቁር መዝግብ ውስጥ አስገብቶ ይከለክለዋል:: ይህ ለምን ክልክል እንደሆነ ፈጽሞ ሊገባኝ አልቻለምና አንድ ቀን ክበብ ውስጥ ቁጭ ብለን ሳለ የዞኑ ሃላፊ ከሆኑት አንዱ መጥቶ ስለነበር፣ በዚያ ክበብ ውስጥ ስላሉት ንቦች አቤቱታ አቀረብኩ:: አቤቱታዬ « እኛ ከቤተሰብ ጋር ስንገናኝ በጣት ሰላምታ ስንሰጥ ችግር ይገጥመናል እዚህ ግን ንብ እየመጣች ስትዝናና ምንም አትሆንም» አልኩ:: እግዜር ይስጠው ቀልዱ ገብቶታል መሰለኝ በሳቅ አለፈው::ኑር ያልኩት ናዝሬት የማውቀው የክበብ አመራር ስለሆነ ከዚያ አይጠፋምና ይህንን ስል ሰምቶ «እድለኛ ሰው ነህ እኔ እንዳንተ ልል ቀርቶ ማሰብ እንኳን አይፈቀድልኝም» ብሎ አሳቀን:: በኋላ ሳስበው እውነቱን ነው በክፉ አላየውም እንጂ ሊያስቀጣው የሚችል ነበር:: ከዚያ በኋላ ሁለት ጊዜ ማሰብ አንዱ መመሪያዬ ሆነ::

ማእከላዊ እያለሁ የጀመርኩትን ህክምና ለመቀጠል እንድችል ለህክምና ተመዘገብኩና ወደ ግቢው ክሊኒክ ሄድኩ:: በዚያ ያሉት ረዳቶች ካዩኝና ችግሬን ካስረዳኋቸው በኋላ ዋናው ሃኪም ዘንድ መቅረብ እንዳለብኝ ተነግሮኝ ሃኪሙ በሚመጡበት ቀን እንድመጣ ቀጠሮ ተሰጠኝ:: በዚህ ቦታ አንድ የተቃለለልኝ ነገር ቢኖር በመጸዳጃ ቤቱ ውስጥ እንደኔ የወገብ ችግር ላለባቸው ታሳሪዎች ሲባል የተዘጋጀ፣ ለመቀመጥም ለመነሳትም ችግር የማያስከትል

መቀመጫ ከመኖሩም ባሻገር፣ ለሚፈልግ ሰው ተዘዋዋሪ የመጸዳጃ ወንበር አምሮ ስለሚሰራ በዚህ በኩል ያለው ችግር ተቃሎልኛል::

የቃሊቲ እስር ቤት አስተዳደር አንድ ሊያደርግ የሚገባው ነገር ከቀይ ሽብር ተፋራጆች ግቢ ትምህርት በማግኘት የሁሉም ዞኖች ታሳሪዎች በሚቻለው መንገድ ግቢያቸውን ውጪ ካለው ህብረተሰብ ድጋፍ በመጠየቅ እና በተለያየ ምክንያት ታስረው ፍርዳቸውን ጨርሰው የወጡትን በማስተባበር ግቢዎች እንዲለሙ ቢደረግ ሁሉም ተጠቃሚ ይሆናል::

በዚህ ሁኔታ ላይ ያየሁትና ያጋጠመኝ ነገር ትንሽ ግራ የሚያጋባ ነው:: በመጀመሪያ የቅንጅት ሰ-ዎች ወደ ሃኪም ቤት ስንሄድ ከሌሎች ታራሚዎች ጋር ሳይሆን ለብቻችን በተለየ ሰአት ሆኖ እኛ በምናልፍበት ሁሉ ሰው አያልፍም:: እኛም ሆን ሌሎች ሰዎች የእግዜር ሰላምታ እንድንለዋወጥ አይፈቀድልንም:: በክሊኒኩ ምርመራ ቦታ ተራ የሚጠብቁም ካሉ ያለምንም ይሉኝታ ተባረው እኛ ገብተን ጨርሰን እንሄዳለን:: ሁላችንም እስረኞች ሆነን፣ ባንድ የእስር ቤት ግቢ ውስጥ እየኖርን እንደተጣላ ደመኛ እንዳንገናኝ፣ እንዳንስማማ የሚደረግበት ምክንያት ምንድን ነው?አይገባኝም:: አንድ የምሰጠው ትርጉም ቢኖር «ክፋት» ብቻ ነው ሊባል የሚቻለው::

የግቢው ክሊኒክ ዶክተሩን እንዳነጋግር ቀጠሮ በሰጠኝ በሁለተኛው ቀን ወደ ሃኪሙ ዘንድ ቀርቤ አስቸኳይ ሪፈራል ለፖሊስ ሆስፒታል ተጽፎልኝ ወደ ፖሊስ ሆስፒታልም በ3 ቀናት ውስጥ ሄድኩ:: ፖሊስ ሆስፒታል ዶክተሩን ለማግኘት ወረፋ ከሚጠበቅበት ክፍል ሲያስገቡኝ፣ በዚያ የነበረው ሁሉ ሰላምታ መስጠትና ስለጤንነቴ ስለሌሎች የቅንጅት አባላት መጠየቅ ስላበዛ ወዲያው ከዚያ ክፍል አውጥተው ዶክተሩ ክፍል አስገብተው አስቀመጡኝ::በዚያም ቢሆን ለሌላ ሥራ የሚመጡት የሆስፒታሉ ሠራተኞችም ቢሆኑ ሰላም ከማለት አልቦዘኑምና የጥበቃው ሃላፊ የሚያደርገው ጠፋው::



ሐኪሙ ሲመጡና ሲያገኙኝ እሳቸውም ከምርመራው በፊት ሰላምታና «እንዴት ናችሁ?»ን ነበር ያስቀደሙት:: ወዲያው መረመሩኝና የችግሬን አሳሳቢነት በመገንዘብ በሚቀጥለው ቀን እንድተኛ ታዞ የአልጋ ቀጠሮዬን ተቀብዬ በነጋታው ለመተኛት የሚያስፈልገኝን ለማዘጋጀትና ለመመለስ ወደ ቃሊቲ ሄድኩ:: እንደደረስኩ ሁሉም ውጤቱን ሲጠይቀኝ እንድተኛ መታዘዙን ተናግሬ የሚያስፈልገኝን ከማዘጋጀት በፊት ምሳ ተበላ:: በምሳ ሰአት የወጪ ተብሎ ከክበቡ ጭማቂ ተጋበዝኩ፣ ቡናም ታዘዘልኝ:: ሁሉም መልካምና የተሳካ ህክምና አድረጌ ቶሎ እንድመለስ ተመኙልኝ::

እጄን ለመታጠብ ስሄድ በጭንቅላቴ አንድ ነገር ብልጭ አለብኝ::ቤተሰቤ መተኛቴን ማወቅ አለበት:: መታመሜንና የሃኪም ቀጠሮ እንዳለኝ ቀደ ጥገናም እንደሚያስፈልገኝ ያውቃሉ:: ተኛ መባሌንና መተኛቴን ግን መነገር አለባቸው:: እግረ መንገዴን ካልሲና መሀረብ ይዤ ወደ አንድ ቦታ ስሄድ አንድ ወጣት አገኘሁና ሰላም ተባብለን ቶሎ ሰው ሳይመጣብን የስልክ ቁጥሬን ነገርኩትና ነገ ፖሊስ ሆስፒታል እንደምተኛ ለቤተሰቦቼ እንዲነግርልኝ ጠየኩት:: «ዛሬውኑ ይደርሳል ጋሽ ደቤ አይዞህ ተረጋጋ እንጠይቅሃለን» አለኝና በዚሁ ተሰነባበትን:: እኔም የያዝኩትን መሃረብና ካልሲ አጥቤ ወደ ክፍሌ ተመለስኩ:: ትንሽ እረፍት አድርጌ ለሆስፒታል የሚያስፈልገኝን በሻንጣ ካዘጋጀሁ በኋላ ቡና ለመጠጣት ወደ ክበብ ስሄድ ሁሉም ጋባዥ ሆነ፤ ሁሉም ጠጣ ማለት ያዘ፤እኔ ደግሞ ከአንድ ቡና ማለፍ አልቻልኩም::

## ወደ ፖሊስ ሆስፒታል

ቀኑ አለፈ፤ ማታም እራት ከተበላ በኋላ ወደ መኝታዬ አመራሁ:: በማግስቱ ጠዋት ስሜ ተጠርቶ ነበርና ቁርስ በልቼ እቃዬን ይዤ በሩ ላይ መኪና መጠበቅ ያዝኩ:: አንድ ፖሊስ መጥቶ የያዝኩትን ሻንጣ ፈተሸና የያዝኳቸውን መጻሕፍት አስቀርቶ እንድወጣ

አደረገ:: የሚገርመው ነገር መጸህፍት የሚገቡት አስፈላጊው ምርመራ ተደርጎባቸው ሲሆን ወደ ሆስፒታል ለመተኛትም ሆነ ለዕለታዊ ህክምና ስንሄድ ለምን እንደምንከለከል አይገባኝም:: ስለዚህም፣ እኔም አልተከራከርኩም ሊሸኙኝ ለመጡ ጓደኞቼ ተመላሽ መጸህፍትን ሰጥቼ ወደ ቀረበልኝ መኪና ገባሁ::

ሆስፒታል ስንደርስ ሃኪሙ አስፈላጊውን ዶኩሜንት ለፖሊስ ሰጥቶ ወደ ሁለተኛ ፎቅ ወስዶ እንድተኛ አዘዘ:: ወደተባለው ሁለተኛ ፎቅ ከመወሰዴ በፊት አንድ የፌዴራል ፖሊስ አባልና ይዞኝ የሄደው ባለስልጣን እኔን ከሊፍቱ አጠገብ ከፖሊሶች ጋር ትተውኝ ሄዱ:: ጥቂት ቆይተው ተመለሱና የፌዴራል ፖሊሱ ሲቀር ሃላፊውና አጃቢዎቼ ይዘውኝ ሁለተኛ ፎቅ፣ ሌሎች እስረኞች እተኙበት ክፍል አስገብተው ከነርሷ ጋር አገናኝተውኝ ተረኛ ከሆኑ ጠባቂ ፖሊሶች ጋር ተፈራርመው ተረካክበውኝ ተለያየን:: ነርሷ የሚመችውን አልጋና ቦታ መርጣ አዘጋጅታ ስለነበር በታላቅ አክብሮትና እንክብካቤ አስተናገደችኝ የሚያስፈልገኝ ነገር ሲኖርም እንድጠይቃት ነግራኝ ወደስራዋ ሄደች::

በክፍሉ ውስጥ ሁለት በሽተኛ እስረኞች አሉ:: አንዱ ባለፈው በወህኒ ቤቱ ተፈጥሮ በነበረው ግርግር እግሩን በጥይት ተመቶ የተኛ "ሻምበል" የሚባል፣ መንቀሳቀስ የማይችል ሲሆን ሌላው ከቀይ ሽብር ተፋራጆች የመጣ እዚያው ግቢ ያወቅሁት ጌታሁን የሚባል ነው::ነርሷ ከሄደች በኋላ ጌታሁን እቃዬን በማደራጀት፣ ሌላም ሌላም በማድረግ በጣም ረዳኝ::ጌታሁን ጨዋታ ያውቃል፣ የሱ በዚያ ክፍል መኖር በጣም ረድቶኛል::በቀዶ ጥገናም ጊዜ «አለሁልህ አታስብ» ይለኝ ነበር፣ ገና ቀኑም ሳይወሰን:: ነርሷ ውሃ መያዣና ቆሻሻ መጣያ ቅርጫት ይዛልኝ ስትመጣ « እባክሽ ለቤተሰቦቼ መተኛቴን ንገሪልኝ ብዬ ስልክ ነገርኳት ምንም ሳታቅማማ ወዲያው ወጣች::ጌታሁን ስለነርሷ ጥሩነት ነገረኝ:: ወዲያው ተመልሳ «ሰምተው ምሳ ይዘው እየመጡ ነው፣ ሲመጡ ይሄን ስጣቸው» ብላ ዶክተሩ የፈረመበት መግቢያ ካርድ ሰጠችኝ::



ትንሽ እንደቆየሁ ሁለት ዶክተሮችና ነርሶች መጥተው ጤንነቴን ከመረመሩ በኋላ የሚደረገው ቀዶ ጥገና ቀላል እንደሆነና እንዳላስብ ነግረውኝ፣ ስለሌሎቹም የቅንጅት ሰዎች ጠይቀውኝ፣ እንዲያውም አንደኛው ሃኪም የያዘውን ታይም መጽሔት ትቶልኝ ሄዱ:: እግዜር ይስጠው፤ ቢያንስ አጫዋቼ ጌታሁን ሲደክመው የማነበው አገኘሁ::

ወደ አራት ሰአት ላይ ሲሆን ወደመተኛው ክፍል ከገባሁ አንድ ሰአት በኋላ ቤተሰቤ ምሳ ይዞ መጣ:: በር ላይ ያሉት ጥበቃዎች "ብቅ በል" ብለው አገናኙን:: የመጡት ባለቤቴና ልጆቼ ነበሩ:: መሳሳም ተፈቀደና ተሳስመን፣ ሰላምታ ተለዋውጠን፣ የቀዶ ጥገናው ቀን እንዳልተወሰነ ነግሬያቸው የመግቢያውን ካርድ ሰጥቼያቸው ከቀትር በኋላ እራት ይዘው እንደሚመጡ ነግረውኝ ተሰነባበትን:: ይዘውት የመጡት ለምሳም ለእራትም የሚበቃ ቢሆንም እኔም መምጣታቸውን ስለምፈልገው አልተቃወምኩም:: እንደሚያደክማቸው አውቃለሁ፣ ቢሆንም ናፍቆቴን ባልወጣም ያጣሁትን በየቀኑ መተያየት ማግኘት ለእኔ ለታሣሪው ቀላል አይደለም::

የተሰጠኝን እድል በመጠቀም ከቤተሰቦቼ ጋር ተጫወትን:: ምን እንደሚያስፈልገኝ ጠይቀውኝ ምንም እንዳልጎደለብኝ «እድሜ ለናንተ እንጂ እኔ ምን ጎድሎብኝ ያውቃል? ይሄው ትመላለሳላችሁ፣ እናንተን አደከምኩ አስጨነቅሁ.. .. .. » ብዬ ንግግሬን ሳልጨርስ « እኛ ምንም ችግር ወይም መጉላላት የሚሉት አልደረሰብንም:: አኛም ትንሽ ትንሽ መቅመስ አለብን እኮ የናንተ ብቻ አይደለም:: ሁለተኛ እንዲህ እንዳትል፣ እንደዚህም እንዳታስብ» ብለው የበለጠ አበረታቱኝ የልብ ልብ ሰጡኝ:: ጊዜውም ስለመሸና የጥበቃ አባላቱም ሲበዛ ዳግመኛ ላይፈቅዱልኝ ይችላሉ በሚል ስሜት እኔም፣ ቤተሰቤም ተግባብተን ተሰነባብተን ተለያየን::

የጀርመን ሬዲዮ ሰአት ስለደረሰ ጌታሁን ሬዲዮኑን በጆሮ ማዳመጫ ከፍቶ ሲያዳምጥ እኔም ጆሮዬ ላይ ሰክቼ ለማዳመጥ ስዘጋጅ፣ ከጠባቂዎቻችን

እንዱ፣ ያውም «ጠርናፊ» የሆነው ወደ ክፍላችን ገብቶ "ምነው ሬዲዮኑን ለብቻችሁ ያዛችሁት?" በማለቱ ጌታሁን ሬዲዮኑን ከጆሮ ማዳመጫው አላቀቀውና ለሁሉም ሆነ:: በዚህም ሬዲዮ ማዳመጥ አለመከልከሉን ተረዳሁ

የቀን ተረኞች የነበሩት ነርሶችና ረዳቶቻቸው፤የጤና ረዳቶች፤ የምግብ አቅራቢዎችና ሌሎችም ለምሽት ተረኞች አስረክበው መውጣታቸው ስለሆነ መጥተው ተሰናብተውን፣ ከምሽት ተረኞች ነርሶች ጋር አስተዋውቀውን ተለያየን፤ የምሽት ተረኞችም አስፈላጊውን የትኩሳት፣ የደም፣ የልብ ምትና ሌላውንም ምርመራ ካደረጉልን በኋላ ስንፈልጋቸው እንድንጠራቸው አሳስበውን ሄዱ::

የጀርመን ድምጽ ስለ ቅንጅት አመራሮችና አባላት መታሰር አግባብ አለመሆን፤ ገዢው ፓርቲ በጉልበት ያደረገው መሆኑን ነበር የሚያስተላልፈው:: ቃለ መጠየቁ ሁሉ በዚሁ ላይ የተመሰረተ፤ የሕዝብ አስተያየቱ ሁሉ ይህንኑ የሚደግፍ ነበር:: ከማዳመጥ ውጪ ማንም ምንም አስተያየት አይሰጥም ነበር:: ፊት ለፊት ባለው ክፍል ውስጥ ያሉት ታካሚዎችና የአንዳንዶቹ አስታማሚዎቻቸው ይታዩኛል:: ሬዲዮኑን እየሰሙ በአጋጣሚው አይን ላይን ከተያየን የቅንጅትን የምርጫ ምልክት እያሳዩኝ ያበረታቱኛል:: እኔ ደሞ አጠገቤ ጠባቂዎች ስላሉ እንዳያዩዋቸው ስለምሰጋ ወደነሱ ከማየት ለመቆጠብ ብሞክርም አልፎ አልፎ ቀና ማለቴ አልቀረም:: ሬዲዮ እየሰማን ቡና ቀድቼ ለራሴም ያዝኩ ለ«ጠርናፊውም» ሰጠሁት:: ተቀበለኝና ቡና ካለ ለነሱም ብትሰጣቸው አለኝ ቀስ ብሎ:: ውጪ ላሉት ጠባቂ ፖሊሶች ማለቱ ነበርና ቀድቼ ሰጠኋቸው:: ከምስጋና ጋር ተቀበሉኝ፣ ሳቅ ይዟቸዋል:: በኋላ የሳቁበትን ምክንያት ሲነግሩኝ ለካስ ጠርናፊያቸው ለነሱም ያለው ብቻውን መጠጣቱ እንዳያስገመግመው አስቦ ነው::

የእራት ሰአት ሲደርስ ከመጣው ምግብና ቀንም ከተረፈው ላይ በጥበቃም ላይ ላሉት ሁለት ፖሊሶች፤



ለጌታሁንና ለሻምበል፤ ለራሴም ከተከፋፈልን በኋላም ብዙ ተርፎናል:: ምን እናድርገው? ቀን በርካታ ፖሊሶች ባሳቻ መንገድ እየመጡ ሰላም ብለውኝ፣ አበረታተውኝ ሄደዋልና ምናልባት ከመሸ በኋላ ይመጡ እንደሁ ጌታሁንን ስጠይቀው «የአሜሪካ ድምጽን ሬዲዮ የሚሰሙት እኔጋ እየመጡ ስለሆነ ይመጣሉ» ስላለኝ ከዳድነን አስቀመጥነው::

ቀጥሎ የሚሰማው የትንሳኤ ሬዲዮ የሚጀምረው በአንድ ሰአት በመሆኑ በመካከሉ የአንድ ሰአት ልዩነት አለ:: እስከዚያ ድረስ የግል ጨዋታችንን ከሻምበልና ከጌታሁን ጋር ያዝን:: ሻምበል ብዙ አይናገርም፤ አንድ ጊዜ ጨዋታ ከጀመረ ግን ያውቅበታል:: ፊት ለፊት ካለው ክፍል አንዲት ዘመዷን የምታስታምም ልጅ እሱንም እንደምታስታምመው እየነገረኝ ሳለ፣ የተባለችው ልጅ «ሻምበልዬ» ብላ ገባች:: እውነትም በፍቅር ይሁን በእህትነት በጣም ታስብለታለች:: "ካልበ-ላህ እኮ አይገጥምም ስብራት የሚገጥመው ሲበሉበት ነው እንጂ ሲተኙበት አይደለም» እያለች ይዛለት የመጣችውን ብርቱካን ታጎርሰዋለች:: ጌታሁን በጨዋታ መልክ "ምነው ልጂ ለሱ ብቻ?" ሲላት፣ "እናንተ ምን ጎሎባችሁ፣ ቤተሰባችሁ ያለችግር ያመጣል፣ እሱ ምን ዘመድ አለው? ለራሱ የሰው ሃገር ሰው፤ እያለች ብርቱካኑን ባፍ ባፉ ስትል፣ ጠርናፊው ፖሊስ "አይበ-ቃም! አንቺ ልጅ" ሲላት "እሺ" ብላ ጥላ ወጣች::ሻምበል እንደማፈር ብሏል:: ጌታሁን ደሞ አልተወውም፤ ቆይ ይንጋ ያቺ ስትመጣ አወራብሃለሁ ይለዋል ሻምበል ሆ ሆይ ይላል እያፈረ::

የትንሳኤ ሬዲዮ ሰአት ደርሶ ስንከፍተው ጠርናፊው ብቻ ሳይሆን ሌላ ጠባቂ ፖሊስም አብረው ገቡ፤ አንዱ ብቻ ውጪ ይጠብቃል:: አሁንም እንደቅድሙ ዝም ብሎ ማዳመጥ ነው፣ አስተያየት መስጠት የለም:: በዚህኛው የሬዲዮ ስርጭት ብዙ ሃተታ ይቀርባል ስለምርጫው መጭበርበር፤ ስለነበረው ሕገወጥነት፤ ስለ ቅንጅቶች መታሰር፤ ስለግድያው፤ በዝርዝር እየተነሳ ይወራል:: በጎዳና ላይ ስለተገደሉት

ሲወራ ጠርናፊው ሳያውቀው «የት ነበር? ያየ አይመስልም?» አለ፡፡ እኔ ጣልቃ ገባሁና «አሁን እኮ ሚስጢር የሚባል ነገር የለም፤ ቴክኒዮሎጂ ሁሉንም ነገር አቅልሎታል፡፡ በሳታላይት ወዲያው ነው በዓለም ላይ የሚሰራጨው» ስለው መልስ አልሰጠኝም፡፡ ይልቅስ ሌላኛው ፖሊስ፣ "አላየህም፣ ሚያዝያ 29 የነበረውን ሰልፍ፣ ወዲያው ማታ ቢቢሲ ሲያሳየው" አለው፡፡ ክርክሩ እዚህ ላይ ቆመ፡፡

የትንሳኤ ሬዲዮ ችግሩ ዜናውና የዜና ትንታኔው ልዩነት የለውም፡፡ ለአንድ ዜና 5 ደቂቃ ስለሚሰጡ የዜናው ጭብጥ ብዙ ጊዜ ይጠፋል፡፡ ያንኑ እያዳመጥን እስከመጨረሻው ቆየንና ሲያልቅ ሁለት ሰአት ላይ ሁሉም ወደየቦታው ተመለሰ፡፡ ምናልባት ዳግም የምንገናኘው፣ ከአንድ ሰአት በኋላ በአሜሪካ ድምጽ ሊሆን ይችላል፡፡ በተረፈችው ሰአት ሁላችንም በየግላችን በየአልጋችን በየህልማችን፣ በየሃሳባችን ተሰማራን፡፡ እኔ ከሄድኩበት የሃሳብ የተመለስኩት ነርሷ መጥታ፣ ለተነገ ወዲያ መዘጋጀት አልብህ ስትለኝ ነው፡፡ ሆድ መታጠብ፣ ከማታው 12 ሰአት ጀምሮ ከምግብ ጋር ጨርሶ መለያየት እንዳለብኝ ስትነግረኝ ነው፡፡ ቁርጥ ሆኗል አልኩና ለክፉም ለደጉም ለቤተሰቤም መንገር አለብኝ አልኩ በሃሳቤ፡፡

ሶስት ሰአት ላይ የአሜሪካን ድምጽን ከጠባቂዎቻችን ጋር አብረን ሰማን፡፡ አሁን ጠያቂ ስለማይመጣና ስለመሸ ሁሉም ወደ ውስጥ ገብተው ነበር የሚያዳምጡት፡፡ ጣቢያው እንደጀመረ ቀን ደበቅ ብለው ከጠየቁኝ የፖሊስ አባላት መሃል 3ቱ መጡ፡፡ ሬዲዮኑን እየሰሙ ጌታሁን እራት ጋበዛቸው፣ አልተገደረደሩም፣ በሉና ቡናም ጠጣን፡፡ ፕሮግራሙንም አዳምጠን ማንም ምንም ሳይል ተለያየን፡፡

ያን ምሽት እኔ፣ ጌታሁንና ሻምበል በመጡኑ ስለነበረው ሁኔታና የተደበላለቀ የፖሊሶቹ ስሜት አወራን፡፡ "የያዘ ይዟቸው ነው እንጂ ሁሉም ቅንጅት ናቸው" አለ ጌታሁን፡፡ እኔም ካየሁት በመነሳት ይህን



ሃሳቡን እጋራዋለሁ፡፡ በዚህ እየተገረምን ሌሎች አጋጣሚዎችን እያወራን ሳለ፣ ጌታሁን "በል እንግዲህ አንድ ቀልድ ጣልብንና እየሳቅን እንተኛ" አለኝ፡፡ ለጌታሁን ቀልድ አልነገርኩትም ቀልድ ከየት ላምጣ መች ዘመኑ የሚቀለድበት ነውና! አሁንስ ያለንበት ሁኔታ ለቀልድ ያመቻል ብለህ ነው ጌቱ ስለው እውነትክን ነው ጋሽ ደቤ፣ የቀልድ ሳይሆን የግድ ጊዜ ነው ብሎ አሳቀኝ፡፡ እውነቱን ነው ሁሉም ነገር በግድ ነው የሚከናወነው ምንም በህግና በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ፤ ወይም በዴሞክራሲያዊነት ላይ ተመሥርቶ የሚከናወን ጉዳይ የለም፡፡

ተኛን፡፡ ጠዋት ነጋ አልነጋ ብለው ቤተሰቦቼ መጡ፡፡የነሱ መንከራተት፤ ድካም፤ በጣም ቢያሳስበኝም እኛ ምንም የሚያሳስብ ነገር የለብንም ያንተ ደህንነትና ጤንነት ነው ዋናው ነገር.. .. .. ስለአሉኝ አውጥቼ አልናገረውም እንጂ በመጡ ቁጥር ይከብደኛል፡፡

ስለተወሰነው የቀዶ ጥገና ነገርኳቸው፤ማታም እራት እንዳያመጡልኝና ለተከታይ ሁለት ቀናትም ፈሳሽ ብቻ እንደምመገብ ነገርኩ፡፡ አልሚም "አንተስ እሺ እነሱስ አሉ አይደለም? ስለዚህ ማታም እንመጣለን " አለችኝ፡፡ ቤተሰቤ የመጣው ማታ ያደሩት ሳይለወጡ ስለሆነ ተለማምደናልና በመዝናናት ነበር ግንኙነታችን፡፡ የሚለወጥ አንሶላ፣ ፒጃማ ይዘውልኝ መጥተዋል፡፡ ሳልነግራቸው የሚያስፈልገኝን ቀድመው ነው የሚያውቁት፡፡

ጥቂት ቆይተው ማታ እንገናኝ ብለው ያደረውን የስንቅ እቃ ይዘው ሄዱ፡፡ በጠዋት የመጣውን ቁርስና ቡና ከአዳሪ ጠባቂዎቻችን ጋር ተቃምሰን እነሱም ለአዲስ ገቢዎች አስረክበውን "እስክምንገናኝ" ብለው ተለያየን፡፡ ቀን ላይ የማላውቃቸው ግን እዚያ መተኛቴን የሰሙ ከየክፍሉ እየመጡ ጠየቁኝ፡፡ በጣም ብዙ ስለነበሩ ለጠባቂዎቹ አዲስ ነገር ሆነባቸው፡፡ በጣም ያስገረማቸው ደሞ አንድም ጠያቂ ባዶ እጁን የሚመጣ የለም ኬኩ፤

ውሃው፤ ለስላሳው፤ ፍራፍሬው፤ አበባው፤ ምኑ ቅጡ? በጣም የበዛ ጠያቂ ነበር።

አንዲት በእድሜ ጠና ያሉ እመቤት መቋሚያቸውን ይዘው አንድ ጎረምሳ አስከትለው መጡና ፖሊስ ጠባቂዎችን «እባካችሁ ገብቼ ግምባሩን ልሳመው» አሉ። እግዜር ይስጣቸው ፈቀዱላቸውና ምንም ሳይሉ ገብተው ግንባሬን ሳሙና «አበጀህ! ፈጣሪ ከናንተ ጋር ነው፤ ምንም አይመጣባችሁም፤ ለራሳችሁ ብላችሁ ሳይሆን ለሕዝብ ብላችሁ ነው፣ አይዞህ» ሲሉ ፖሊሶቹ እማማ ይበቃል ይውጡ አሏቸው። ወደ ፖሊሶቹ ጠጋ ብለው «ለኔም ለናንተም ነው እነሱ ምን ጎደለባቸው?» ብለው «ለነገሩ እናንተንም ፈጣሪ ይባርካችሁ» አሉና ሄዱ። መቼም አልረሳውም ሁኔታቸውን፤ ትልቅ ትልቅ የመንፈስ ደስታ ነው ያሳደሩብኝ።

ማታ ቤተሰቦቼ ፈሳሽ ምግብ ይዘውልኝ መጡና "አይዞህ ብለው አበረታተው ጠዋት ቀደም ብለው እንደሚመጡ ነግረውኝ፣ "ስትነቃ የምታየው እኛን ነው" ብለው አበረታተውኝ ተጫዋውተን ሄዱ። ይገባኛል፣ ቤተሰቤ እንቅልፍ አጥቶ ስለኔ የነገ ሁኔታ ሲያስብ ነው የሚያድረው። ከኔ ይበልጥ ለኔ የሚጨነቅ ቤተሰብ እንዳለኝ ስለማውቅ የሚሰማቸውን መገመት አያስቸግረኝም። ማታ ነርሷ በገባቸው ቃል መሰረት የሚያስፈልጋትን ቁሳቁስ ይዛ መጥታ ሆዴን አጠበችኝ። ገላዬን እንድታጠብ የመታጠቢያ ክፍሉን ቁልፍ ሰጠችኝ፤ በቃ የእራት ጉዳይ ብላ ተለያየን።

ሌሊት ትንሽም ቢሆን ማሰቤ አልቀረም።እርግጥ ከትርፍ አንጀት ጀምሮ የሸርኒያም፣ የጀርባ አጥንትም ማስተካከል አድረጊያለሁ ሁሉንም ታዲያ ከኢትዮጵያ ውጪ ነው ያደረግሁት። ያም ሆኖ አሁን ትንሽም ቢሆን መፍራት ማሰብ አልተወኝም ደግነቱ ወዲያው እንቅልፍ ይዞኝ ሄደ። የነቃሁት አዳሪው ወንድ ነርስ መጥቶ "ጋሽ ደቤ፣ እንግዲህ ወደ ቁራ መሄዳችን ነው፣ ተዘጋጅ" ሲለኝ ነው። ያን ቃል ለሰው ሲባል



አልወደውም። ቁራ ከብቶች ገብተው አይወጡም የመጨረሻቸው ነው። ታዲያ ለምንድን ነው ይህን የቀዶ ጥገና የማይሉት? በተለምዶ ቁራ ሲሉት ይቀፈኛል።

ቁራም ተባለ ቀዶ ጥገና ወደ ማይቀረው የእለቱ ፕሮግራም መሄዴ አልቀረም።ለመውሰድ የተመደበው ነርስ ለዚያ የሚሆነውን ጋውን የመሰለ አረንጓዴ ልብስ አልብሶኝ ይዞኝ ሄደ። በቦታው ስደርስ ከሶስት የማያንሱ ዶክተሮች፣ በርከት ያሉ ነርሶች ነበሩ። ሰላም ካሉኝና ስለክሳችን ሁኔታ ካዋሩኝ በኋላ፣ አንደኛው "እኔ የአኒስቴዚያ (የማደንዘዣ) ባለሙያ ነኝ አደንዝዤህ ነው ቀዶ ጥገናው የሚሰራልህ፣ ብሎ አንዳንድ ነገሮችን ከጠየቀኝ በኋላ አልጋው ላይ አስተኝተውኝ ማደንዘዣውን ሰጡኝ። ያወሩኛል፣ "እንዴት ነው? ምን ይሰማሃል? በል እንጂ አጫውተን?" እያሉኝ ድብልቅልቁ የወጣ ሃገር የገባሁ ይመስለኛል ሰው አይሏቸው አውሬዎች ይታዩኛል። ድንብርብሩ የወጣ ቅዠት ይመስለኛል። በዚያው ጭልጥ፣ አልሰማ አልለማ ዥው አርጎ ወደሚወስደኝ ወሰደኝ። ስነቃ መጀመሪያ የጠራሁት የባለቤቴን የአልሚን ስም እንደሆነ በዚያ የነበረች ነርስ ነግራኛለች። የማስታውሰው አንድ ከላይ ሲጠብቀኝ የነበረ በቃሊቲም የማውቀው ደህና ከምላቸው ፖሊሶች አንዱ አጠገቤ ጠመንጃውን እንደያዘ ቆሟል፣ መናገር አልቻልኩም ግን አየሁት።

ደሞ እንቅልፍ ወስዶኝ እንደገና ስነቃ ሽንት ወጥሮኝ ግን አልወጣልህ ስላለኝ ለፖሊሱ ነገርኩትና ነርሶች ጠርቶልኝ ካትኢተር ተደርጎልኝ ተነፈስኩ። ወደክፍሌ ሲወስዱኝ አልሚንና ሌሎችንም ሰዎች አየሁ። ግን ከአልሚ በቀር ማንንም አልለየሁም። ክፍሌ እንደገባሁ እንደገና እንቅልፍ ወሰደኝ። ቤተሰቤ በእርግጠኛነት ሃኪሞቹንም አነጋግረው እኔንም አይተው እፎይ፤ተመስጌን እንዳሉ እርግጠኛ ነኝ።ክፍል ከገባሁ በኋላ ለረጂም ጊዜ እንቅልፍ ወስዶኛል አሁን ስነቃ ውሃ ጥም አቃጥሎኛል። ነርሷን አስጠርቼ "ውሃ አጠጪኝ" ብላት ከንፈሬን ፊቴን ግንባሬን በውሃ ጠራርጋልኝ ሲያምርህ ይቅር እንደማለት «ይሄው ነው ዛሬ የሚፈቀደው» አለችኝ።

ሙሉ ቀን እንቅልፍ እየወሰደ ሲመልሰኝ ዋለ::ከቀትር በኋላም አልሚ መጥታ ለፖሊሶቹ እግዜር ይስጣቸው ፈቅደውላት አይታኝ "አይዞህ" ብላኝ አጫውታኝ ሄደች እግሯ እንደወጣ ወዲያው እንቅልፍ ይዞኝ ሄዶ እንደገና የነቃሁት በርከት ያሉ የሆስፒታሉ ሠራተኞች ነርሶችና ሃኪሞች መጥተው ሲያነጋግሩኝ ነው:: አሁንም እንደትላንትናው በርካታ ሰዎች እየመጡ ከበሩ ላይ በመቆም የያዙትን ለጌታሁን እያስረከቡ ሰላም ብለውኝና ጠይቀውኝ፣ ጤንነት ተመኝተውልኝ ይሄዳሉ::

ማታም ነርሶቹ እየተመላለሱ እያዩኝ፣ ቤተሰቤም ማታ ገደማ መጥተው እንደገና አይተውኝ፣ እኔም በመምጣታቸው ተበራትቼና ተደስቼ፣ ለቀኑ ያለኝን ጨርሼ እስከ ጠዋት እንቅልፍ ይዞኝ ነጎደ::

በማግስቱ ስነቃ ቀዶ ጥገናውን ያደረገልኝ ዶ/ር ግርማ አልጋዬ አጠገብ ቆሞ፣ "ታዲያስ አቶ ደበበ! እየበረታህ ነው?" ብሎ ቁስሉን አይቶ "ጥሩ ነው" ብሎኝ ሄደ:: እሱን ተከትሎ የእለቱ ተረኛ ሃኪም መጥቶ የነርሶቹን ሪፖርት አይቶ በርታ ጥሩ ነው ብሎኝ ሄደ፤ ወዲያው እነ አልሚ ቁርስ ይዘውልኝ መጡና አጥሚት ውሃነትም ስላለው ለውሃ ጥሙም" ለረሃቡም ጥሩ ነው ብለውኝና አዳሬን ጠይቀውኝ ሲያጫውቱኝ ቆይተው ተመልሰው ሄዱ::

ሁለተኛ ፎቅ ባሉት ጠባየ ሸጋ ነርሶችና ሌሎች የሆስፒታሉ አባላት በቤተሰቤ ድጋፍ እንክብካቤ፣ በማውቃቸውና በማላውቃቸው ጠያቂዎች አይዞህ ባይነት፣ በጌታሁን አስታማሚነት፣ በሻምበል ጠያቂነት 15 ቀናት ተኝቼ ጤነኛ ሆኜ ለክትትል ምርመራ ቀጠሮ ተቀብዬ በቀጣይ ፊዚዮ ኖራፒ ታዞልኝ ወደ ቃሊቲ እሥር ቤት ተመለስኩ:: ከሆስፒታል ወደቃሊቲ ስሄድ ከነጌታሁን መለየቱ በጣም ነበር ቅር ያለኝ፣ ለምደውኝ ለምጃቸው ጥሩ ባልደረቦች ሆነን ነበር:: በተለይ ሻምበል እየቆየሁ ስሄድ ሚስጥረኛው አድርጎኝ ነበርና ስሄድ በጣም ቅሬታ ተሰምቶት "ጋሽ ደቤ ቀድመውኝ ከወጡ



አሉበት ድረስ ስፈታ እመጣለሁ' እንዳይረሱኝ" ብሎኝ ነበር ግን እሱ ነው ቀድሞኝ የወጣው::

ፖሊስ ሆስፒታልን መልቀቁ ቅሬታ የፈጠረብኝ ከቤተሰቤ ጋር በየቀኑ መገናኘትም ስለሚቀርብኝ ነው::ቤተሰብን በየቀኑ ማግኘትና ከነሱ ጋር ጥቂትም ቢሆን ማውራት ትልቅ እድል ነው::

ቃሊቲ ስደርስ፣ ቀደም ብዬ በነበርኩበት ክፍል ውስጥ ታችኛው አልጋ ላይ ቦታ ስላልተገኘ ዶ/ር በፈቃዱ ወዳለበት ቀጥሎ ወዳለው ክፍል ቦታ አዘጋጅቶልኝ ኖሮ እዚያ ገባሁ:: ሁለቱ ክፍል ጎን ለጎን ስለሆነ ቀደም ብዬ ስለማውቃቸው እንግድነት አልተሰማኝም:: "እንኳን ደህና መጣህ" ባዩ የግቢው ሰው በሙሉ ነው::ጋባዡም ሁሉም ነበር:: ከሆስፒታል ወጥቼ ከጥቂት ቀናት በኋላ የታዘዘልኝን ፊዚዮ ቴራፒ ለማድረግ ወደ ፖሊስ ሆስታል ሄጄ ቅድሚያ ተሰጥቶኝ ወደመታሻው ክፍል ገብቼ በመታሸት ላይ እያለሁ አንዲት ወረፋ የሚጠብቁ ታካሚ ስለሞተ ሰው ሳልስት ያወራሉ በሞባይል ድንገት የታላቅ ወንድሜ ስም ጆሮዬ ጥልቅ አለ::ደነገጥኩ ሴትዮዋ አላወቁም ለካ የወንድሜ ሰልስት ነው የሚወራው ሰውነቴን ሁሉ ወረረኝ በቃኝ አልኩት የሚያሸኝን ሰውና ለባብሼ ወደ ቃሊቲ ውሰዱኝ ብዬ ሄድኩ ማንም አላወቀም:: እንባዬን ቋጥሬ ክፍሌ ገብቼ ተሸፋፍኜ ብቻዬን የወንድሜን ሞት ድንገት ተረድቼ አለቀስኩ::መታመሙን አውቃለሁ ግን ለዚህ ይደርሳል ብዬ አልጠረጠርኩም ነበር::ለካስ ለወህኒ አስተዳደር ተነግሮ ቅዳሜና እሁድ ሊነግሩኝ ነበር የሚጠበቀው::ሰማሁትና በእስር ላይ ለቅሶ እንደማያምር ተረዳሁ:: በቅድሚያ ዶ/ር በፈቃዱ ሰምቶ ከኔ ጋር አብሮ ተሸማቀቀ:: አዘነ:: ለወንድሜም ለኔም አዘነ::ወዲያው ሁሉም ሰምተው አስተዛዘኑኝ::የቃሊቲ አስተዳደር ወንድሜ እንዳረፈ ተነግሯቸው ለቀብር ባይፈቅዱልኝም ቅዳሜ እንድረዳ ለዞን አስተዳዳሪዎች ተነግሮ ነበር ቀድሜ አንጉል ሰማሁት እንጂ:: እኔ ሐሙስ ሰምቼ ቅዳሜ ቤተሰቤ ሲመጣ ምስጋና ይድረሳቸው የቃሊቲ ሃላፊዎች ክፍል አዘጋጅተው ቤተሰቤ ጋር አገናኙተውኝ ተላቅሰን ትንሽ ወጣልኝ::

አይጠቅምምና ሃዘኔን በአጭር አደረግሁት።በአሥር ላይ ለቅሶ ያውም የቅርብ ሰው ለቅሶ አያድርስ ነው።በቃሊቲ ያሉ ታሳሪዎች እንደጦር የነሚፈሩትና የሚጠሉት ነገር ቢኖር መርዶ ነው።አንዳንዶች ለቀብር እንዲሄዱ ይፈቀድላቸዋል ሌሎች አይሄዱም እኔም ከማይሄዱትና ቀብር ከማይፈቀድላቸው አንዱ ሆኜ እንጂ ቤተሰቤ በወቅቱ ጠይቆ ነበር።ሃዘኔን በዚህ አለፍኩት። የፍርድ ቤት ቀጠሮችን ደረሰና ለመጀመሪያ ጊዜ ከቃሊቲ ወደ ስድስት ኪሎ ፍርድ ቤት ለመሄድ ተዘጋጁ የተባልነው ሌሊት ሳይነጋ በ10 ሰአት ተኩል ነበር።በትእዛዙ መሰረት ተዘጋጅተን ስንጠብቅ 11 ተኩል እስኪሆን ድረስ ማንም አልመጣም። 11:30 ሲሆን መኪና ቀረበ፤ የሥጋ መጫኛ የሚመስለው የታሳሪዎች መኪና፤ ከማደሪያ ግቢያችን እየወጣን ተፈትሸን ብርድ እያንዘፈዘፈን ገሚሱ ቆሞ ገሚሱም ተቀምጦ መኪናው እየነጠረና እየተቀጠቀጠ በየጉራንጉሩ ተጉዘን ስድስት ኪሎ ደረስን። በዚያ ጠዋት መንገዱ ሁሉ ፖሊስና ወታደር ብቻ ነበር። አሳቻ በሆነ መንገድ መሄድ ለምን እንዳስፈለገ አሁን ድረስ ያልገባኝ ጉዳይ ነው።

ለነገሩ ቢሮዎች የሚከፈቱበት ሰአት እየታወቀ በ12 ሰአት ተኩል ፍርድ ቤቱ ግቢ ውስጥ ወስዶ ብርድ ላይ መጎለቱ ከቅጣቱ አንዱ አካል ይሆን? ወይስ የፍርሃት ምልክት በስድስት ኪሎ ፍ/ቤት ደርሰን የተቆላለፈውን እግራችንን ለማፍታታት ብንጠይቅም፣ ቦታው አመቺ አይደለም ስለተባልን ከመቀመጡና ከመተሳሰሩ፣ ከመደንዘዙ፣ ለመገላገል "ለሽንት ውሰዱን" በማለት በአራት በአራት እየተከፈልን መሄድ ጀመርን። መሄድ መመለሱ ብዙም ስለማያንቀሳቅስ ያለን አንዱ ዘዴ፣ አንድ ሰው መጸዳጃ ቤት ገብቶ ረዘም ያለ ጊዜ በመውሰድ ሌሎች በዚያችው ባለችው ጠባብ ቦታ እንዲንቀሳቀሱ እድል መስጠት ነበር።

ከቃሊቲ ነጋ አልነጋ ብለው ይዘውን ስለወጡ ሻይ የሚባል ነገር አልቀመስንም።ሁላችንም ግን ደረቅ «መኖ» ይዘናል። ያንኑ ስንቆረጣጥም ሻይና ቡና እዘዙ ተብለን ታዘዝና ከዳቦ ጋር መጥቶ ሁሉም የፈለገውን ወሰደ። ሂሳቡን አልተጠየቅንም፣ ግብዣ ነው።



የፍርድ ቤቱን ሂደት ካየነው አኳያ የሚሰጠውን ፍርድ ከወዲሁ ስለተገነዘብን ጥቁር ለብሰን እንድንወጣ ተስማምተንና ወደ ፍርድ ቤትም ላለመሄድ ወስነን ነበር። በማስገደድ ወደ መኪና እንድንገባ ሲደረግ፣ የለበስነውንም ጥቁር ሸሚዝና ሹራብ እንድንለውጥ ታዘዝን፣የወንድሜ ሃዘን ነው ጥቁር መልበስ ደሞ መብን ነው ብል ከፍርድ ቤት መልስ ታዝናለህ ተባልኩና ተከለከልኩ። በካቴና እየታሰርን (ገሚሶቻችን)። በዚህ ሁኔታ ከቃሊቲ በቦሌ ቀለበት መንገድ አድርገን መሳሪያ በታጠቁ ፖሊሶች ታጅበን፣ በየመኪናው ቢያንስ ሁለት ነጭ ለባሽ ተካቶ፣ መንገዱ በተለመደው መልክ ተወጥሮ ወደ ስድስት ኪሎ ሄድን።

ዛሬም በፍርድ ቤቱ አካባቢ ያለው ሁኔታ ያው ነው፣ የተለወጠ ነገር ቢኖር አሁን ይዘውን የመጡት የቃሊቲ እስር ቤት ሃላፊዎች መሆናቸው ነው። በዕለቱ የፍርድ ቤት ውሎ ብዙም ሳይባል፣ አቃቤ ሕግ የክስ ሰነዱን ለሁሉም ተከሳሾች እንዲያደርስ፤ስለ ቦታ ለውጡም ቢሆን አቃቤ ሕግ በጠየቀው መሰረት ይሆናል የሚለውን ተለዋጭ ቦታ ለፍርድ ቤቱ እንዲያዘጋጅና እንደደረሰ ወደዚያው እንዲለወጥ በማለት ቀደም ሲሉ ለተነሱ ጥያቄቻችን አንድም የረባ ምላሽ ሳይሰጠን ሊዘጋ ሲል፣ ወ/ሪት ብርቱካን ተነሳች «ክቡር ፍርድ ቤት ቀደም ሲል የፍርድ ሂደቱ ሳይጀመር ጠቅላይ ሚኒስትሩ በግልጽ ባደባባይ የሞት ፍርድ የፈረዱብን ስለሆነና የሚለወጥም ፍርድ ባለመኖሩ ይሔው በወረቀት ተወስኖ ይላክልን» አለች። ዶ/ር ብርሃኑም

«ክቡር ፍርድ ቤት ዛሬ ወደዚህ ስንመጣ በካቴና ታስረን ነው የመጣነው። ይህንንስ ፍርድ ቤቱ አውቆ የፈቀደው ነው?» በማለት ሲያመለክት

«ዳኛ» ልዑል ገ/ማርያም በንዴት፣ "ምን ለማለት ነው ዶ/ር? ይህን የለበጣ ንግግር ምን አመጣው? እንዴት ይህን እንፈቅዳለን?» በማለት ተቁነጠነጡ።

ዶ/ር ብርሃኑም «ለበጣ አይደለም፣ የሆነውን ነው ያመለከትኩት። እኛ እኮ ይህ ፍርድ ቤት በአደራ ወደ ቃሊቲ እስር ቤት የላከን በመሆኑ ሁኔታዎችን አደራ ለሰጠን ለፍርድ ቤቱ ማቅረብ አለብን።ቀደም ሲልም የተወሰደ ንብረታችን ይመለስልን ብለን አመልክተን እስካሁን ምንም ምላሽ አላገኘንምና ንብረታችን

ሊመለስልን ይገባልና ይታዘዝልን በየጊዜው ፍተሻ እየተባለ ንብረትና የያዝናቸው ማስታወሻዎች ይወሰዱብናል ግን አይመለሱልንምና ፍርድ ቤቱ ይዘዝልን» በማለት አመለከተ።

የማረሚያ ቤቱም ተጠሪ "በማረሚያ ቤት የማይፈቀዱ እቃዎችን እንወስዳለን። ደሞም የምናስተናግደው ባለን አቅምና ቦታ ነው። በካቴና ስለመታሰራቸው ግን የማውቀው ነገር የለም" በማለት አስተባበለ።ይህ የመታሰራቸውን ነገር አላውቅም ያለው ሃላፊ ነበር ጠዋት ካቴና አስመጥቶ ይህን እሰረው ይህን ተወው እያለ ሲያስቸነክር የነበረው።ይሄው ቆሞ ያሳሰረን ሰው "አላውቅም" ሲል የሱ ቃል ተቀባይነት አግኝቶ ጉዳዩ መታለፉ የፍርዱን ሂደት ምንነት በሚገባ የሚጠቁም ነበር።እኔም ጥቁር ለብሼ ነበርና «ወንድሜ አርፎ ሃዘን ላይ ነኝ»ብልም ስትመለስ ትለብሰዋለህ አውልቅ ተብዬ አውልቄያለሁ። በዚህ ሁኔታ የእለቱ ፍርድ ቤት ተጠናቆ በመጣንበት መኪና ታጭቀን ወደ ቃሊቲ እሥር ቤት ተመለስን።

በዚህ እለት የወጣነው በፊት ለፊት ሳይሆን በጀርባ በር ነው። አቃቤ ሕግ ያቀረበው የፍርድ ቤቱም ቦታ ይለወጥ ለካ ዝም ብሎ የተነሳ አልነበረም። ከስድስት ኪሎ ፍርድ ቤት ስንወጣ አንበሳ ግቢ ፊት ለፊት የተሰበሰበው በርካታ ደጋፊያችን «መሪዎቻችንን ፍቱ፤ የግፍ አሥራት ይብቃ፤.. .. .. » በማለት ጩኸቱን ያሰማ ስለነበርና ይህን ለማስቀረት ወይም ከዚህ የሕዝብ ጥያቄ ለመሸሽ የተደረገ ዘዴ ነበር።ዛሬም እንደወትሮው በአሳቻ መንገዶች ተዘዋውረን ተመልሰን ቃሊቲያችን ገባን።

በቃሊቲ አብረውን በአንድ ግቢ ያሉት እሥረኞች ስንመለስ፣ "ይሆናል" ብለው ያሰቡት ነገር ባለመሆኑ ሁሉም ከኛ ባላነሰ መልኩ በፍርድ ቤቱ ላይ አዘኑ። ሲሆን ያን እለት ለሁሉም፣ አለያም ለከፊሉ የዋስ መብት ይፈቀዳል የሚል እሳቤ ነበራቸው። ባለመሆኑ ቢያዝኑም አይዟችሁ እያሉ ለማበረታታት ጥረዋል። በኛ በኩል ከዚህም የከፋ ነገር ሊያደርሱብን እንደሚችሉ ተገንዝበነዋል። ስለ ዴሞክራሲ፤ ስለሰብአዊ መብት፤ ስለእኩልነት፤ አንድነት፤ ሉአላዊነት እያነሳን ከወያኔ/ኢህአዴግ ጋር በዋዛ መላቀቅ እንደሌለማ



ገብቶናል። በዚህ የፍርድ ሂደት ቀኑ ቀን እየወለደ፣ ኢህአዴግም "በፍርድ ቤት ሥርአት ጣልቃ አልገባም" እያለ ግን መመርያ እየሰጠና በሚያመቸው መንገድ የፍርድ መስመር እየቀየሰ ዳኞች ነን ያሉትም መመሪያቸውን በየቀጠሮው ቀን እየተቀበሉ እንደሚመጡ ቀድመን ያወቅነው ነው።

አንድ ምሽት ድንገት በግቢው ተኩስ ተጀመረ፤ ማን ነው የሚተኩሰው ለምን ወዴት ምንም ያወቅነው ጉዳይ የለም። እኔ ደሞ ወደ መጸዳጃ ክፍል ሄጄ ሳልመለስ ነበርና ተኩሱ የተጀመረው በግቢው ውስጥ የነበረ ፖሊስ ወደ መታጠቢያ ቤት መጥቶ ስሜን ጠርቶ «እዚሁ ቆይ» ብሎኝ ኖአይዞህ በሩ ላይ እኔ አለሁ ተኩሱ እስኪቆም እዚሁ ቆይ. ብሎኝ አቆየኝ።ተኩሱ ጋብ ሲል «በል እንሂድ»ብሎ አብሮን በሬ ድረስ ሄድን።ወደ ክፍል ስገባ ሁሉም ደንግጠው ስለኔ ሲነጋገሩ ደረስኩ።እፎይታቸው ታየኝ፡ በኋላ ስንሰማ ተኩሱ እስረኞች ለማምለጥ ሲሞክሩ ነበር።ያመለጡም የተያዙም የተመቱም ነበሩ፡፡፡

ጥቂት የቅንጅት ሰዎች ከቀይ ሽብር ተፋራጆች በተለይም የደርግ አባላት ከነበሩት ጋር ቁጭ ብለው ሲወያዩ ታዩ። ወዲያው ወሬው ለዞን ሃላፊ ለተባሉት ደረሰና በጥድፊያ ውሳኔ ተደርሶ ወደ ማታ ግድም ድንገት ስማችን እየተጠራ ወጥተን ሳናስበው በድንገት በመኪና ተጫንን እቃችንም ተጫነ።ወዴት እንደምንሄድ ጨርሶ አልተነገረንም እኛም ወዴት ብለን አልጠየቅንም።በየመኪናው አድርገው ወስደው ከግቢ ሳንወጣ በተለያየ ዞን በታተኑን።

ከቀይ ሽብር ተፋራጆች ዞን ወጥተን ወደተለያዩ ዞኖች እንድንሄድ የተወሰነብን፣ አንደኛ በነሱና በኛ መሃል ምንም ግጭት በመጥፋቱ፣ ሁለተኛ በዚያ ግቢ ውስጥ የተሟላ አገልግሎት ተካፋዮች ስለሆንን ችግርን ይቅመሱት በሚል በሌላ በኩል ደሞ ምን እየተመካከሩ እንደሆነ ስለማይታወቅ ጤናማ አይሆንም መለያየት አለባቸው በሚል ይመስለኛል። በየዞኑ ስንበታተን ማንም በቀይሽብር ተፋራጆች ዞን የቀረ የለም። በተለያየ ዞን ነው የተበታተንነው። ስለዚህም እንደ አዲስ ጎጆ ወጪ ሆንን። ቤተሰቦቻችን በቀይ ሽብር ዞን እያለን የስንቅ አመጣጥ ወረፋ አውጥተንላቸው በየቀኑ

ከመመላለስ ድነው ነበር:: አሁን እንደገና እስክንቀናጅ ችግር ሊፈጠር ነውና በቶሎ አንድ ዘዴ መቀየስ ነበረብን:: የመጀመሪያው፣ አንድ የተቀናጀ የምግብ ማመላለሻ ተራ ማውጣትና ለቤተሰብ እንዲደርስ ማድረግ፣ ሁለተኛው ፍሪጅ ለማስገባት እንዲፈቀድልን መጠየቅ፣ ሶስተኛው ለፍሪጅ መግዣ ገንዘብ ከየግላችን ማሰባሰብ ነበር:: ይህን ወስነን ማመልከቻችንን አስገብተን ሳለን ምግቡ ከቤተሰባችን በየተራ እንዲገባ ለማድረግ ምንም ችግር አልገጠመንም አርብ ተዛውረን ቅዳሜ የቤተሰብ ግንኙነት ቀን ስለሆነ ወዲያው ለቤተሰቦቻችን የለውጡን ፕሮግራም ነገርናቸው ተስተካክለና ወዲያው ተግባራዊ ሆነ:: የፍሪጁና የቡና ማፍያው የምግብ ማሞቂያው ጥያቄ ጥቂት ቀን ቢወስድም በመጨረሻው ተፈቀደልንና ለመግዛት ዋጋ ጠይቁ ብለን ለቤተሰብ ስንልክ ልጄ ዮዲት ደበበ "ፍሪጁን እኔ አመጣለሁ" ብላ በግሏ ስጦታ ስላደረገችልን ወዲያው አስገባችልን:: የምግብ ማሞቂያውን፣ የነጭ ጋዝ ምድጃ የአቶ አባይነህ ቤተሰብ አመጣልንና ጎጂችን እየተሟላ ሄደ::ችግሩ ከሞላ ጎደል እየተስተካከለ እኛም ሁኔታውን እያሟላን ቀሪውን ጊዜ ለመቀጠል ተዘጋጀን::አሁን ባለንበትስ ቦታ ምን ያህል ያቆዩን ይሆን? ማን ያውቃል? ተነሱ እስኪሉን መጠበቅ ነው::

በዚህ ዞን ውስጥ ያለው ከፍተኛ ችግር የዓይጥ መንጋ በመሆኑ ሻለቃ አፈወርቅን ድመት እንዲያመጣልን ጠይቄው ከቀይ ሽብር ተፋራጆች ግቢ አንድ ድመት አመጣልኝና ቃሊቲ ብያት ማሰደግ ጀመርኩ::ከመጣችበት ቀን ጀምሮ እድሜዋ ሳይሆን ድምጧ ትንሽ ትንሽ አይጦችን አስፈራርቷል:: እየቆየች ትገላግለናለች::

## የቃሊቲ 2ኛ ወንጀል ችሎትና የሠነድና የሰው ምስክሮች ትርዒቶቹ

በ11/10/98 ለመጀመሪያ ጊዜ ቃሊቲ ባለው የሃገር ፍቅር ቴያትር ቤት ቅርንጫፍ አዳራሽ በተዘጋጀው ፍርድ ቤት ቀረብን::



እኔ ተሰይሜ ለሕበረተሰቡ ሙያዊ ቴአትር ጨዋታ የማቀርብበትን መድረክ ተነጥቄ ዛሬ እኔ ተመልካች ሆኜ ሳይሆን ተከሳሽ ሆኜ፤ቤቱም የተከበረ ቴያትር ቤት ሆኖ ሳይሆን ፍርድ ቤት ሆኖ በኔ ቦታም የተሰየሙት ተዋንያን ሆነው ሳይሆን ዳኞች ሆነው ሳያቸው እኔ በሌላ ቴያትር ቤት የቴያትር ትርኢት ላይ ሄጄ ያልተገሩ ተዋንያን ቴያትር ሲሰሩ የምመለከት እየመሰለኝ በመሰልቸት ለመውጣት ይዳዳኛል ወዲያው ሁኔታውን ሳገናዝብ ያለሁበት ትዝ ይለኝና ገርሞኝ አርፌ ቁጭ እላለሁ::በዚህ ሁኔታ ማስረጃ የማቅረብ ሂደቱ ተጀመረ:: ማስረጃዎቹ ከቅንጅት ጽ/ቤቶች የተወሰዱ፣ በተለያየ የቅንጅት ስብሰባዎች ላይ ለዶኩሜንት ተብለው የተቀረጹ የተለያዩ የስብሰባ ሂደቶች በቴሌቪዥን የተላለፉ የምርጫ ክርክሮች፤ሕዝባዊ የምርጫ ስብሰባዎች፣ መግለጫዎች፣ ቃለ መጠይቆችና የኘሬስ መግለጫዎች /Press Release/ ናቸው:: ሁሉም ስለምርጫ ገዢው ፓርቲ የፈጠረውን ሰብዓዊ መብት ረገጣ መሰረት የተደረጉ እንቅስቃሴዎች ናቸው ማስረጃ ሆነው የቀረቡት::

ከሕብረተሰቡ ጋር የተደረጉ ሰላማዊ ቅስቀሳዎ-ችና ውይይቶች ሁሉ የወንጀልን እንቅስቃሴ ለመሸፋፈን የተደረጉ እየተባሉ ተከሰስንባቸው::በዚህም መሰረት አቃቤ ሕግ ቀጠሮው እንዲራዘምለት ብቻ ጠይቆ ለ4/11 ተቀጥሮለት በዚሁ ተመልሰን ቃሊቲ ገባን::

በዚህ እለት ፍርዱ እየተካሄደ እኔን ሲያስገኝ የነበረው «እናንት ደፋር ሰዎች አለቦታችሁ በኔ መድረክ ላይ ፊጥ ብላችሁ የማታውቁበትን ቴአትር ለመጫወት በመሞከር የምወደውንና የማከብረውን የኖርኩበትን ሕይወቴ የሆነውን ሙያ ታበላሻላችሁ::ሕግ ታውቁ እንደሆን በሕግ ዓምላክ እላችኋለሁ ቦታዬን ልቀቁ»ማለት ነበር::

---

እኔና አልሚ ዘወትር በየዓመቱ ጋብቻችንን የፈጸምንበትን እለት ልጆቻችንና የቅርብ ወዳጆቻችን ጋር በመኖሪያ ቤታችን እናከብረው ነበር:: ከታሰርኩ ጀምሮ ግን በተለያየ ቦታ በመሆናችን አብረን ባንችልም በየአለንበት ሆነን እናስበዋለን:: ለአልሚ የስጦታ ልምድ

ስላለኝ፣ አካባቢው ከፈጠረው ምን ሳገኝ እንደምችል ከሌሎች ዞኖች ጋር በቤተሰብ ጥየቃ ሰዓት ከሚገናኙ የዞናችን ሰዎች ጋር ስመካከር በአንድ መኝታ ክፍል አብሮኝ ያለው መኮንን ሐጎስ የሚባለው እስረኛ በቁም ነገር አስቦበት ጥሩ ስጦታ አገኘልኝና ገዝቶ አመጣልኝ::

ያንን ያዩት የቅንጅት ወንድሞቼ ደግሞ በድብቅ ሳልሰማ፣ ዝግጅት አዘጋጅተው ምሳ ከተበላ በኋላ ወደ ቤተሰብ ግንኙነት ከመውጣታችን በፊት ቤት ያፈራውን አዘጋጅተው ሻማ ለኩሰው "እንኳን አደረሰህ" ብለው በኢትዮጵያ ባንዲራ ያጌጡና ሁሉም የፈረሙበትና የመልካም ምኞት መግለጫ በጋሼ መስፍን ጽሑፍ የሰፈረበት ለኔና ለአልሚ ሰጡን:: ስጦታውን በሁለታችንም ስም እኔው ብቀበልም በቤተሰብ ግንኙነት ሰዓት ይዤ ወጥቼ ለአልሚ አስረክቤያለሁ::

ዛሬ ልዩ ቀን ስለሆነ ከቤተሰብ የቀረ የለም:: ሁሉም አንድ አንድ ስጦታ ይዘዋል:: ዮዲት ነበረች ኬኩን የያዘችው:: ልክ እኔጋ ስትደርስ ምን እንደነካው አይታወቅም ኬኩ ከእጇ አምልጧት ወደቀ:: ምርር ብላ አለቀሰች:: ደሞ ቅሪት ነበረችና ማልቀሷ ውስጤን አቆሰለኝ:: ባባብላት ተይ ብትባል "እዚህ ድረስ አምጥቼው?" እያለች እንባዋ እንደጉድ ፈሰሰ:: ለኔ ላባቷ የመጣው ኬክ በመሰበሩ አዘነች:: ጋሼ መስፍን ያንን አይቶ መጣና "ዮዲት፣ ይሰበራ! ምን አለበት? ጦሳችንን ይዞ ይሂድ:: የወያኔ አይን ጥሩ ነገር ሁሉ ያጠፋል፣ ነገ ሽፈን አድርገሽ አምጪ " ብሎ ከለቅሶዋ መለስ አደረገልኝ:: ዮዲት ስታለቅስ አልሚም፣ እህቷ ማለዳም፣ እኔም ልናጅባት እየዳዳን የባሰ እንዳታለቅስ ነው ታግለን የመጣውን የመለስነው:: ዮዲት እንደዛ ያለቀሰችበት ቀን አይታወሰኝም::

የመጣው ኬክ ያ ብቻ አልነበረም:: ሌላም ኬክ ስለነበረ ወደ ዞናችን ስንመለስ እራት ከተበላ በኋላ በሰነስርአት ተቆርሶ ሁሉም መልካም ምኞታቸውን እንደገና ገለጹልኝ:: ኬኩን በተቻለ መጠን በዞን ላሉት እስረኞች ለማዳረስ ተሞክሯል:: በማግስቱ የዞን ሃላፊው ጠርቶኝ "ባንተ ጋብቻ በዓል ሳቢያ ልዩ ልዩ መፈክር ሲሰማ ነበር ትላንት" አለኝ::



"አይ እኔ መፈክር አልሰማሁም፣ የመልካም ምኞት መግለጫ ነው በጓደኞቼ የሰማሁት፣ ያ ደግሞ ክፋት የለውም:: ምናልባት ያልገባቸው እንደመፈክር አድርገውት ከሆነ ስህተት ነው" ስለው፣

"ምን ስህተት ነው አንተነህ የሚባለው የተናገረውን ሰምቻለሁ" አለኝ::

"እኔም ሰምቻለሁ:: ያውም እንዳንተ የሰሚ ሰሚ ሳይሆን በቀጥታ ከአፉ ሲወጣ ነው የሰማሁት:: ያለውን ልድገምልህ፣ «ዛሬ በዚህ ማረሚያ ቤት የጋብቻ በዓልህን እንዳከበርከው ሁሉ የሚቀጥለውን በቤትህ ተሰባስበን ለማክበር ያብቃን! ነው ያለው:: ከዚህ ሌላ አልተናገረም" ስለው፣

ያስ ቢሆን ምን ያስፈልጋል አለ:: ለማስረዳት መሞከር ድካም ነው ትርፉና እንዲያው ቢተወኝ ብዬ

«ይሄ እኮ እንኳን ጾም ልጓሙን ፈታልህ፣ እንኳን አደረሰህ እንደማለት ነው" ብዬው ሌላ ጊዜም አይደገምም፣ ምክንያቱም የሚቀጥለውን እዚህ አናከብረውም ብዬው ወጣሁ:: የሚገርመው ሄዶ ያሳበቀው ከኛው ጋር ኬኩን ጥርግ አርጎ የበላውና እሱም ምኞቱን የገለጸልኝ ሰው ነው:: እንዲህ እንዲህ እያልን ቀኑ በቀን እየተተካ አልፎ፣ የሰነድ ማስረጃ ለማዳመጥ የተሰጠው የቀጠሮ ቀን ደርሶ፣ ወደ ፍርድ ቤት በተለመደው ሁኔታ ሄድን::

የሰነድ ማስረጃው እንዲጀመር ተቀጥሮ ሳለ አቃቤ ሕግ "አልደረሰልኝም" በማለት የ4/11/98 ቀጠሮ ተላልፎ፣ ለ6/11/98 ጥዋት ተቀጥሮ የነበረውም ጠዋት ተሰርዞ ለቀትር በኋላ ተብለን ተመለስን:: በዛሬው ቀንም አቃቤ ሕግ እንደተለመደው አርፍዶ ነበር::የዛሬው ግን በጣም ስላረፈዱ ይመስላል ከፍርድ ቤቱ ተግሳጽ ተሰነዘረ:: ለዘብ ያለ ነው::ቢሆንም ከምንም ይሻላል:: ማስረጃው ለያንዳንዱ ተከሳሽ ታደለ፣ የጥራዙ ብዛት አይጣል ነው:: ለሸክም ያዳገተ ጥራዝ ታደለን::ሂደቱን ለመቀጠል ግን ፕሮጄክተሩ አልሰራም፣ ትርጉም አልደረሰም በሚል ሰበብ አጭር ቀጠሮ ሲጠየቅ፣ ዳኛው «እስቲ ይስተካከል እንደሁ ለ10 ደቂቃ ይሞከር» ብለው እረፍት ሆኖ ሲመለሱ ፕሮጄክተሩ ሰራና ማስረጃ

ማዳመጡ ቀጠለ:: አቃቤ ሕግ የማስረጃውን መግለጫ ማቅረብ ቀጠለ::አቃቤ ሕግ 100 ገጽ መግለጫ አነበበ::

ማስረጃዎቹ የቅንጅት መመስረቻ ጽሁፍ፤ የ4ቱ ፓርቲዎች የውህደት ስምምነት፣ ቃለ ጉባኤዎች፤ የአንዳርጋቸው ፅጌ «ነጻነትን የማያውቅ ነፃ አውጪ» መጽሐፍ በስጦታ ለቅንጅት መሰጠቱን የሚያስረዳ፤ በምርጫው ወቅት የተሰጡ ጋዜጣዊ መግለጫዎች፤ ኢሕአዴግና ነጻ ምርጫ አይተዋወቁም ማለታችን፤ ገዢው ፓርቲ አላሸነፈም መባሉ፤ ምርጫ ቦርድ ለገዢው ፓርቲ የቆመ ነው መባሉ፤ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲን ረብሻ ማበረታታት፤ የተቃውሞ እንቅስቃሴ ያደረጉትን በማመስገናችን፤ ከሕብረት ጋር በአንድነት በመሆን ጠቅላይ ሚኒስትሩ ለሰነዘሩት ማስፈራሪያ «ጅራፍ ራሱ ገርፎ ራሱ ይጮሃል» የሚል ጋዜጣዊ መግለጫ በመውጣቱ፤ የመኢአድ አመራር «ሰላማዊ ትግል እያለ በሚያንቆላጽሰው» አመጽ ተብሎ የቀረበው ነው ማስረጃ የተባለው:: በዚህ ቀን የተጀመረው የማስረጃ ማዳመጥ በየዕለቱና ሲያስፈልግም በየሁለት ሶስት ቀኑ ርዝመት እየተቀጠረ አንድም አንቀጽ ሳይቀር በኢትዮጵያ ያሉ አንቀጾች ሁሉ ተጠቅሰው ቀረቡና ይሄው ሂደት እስከ ሐምሌ 28 ቀን 1998 ቀጥሎ፣ በዚሁ ፍርድ ቤት ለክረምት ተዘጋ::ቀጣዩ ቀጠሮ ለመስከረም 29/1/99 እንዲሆን ሲወሰን ጋሽ መስፍን ተነስቶ «እንደምታውቁት ላለፉት በርካታ ወራት እኛ አስር ቤት እናንተ እቤታችሁ ከቤተሰባችሁ ጋር ናችሁ:: እና አሁን እኛን የዋስ መብት ከልክላችሁና ቀጥራችሁ ለመሆኑ ሰላማዊ እንቅልፍ ይወስዳችኋል?» በማለቱ ቀጠሮው ትንሽ ቀን ተቀንሶለት ለ25/1/99 እንዲሆን ተወሰነ:: ጋሽ መስፍን የተናገረው ትንሽ ስሜታቸውን የፈተነውና የሞገተው ይመስላል::

ተመልሰን ወደ እስር ቤታችን ገብተን በየዞናችን ላሉት ስንነግራቸው ማመን አልቻሉም:: «የናንተም እንደኛው ቀን እየጨመረ መጓተት ያዘ? አይ ጉልበት፣ አይ ስልጣን!? ብለው አብዛኛዎቹ እስረኞች አዘኑ::

ያለንበት ዞን አዲስ የተቋቋመ ባይሆንም ቀደም ሲል የሴት እስረኞች ሲወልዱ የሚታረሱበት፣ የእመጫቶች ቤት የነበረ ነውና ብዙም ትኩረት ሳይሰጠው የከረመ ነው:: ስለዚህም አሁን በተለይ



ለክረምቱ ብዙ መሰራት ያለበት ነገር አለ:: ግቢው እንደሌሎች ዞኖች ቀይ አሸዋ አልተበተነበትም፤ ዝናብ ሲጥል ጎርፉ ወደ ቤትም ይገባል:: ስለዚህም የክረምት ሥራችን ግቢያችንን ማልማት ይሆናል በሚል ለማረሚያ ቤቱ አስተዳደር ማመልከቻ አስገባን:: ማመልከቻው በገንዘባችን ቀይ አሸዋ ማስመጣት እንድንችል ይፈቀድልን የሚል ሲሆን ወዲያው በዞን ሃላፊው አማካይነት ተፈቀደ ተባልን::በዚህም መሰረት ብርሃኑ ለማስመጣት ፈቃደኛ ስለሆነ ለቤተሰብ ቅዳሜ ተነግሮ፣ ማክሰኞ እለት አሸዋ የጫነው መኪና ገብቶ ዞኑ በር ላይ ሲደርስ ፖሊሶች ተከታትለው መጥተው "ውጣ ተብለሃል" አሉት ሾፌሩን:: አብሮት የነበረው ሰው "አሸዋውስ?" ቢል "ከነአሸዋው ውጣ ተብሏል" ሲባል የዞን ኃላፊው ተጠርቶ «ስህተት መሆን አለበት፣ ተፈቅዶ ነው የመጣው» ቢልም የሚሰማ ጠፋና የመጣው ፖሊስ « ይውጣ ተብሏል ይውጣ» ብሎ መኪናው ከነአሸዋው በገባበት በር ወጥቶ ሄደ:: እንዳያንስ በሚል የአቶ አባይነህም ቤተሰብ ሌላ መኪና አሸዋ አምጥተው ነበር ያም ተመለሰ:: የሚያሳዝነው ጉዳይ መኪናው የኪራይ ስለነበር ያን አሸዋ እንደገና ጭኖ የሚመለስበትን ሊያስከፍል ስለሆነ ባለመኪናው ከፈለገ አሸዋውን እንዲወስደው ተመረቀለት::

የዞኑ ሃላፊ በጣም ተገርሞ ጉዳዩን ለማጣራት ሲሞክር «መንግሥት ያስመጣል፣ እነሱ ማምጣት አያስፈልጋቸውም» የሚል መልስ ነበር የተሰጠው ያንን በማዘንና በመገረም ሲነግረን በጣም አዘንን:: ምን ማለት ነው? በተፈቀደው መሰረት ከመጣ በኋላ ለምን ይፍሰስ ይባላል? መንግሥትስ የሚረዳው ቢያገኝ ክፋቱ ምን ላይ ነው?ለዚህም የሚሰጠው የትርጉም ስም «ክፋት» ከመሆን አያልፍም::

ክረምቱ ብዙም አላስቸገረንም:: አልፎ አልፎ ከሚጥለው ኃይለኛ ዝናብ ጎርፍ የመጣበት ወይም እንደተፈራው መሰረት አልፎ ወደየመኝታችን የገባበት ጊዜ ብዙ አልነበረም:: ቤተሰቦቻችን በክረምቱ ምክንያት ብርድ ያስቸግራቸዋል የሚል ጭንቀት ቢያድርባቸውም ብዙ ችግር አላጋጠመንም:: ይልቅስ እኛን ሲያሳስበን የነበረው የኛ ቤተሰብ መገናኛ ሰአት ሲደርስና ሰማዩ ሲጨልም ለኛ ስንቅ በማቀበልና እኛን ለማበረታታት

የሞራል ጥንካሬ እንዲኖረን በመጣር ላይ መድከማቸው አንሶ ደሞ ዝናብ ሲመታቸው ነው ብለን ነው የምንጨነቀው።የሚገርመው ነገር በቤተሰብ ግንኙነት ሰአት ዝናብ የጣለውና ሁላችንንም የመታን አንድ ቀን ብቻ ነው።ያም ቢሆን ለአጭር ጊዜ።

ሰማዩ ይጠቁርና ሰማይ ሰማይ ስናይ ወዲያው ፈጣሪ ጭንቀታችንን እያየ፣ ጸሎታችንን እየሰማ የቤተሰቦቻችንን ድካም ከቁጥር በማስገባት ይመስላል፣ ደመናው ይገፍና ዝናቡም ይጠፋል።ለፈጣሪ ምስጋና ይግባው!

በወህኒ ቤት አንድ ልምድ አለ። ሁልጊዜ ከባድ ዝናብ በሚዘንብበት ሰአት ምን ጊዜም ይሁን ፖሊሶቹ መጥተው ያስገቡንና በሩን ይቆልፉብናል፤ ሲያባራ ደሞ ይከፍቱታል። ለምን እንደሆነ ለማወቅ ባደረብኝ ጉጉት አንድ ቀን ወደ ሆስፒታል ሲወስዱኝ አንዱን ፖሊስ ጭር ባለና ብቻችንን በሆንበት ሰአት ሥራዬ ብዬ ጠየቅሁት።የሰጠኝ መልስ «ለነገሩ እናንተ ዞን እንኳን ተዘጋም አልተዘጋም ልዩነት የለውም።በሌላ ዞን የሚዘጋበት ምክንያት ያንን ሃይለኛ ዝናብ መከታ አድርገው ለመጥፋት የሚሞክሩ ስለሚኖሩና ከዚህ በፊት አጋጥሞ ስለሚያውቅ ነው» አለኝ። ጥሩ ጥንቃቄ ነው። ግን ምናለ ሲጠፉ የሚሞክሩትንና የማይሞክሩትን ቢለዩ? ለነገሩ ሲያባራ እስከተከፈተ ድረስ፣ ባይዘጉትም በፈቃዳችን ዝናቡን ለመሸሽ ወደ ቤታችን መግባታችን የማይቀር ነው።

በእስር ቤት በቀዝቃዛ ውሃ ከመታጠብ ውጪ አማራጭ የለውም እየዋልን እያደርን ስንሄድ ቀዝቃዛ ውኃ ያለመድነውም፣ በቀዝቃዛ ውሃ መታጠብ ጤናማ እንደሆነ ተረድተን ወደነዋል። ደሞም የቃሊቲ ዓየር ሞቃት ስለሆነ፣ በበጋው ቀኑን ሙሉ ማጠራቀሚያውን ጸሃይ ሲመታው ስለሚውል ውሃው እንደ አዲስ አበባ ውሃ አይቀዘቅዝም፤ለብ ያለ ስሜት አለው።ችግሩ በክረምት ነው፤ በተለይ የጤንነት ችግር ላለባቸው። የዘንድሮው ክረምት ግን አልፎ አልፎ ጸሐይ ስለሚወጣ አላስቸገረንም፣ እኔ ደሞ ለፊዚዮቴራፒ ሆስፒታል ስለምሄድ የሙቅ ውሃ ሻወር የማግኘት እድል አለኝ።

ሌላ አንድ የማይረሳኝ ክፋት አለ። ወደ አዲሱ ዞን ተዛውረን ሳለ ወዲያው የፋሲካ በዓል ደረሰ።



እንዲያው የመጀመሪያው ምቀኝነት ይህ ሳይሆን ይቀራል? አንድ ጥያቄ ወህኒ ቤቱን ጠየቅን። «አውዳመት በመሆኑ ከቤተሰቦቻችን ጋር በመመካከር፣ አብረውን ካሉትም ታራሚዎች ጋር በመሆን ፋሲካ በዓል በዓል እንዲሸት የሚያስፈልገውን ሁሉ ከቤተሰቦቻችን እንዲመጣልን ይፈቀድልን» አልን። ብንጠይቅ እሺም የለም እምቢም የለም ዝም ዝም ሆነ። ደጋግመን ብናስታውስም ለበላይ አቅርበናል እስካሁን መልስ አልተሰጠም ብቻ ሆነ። ቀደም ሲል ይህ በዓል በእስረኞች መዋጮም ሆነ በበጎ አድራጊዎች ስጦታ በጋራ ይከበር ነበር። በጣም የሚያሳዝነው የኛ በዚህ ቦታ መታሰር የሌላውንም ታሣሪ እድል አበላሸ። እኛ ይህን በዓል ለማክበር የሚያስፈልገውን በእስር ቤቱ ደንብ መሰረት ስንጠይቅና ስንከለከል በየዞኑ የኛ ሰዎች በመኖራቸው ሁሉም በአንድነት ተከለከለ። ምናለ ቢፈቅዱልን ኖሮ? ምናለ ከሩቅ ቦታ መጥተው ጠያቂ የሌላቸው፤ አቅም የሌላቸው ጋር ለማክበር ብንችል ምን ነበረበት? በዚህ ከታሳሪው ፍቅር እንዳናገኝ ነው? እኛ ለዚህ አልነበረም ሃሳባችን። እስረኛው ፍቅሩንማ ከሰጠን ቆየ! ይህንንማ በገሃድ እያየነው ነበር፤ የወህኒ ቤቱም አስተዳዳሪዎችና ሹሞች የሚያደርጉት ጠፍቷቸው ነው እንጂ ፍቅሩንማ አይተውታል።

በብዙ መንገድ እኛን ከሌላው ታሳሪ ለማጣላት ለማለያየት ተሞክሮ ነበር። ከኛ ጋር የተጫወተ፤ ቡና የጠጣ፤ እኛ ጋር የበላ፤ እቃ እንኳን የተዋሰ፣ ችግር ወዳለበት ዞን ተዛውሯል፤ አንዳንድ ጥቅማ ጥቅም ተነፍጓል። ወረቀት አመላለስክ እቃ ከሀብረት ሱቅ ገዛህላቸው፤ ከሌላ ዞን ቅርጻ ቅርጽ ገዝተህ አመጣህላቸውና ሌላም ሌላም እየተባለ በግምገማና በወቀሳ መከራውን በልቷል።።።።

አንድ በጣም የሚያሳዝን አጋጣሚ ልጥቀስ።እኔ በነበርኩበት ዞን አንድ በሌላ ወንጀል የተከሰሰ ግለሰብ ነበር። አሁን በህይወት የለም። ግለሰቡ የኤይድስ ታማሚ በመሆኑና የማራዘሚያ መድሃኒት ስለሚወስድ ደህና ምግብ ያስፈልገዋል። ቤተሰቡ አቅም የለውም። ከወህኒ ቤቱ የሚሰጠው በቂ አይደለም። ስለዚህ ከኛ ምግብ ልንሰጠው ወሰንን። በዚህም ተስማምተን መስጠት ስንጀምር ተጠርቶ «እኛ እኮ አንተን ወደ

ተስፋ ድርጅት ሄደህ እንድትሰራ የፈቀድንልህ ደህና ሰው ነህ ብለን ልንረዳህ ነበር፣ አንተ ግን ከቅንጅቶች ጋር ማህበር እየተጣጣህ ነውና ብታስብበት ይሻላል» አሉትና ግራ ገባው:: ቀስ ብሎ አጋጣሚ ጠብቆ ነገረኝ፤ ተመካከርንና እሱ እየመጣ መውሰዱን እንዲተውና እኛ ሹልክ እያደረግን እንድንሰጠው ሆነ::

በዚህ መንገድ ጥቂት እንደሄደ በመጨረሻው "በቃ የፈለጉትን ያድርጉ ተደብቄ አልበላም፣ እኔው እወስዳለሁ" ብሎ ወሰነና በዚያው ቀጠለ፣ ከተስፋ ድርጅትም አስቀሩት:: ከጥቂት ወራት በኋላ በሽታው አዳክሞት ዋርድ ሄደና ተኛ:: እዚያም ስንልክለት ቆየንና በስተመጨረሻ እንዳይላክለት ትዕዛዝ ተላለፈ:: አሁን ይሄን ምን ይሉታል? ክፋት እንጂ ሌላ ምን ትርጉም ይሰጠዋል?በቀለም በዚያው ሕይወቱ አለፈ::

አዲስ አመት ደረሰ:: አንድ ምክክር አደረግን:: የሁላችንም ቤተሰብ ይመጣል፣ ሁሉም ቤተሰብ ለዘመን መለወጫ ምግብ ያመጣል:: ሁሉም ዶሮ ወጥ፣ ዱለት፣ ጎረድ ጎረድ ማምጣት የለበትም ተባብለን ማ ምን ያምጣ ብለን ወሰንን:: ዝርዝር ስናወጣም፤ ዳቦ፤ ፌጦ፤ ዶሮ፤ ዱለት.. .. .. እያልን ተመዳደብን:: ይሄው ለቤተሰብ ተነገረ:: ከቤተሰብ ውጪም የሚያመጡልን ወዳጅ ዘመዶቻችን አሉ የነሱም ተዳምሮ በግቢው ላለነው ይበቃናል:: ደሞ አንዳንድ ታሳሪዎችም ከቤተሰባቸው ስለሚመጣላቸው እኛ ማሰብ ያለብን ምንም ለማይመጣላቸው ነበር:: በዚህ ተስማምተን ቤተሰብም አውቆት፤ እነሱ ደክመው ተቸግረው ሊያመጡ እኛም ተካፍለን ልንበላ ተዘጋጀን:: ቀኑ ደረሰ::የበዓሉ እለት የቤተሰብ መጠየቂያ ሰአት ይለወጣል፣ እንደሌላው ጊዜ ከቀትር በኋላ መሆኑ ይቀርና ጠዋት ይሆናል:: በዚህም መሰረት እኛ ከቤተሰብ የምንገናኘው በአምስት ሰአት ነው:: ተዘጋጅተን በሰአቱ ስንወጣ፣ እንዳሰብነው ቤተሰቦቻችን በስምምነታችን መሰረት፣ ከቤተሰብ ውጪም ያሉት ወዳጆቻችን የተለያየ አይነት ይዘውልን መጡ:: ዳቦ፣ ብስኩት፣ ኬክ አልቀረም:: ያንን ተሸክመን ይዘን ከገባን በኋላ በመጀመሪያ በተለምዶ ከኛ ጋ ምግብ ለሚወስዱት በቅድሚያ እኛ ከመብላታችን በፊት የተቻለውን ያህል ከየአይነቱ እያደረግን ሰጠን:: የግቢው ታሳሪዎች



ኮሚቴም ከህብረት ሱቁ የሚሰጠውን ለስላሳ አደለ:: ቄጠማም በግቢው ተነሰነሰ እጣኑ ተጨሰ፣ ግቢያችን በዓል በዓል ሸተተ:: ዳቦው ተቆርሶ ከግቢ ውጪም በጥበቃ ላይ ለነበሩት ሁሉ ታደለ:: ተመራርቅን፣ ጥሩ በዓል አሳለፍን::

ይህን ልተወውና ወደ ፍ/ቤት ላምራ:: ሲጠበቅ የነበረው መስከረም 25/99 ደረሰ:: በተለያየ ዞን በመታሰራችን አንተያይምና በጣም እንነፋፈቃለን:: በተለይ በክረምቱ ምክንያት ከሁለት ወር በላይ የተሰጠው የመስከረም ቀጠሮ እጅግ ረዝሞብናል:: ናፍቶቃችንን አባብሶታል:: የቸኮልነውም ምንም ውጤት ለማይገኝበትና እርባና ለሌለው ፍርድ ቤት ሳይሆን እርስ በርሳችን ለመተያየት ነበር::

መስከረም 25/99 ጠዋት እንደተለመደው በመኪና ተጭነን ቀደም ብለን ወደ ፍርድ ቤት ሄድን::ያው ነው የተለወጠ ነገር የለም::ቁጭ መኪና ውስጥ፤እግራችን ሲደነዝዝ በአጃቢ ወደ መታጠቢያ ቤት አስፈቅዶ መሄድ፤ እንደገና ተመልሶ መጥቶ መጠበቅ::

ከመግባታችን በፊት የዳኞች መኪና ሲገባ ብናይም አቃብያነ ሕጎችን ግን አላየንም::

በመጨረሻ ላይ ግቡ ተባልንና ወደ ፍርድ ቤቱ ስንገባና ከጓደኞቻችን ጋር ስንገናኝ እየተቃቀፍን ናፍቆታችንን ስንወጣ፣ ቤተሰቦቻችን በደስታ ተሞልተው ያዩናል:: እኛ አሁን ተቀናጅተን አንድ ቤተሰብ እንደሆን ሁሉ ቤተሰቦቻችንም እንደዚያው አንድ ሆነዋል:: እነሱ አልተነፋፈቁም በየሳምንቱ ለጥየቃ ሲመጡ ይገናኛሉ::

ቢያንስ 4 ሰአት ድረስ ተቀምጠን አቃቢያን ህጎች መጡ:: የስነስርአት አስከባሪው ገብቶ ለዳኞቹ መምጣታቸውን ነግሮ ዳኞቹ ገቡ:: ሁለት ብቻ ናቸው፣ ልኡልና መሀመድ አሚን:: ዳኛ ልኡል ዳኞች ባለመሟላታቸው ብሎ ለ3/2/99 ቀጥሮ ችሎቱን አሰናበተ፣ እኛም በመጣንበት ሁኔታ ተመልሰን ወደ ወህኒ ቤት ሄድን::

የዞናችን ታሳሪዎች ሁል ጊዜ ወደፍርድ ቤት ስንሄድ የምንፈታ ይመስላቸዋልና ተመልሰን ተቀጠረ ስንል ከኛ ይልቅ ተስፋቸው የሚጨልመው የነሱ ነው:: «እናንተ እኮ እንደኛ ገደላችሁ፣ ወይ ዘረፋችሁ አለያም አስገድዳችሁ ደፈራችሁ አልተባላችሁም:: እናንተ እኮ

ምርጫ ገባችሁ አሸነፋችሁ ታሰራችሁ:: በቃ!:: ጥፋታችሁ ማሸነፋችሁ ነው» ይሉናል:: ከታሰሩትም ውስጥ ክፉም ደግም የማይሉን ግን በወሬ በወሬ ስንሰማ መታሰራችንን ልክ ነው ብለው የሚደግፉ 1 በመቶ የሚሆኑ አሉ ምክንያታቸውም ይገባናል::

ቀጣዩ ቀጠሮ ቀኑ ደርሶ ወደፍርድ ቤት ሄድን::ዛሬ አንድ ነገር ለማድረግ ተነጋግረናል:: ዳኞቹ አቃብያነ ሕጎችን በመጠበቅ እኛን እየጎዱን ነው:: ወህኒ ቤቱ ስንደውልልህ አምጣቸው ስላልተባለ እያጣደፈ ይወስደንና ይጎልተናል:: ወይ አቃብያነ ሕጐች እንዳያረፍዱ ማስጠንቀቂያ ለይስሙላ አንድ ቀን ቢሰጥም፣ እነሱ ግን ማን አለብን ብለው አሁንም ከማርፈድ አልተመለሱም:: ከኛው መሃል ዳኞች በመኖራቸው አቃብያነ ሕጎች አርፍደው ካልገቡ የፍርድ ሂደቱ ይሰናከላል ወይ? ብለን ብንጠይቃቸው ደንቡማ ዳኞች ከመግባታቸው በፊት ገብተው ተዘጋጅተው ነው መጠበቅ ያለባቸው» ብለውናል:: ዛሬ ካረፈዱ ከመቀመጫችን ተነስተን እንቀበላቸው ተባብለን ስለነበር እንደተለመደው አርፍደው ሲገቡ ሁላችንም ብድግ አልን፤ በጣም ደነገጡ:: ከእኛ ውጪ ሁሉም መጀመሪያ ስላልገባው ግራ ተጋብቶ ነበር፣ በኋላ ስንሳሳቅና አቃብያነ ሕጎች ሲሽማቀቁ ገባቸውና ከፊሎቹ ሳቁ::

ዳኞች እንደተለመደው ገብተው ሁሉም መቅረባቸውን ካረጋገጡ በኋላ ሥራቸውን ጀመሩ:: ወዲያው አቃቤ ሕግ ተጨማሪ የሰነድ ማስረጃ እንዳለውና እንዲያቀርብ እንዲፈቀድለት ጠየቀ:: እነ ዳንኤል "ይህ ተጨማሪ የሚባለው ማስረጃ በብርበራው ከቤታችን የተገኘ ሳይሆን በሕገወጥ መንገድ የቀረቡ ፎቶ ኮፒዎች፤ ከኢንተርኔት የተገኙ በድጋሚ የቀረቡ ናቸው" በማለት ተቃውሞ አቀረቡ:: አቃቤ ሕግም አንዳችም እንዳናቀርብ የሚያስገድደን ሕግ የለም በማለቱ ዳኞቹ "ከአስር ደቂቃ በኋላ በዚህ ላይ ውሳኔ እንሰጣለን " በማለት ወጥተው ሄዱ:: ለማስመሰልና ትንሽ ትንሽም ቢሆን ፍርድ ቤት ፍርድ ቤት እንዲሸት የታቀደ ዘዴ ነው::ማን ያውቃል? ምናልባትስ ወደ በላይ አካል ደውለው እንዴት እናድርግ ብለውስ እንደሆን?

ዳኞቹ ሲወጡ ሁላችንም «አሁን ሲመለሱ ተቃውሞውን ውድቅ አድርገው ተጨማሪ የተባለውን



ማስረጃ እዲያቀርብ ይፈቅዱለታል ተባባልን::ወዲያው ዳኞች ተመልሰው መጡና «ጉዳዩን ከመረመርን በኋላ የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፤ Inadmissible የሚባል ሕግ የለም::ከተጠቀሰው ቀን ውጪ ብርበራ በመደረጉ ሕገወጥ ነው ለማለት አይቻልም::ፎቶ ኮፒም አሳማኝ ከሆነ ተቀባይነት ያገኛል::ከዌብሳይት የተገኙም ወደፊት የሚመዘኑ ናቸው::በድጋሚ የቀረበው ብቻ ተቀባይነት አይኖረውም ሌላውን ግን ማቅረብ ይቻላል::» ብለው ወሰኑ:: በኛ በተከሳሾች በኩል ጋሽ መስፍን (ፕሮ/ር)፣ «የተከበረው ፍርድ ቤት አንድ ነገር እንዲያዳምጠን እንጠይቃለን:: አቃቤ ሕግ በኢትዮጵያዊ ባሕል መከባበር ያለ ቢሆንም እኛን ተጠርጣሪዎችን ወይም ተከሳሾችን ያዋረደ መስሎት ባሕላችንን እያዋረደ መሆኑን ከሂደቱ አይተናል.. .. » በማለት እውነቱን እያነሳ አቤቱታ ሲያቀርብ አቃቤ ሕግ ከስነስርአት በወጣ መልኩ ጣልቃ በመግባት

« እነሱ መመርያ ሊሰጡን ነው?» አለ::

ዳኛው «ይቀጥሉ» አለ፣

ጋሽ መስፍን «እና የመዘርጠጡ ነገር እንደፈቀደው ይሁንና ብንወልድ የምናደርሳቸውን አንተ በማለታቸው ከኛ የሚቀነስ ነገር የለም ግን የተከበረው ፍርድ ቤት አድመኞች ወንጀለኞች እያለ ከፍርድ በፊት የሚጠቀምበትን ቃል እንዲተውና ተከሳሾች እንዲል ይታዘዝልን» አለ:: ዳኛው ይህንኑ በመቀበል ተከሳሾች በሚሉት እንዲጠራ ሲሉ ወሰኑ:: ተመስገን ይቺ አቤቱታችን ተቀባይነት አገኘች::

ቀደም ሲል የምስክሮች ዝርዝር እንዲሰጠንና በቅድሚያ አውቀናቸው ለመስቀልኛ ጥያቄ እንድንዘጋጅ በማለት የነዳንኤል ጠበቆች ያቀረቡትንም ጥያቄ አቃቤ ሕግ

«የምስክሮች ማንነት አሁን በቅድሚያ ከተገለጸ የተከሳሾች ደጋፊዎች ጉዳት ሊያደርሱባቸው ስለሚችሉ ከመመስከር ወደኋላ ሊሉ ይችላሉና ጥያቄው ውድቅ ይሁንልን » ሲል ባመለከተው መሰረት ፍርድ ቤቱ ተቀብሎ ዝርዝሩ በቅድሚያ እንዳይሰጥ ወሰነ:: አቃቤ ሕግ በሃገር ውስጥ ያለው የሕግ አንቀጽ አልበቃህ አስኪለው ድረስ ጠቅሶ በከፍተኛ ቅጣት ሊያስፈርድ እየጣረ ሳለ፣ የምስክሮች ዝርዝር አስቀድሞ እንዳይሰጥ

የቀረበውን ጥያቄ ፍርድ ቤቱ መቀበሉ የሚያስተዛዝብ ጉዳይ ነው። የምስክሮች ማንነት በምን ላይ ይመሰርታሉ የሚለው ጭብጥ ምስክር ለሚቀርብባቸው ወገኖች ያለው ጥቅም፣ የምስክሮች ማንነትና ተአማኒነት ከአስመስካሪው ወይም ከሚመሰክርበት ጋር ያላቸው ግንኙነት፤ በጥቅም የተገዙ ወይስ በእውነት ለእውነት የቆሙ?የሚለውንና ሌሎችም ጥያቄዎችን ለመመለስ የሚያስችል ሆኖ ሳለ ለምን በቅድሚያ አይሰጥም እንደተባለ ግልጽ አይደለም። አቃቤ ሕጉ በቅድሚያ ማንነታቸው የታወቀ እንደሆነ የተከሳሽ ደጋፊዎች ጉዳት ሊያደርሱባቸው ይችላሉ የሚል መከላከያ ነው ያቀረበው። ይህ እንደማይሆንና የተከሳሽ ደጋፊዎች በሰላማዊና ፍትሓዊ ሂደት እንደሚያምኑ ፍርድ ቤቱም አቃቤ ሕጉም በእውነቱ መንገድ የሚያውቁት ነው።

ቀጣዩ አቤቱታ በሙሉነህ ኢዮኤል በኩል የቀረበ ነበር። ሙሉነህ ያቀረበው አቤቱታ
«የተከበረው ፍርድ ቤት፤በ12/12/98 ታምሜ ተኝቼ ነበር፤ ትፈለጋለህ ተብዬ ከተኛሁበት ከተቀሰቀስኩ በኋላ ወደ ምፈለግበት ቦታ ስደርስ በፖሊሶች ታጅቤ ጨለማ ቤት ተወስጄ ተዘጋብኝ በ3/13/98 ከጨለማ ቤት አውጥተው ትኩስ ሲሚንቶ የተለቀለቀ ወለሉ ላይ አስተኙኝ ከሰማይ ሌላ የሚታይ ነገር የለም፤ ያ አልበቃ ብሎ ጭራሽ ቅዳሜና እሁድ ከቅርብ ዘመድ በስተቀር ማንም እንዳይጠይቀኝ ተደረጎ ግፍ እየተሰራብኝ ነው።» ሲል አንዱዓለም አራጌም ተመሳሳይ ሁኔታ እንደተፈጸመበት፣መላኩ ፋንታዬም በበኩሉ «በየቀኑ እየጠሩኝ ጭለማ ቤት ትታጎራለህ እያሉ ያስፈራሩኛል። ባዶ ቤት እያስገቡ ይፎክሩብኛል፤መታመሜን በመግለጽ ለፍርድ ቤቱ ህክምና መከልከሌን አቤት ብዬ ቢታዘዝልኝም አስካሁን ድረስ ምንም ፍትህ አላገኘሁም። ከ3 ሳምንት ደጅጥናትና ልመና በኋላ ምርመራ ተደርጎልኝ የታዘዘው የደም ምርመራ በሐምሌ ተደርጎ ውጤቱ እስካሁን ድረስ ለሃኪም አልቀረበም፣ እኔም አልቀረብኩም። ቢያንስ እስር ቤቱ የፍርድ ቤቱን ትእዛዝ ማክበር ይገባው ነበር።» ሙሉነህና አንዱዓለም አራጌ ለ3 ሳምንታት የቤተሰብ ግንኙነት ተከልክለው ነበር።



ፕ/ር መስፍንም በበኩላቸው ፍርድ ቤቱን ለመናገር አስፈቅደው
«የተከበረው ፍርድ ቤት ብርበራ በሚል ሰበብ ከየመኝታ ክፍላችን የተወሰዱብን ማስታወሻዎች አልተመለሱልንም። ባለፈው አቤቱታ አቅርበን መክሰስ ትችላላችሁ ተብለናል። እኛ እኮ እስረኞች ነን እንዴት አድርገን ነው የምንከሰው?» ላሉት ፍርድ ቤቱ "በውክልና መክሰስ ትችላላችሁ" ብሎ በአጭሩ ዘጋው። ውክልና ለመስጠትም ከቤተሰብ ጋር መገናኘት እንደሚያስፈልግ፣ ያም ቢሆን በእስር ቤቱ ሃላፊዎች መልካም ፈቃድ የሚፈጸም መሆኑንና ከወህኒ የሚወጣ ማንኛውም ወረቀት በሃላፊዎቹ እየታየ እንደሚወጣ፤ እነሱን ለመክሰስ የሚወጣ ወረቅትም ፈቃድ እንደማያገኝ በሚገባ እየታወቀ ሆን ተብሎ የተላለፈ የለበጣ ውሳኔ ነበር። ቀጣዩ ቀጠሮ ለ8/2/99 ሆነ።

በ8/2/99 በዋለው ችሎት የተጨማሪው ማስረጃ መግለጫ ቀረበ። አቃቤ ሕግ ምስክሮች ማሰማት እንዲጀምር ለ15/2/99 ቀጠሮ ተሰጠው። አቃቤ ሕግም ምስክሮች ለተጽእኖ የተጋለጡ ስለሆነ ማንነታቸው በሚዲያ እንዳይገለጽ ትእዛዝ ይሰጥልን የሚል ጥያቄ አቀረበና ይሄው ጸደቀለት። ፍርድ ቤቱ ምስክሮችን በተመለከተ 10 ምስክሮች እንዲያቀርብ ቢወስንም በ15/2/99 የቀረቡት ምስክሮች ግን 8 ነበሩ። ከቀረቡት ምስክሮች ጥቂቶቹ የተከሳሾች ቤት ሲበረበር ታዛቢ ሆነው መምጣታቸውንና የቀረቡትም ሰነዶች ያዩዋቸው መሆናቸውን መሰከሩ። ጥቂቶች ደግሞ በ29/9/97 በመኢአድ ጽ/ቤት የተደረገውን ስብሰባ "የአመጽ ቅስቀሳ" በማለት ይህንኑ ያስረዳል የተባለው ሰነድ እንደሚያውቁ አረጋገጡ፤ ሌሎቹ ደግሞ ሰኔ 1/97 በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በተነሳው ረብሻ ተከሳሾች የነበራቸውን ሚና ለማስረዳት የቀረቡ ነበሩ።

ታዛቢ ነበርን ያሉት የመሰከሩት የተገኙት ማስረጃዎች ጋዜጣዊ መግለጫዎች፤ የስብሰባ ማስታወሻዎች፤ በምረጡ ቅስቀሳ ላይ የተቀረጹ ቪዲዮ-ዎች፤ ኮምፒዩተሮች፤ ሲዲዎችና የመሳሰሉት ናቸው።

ምስጉን ገብረሊባኖስ የተባለው "ነጋዴ ነኝ" ያለው ሲመሰክር፤

«ኢንጅነር ግዛቸውን አውቃቸዋለሁ ቤታቸው ሲፈተሽ ታዛቢ ነበርኩ። በራሳቸው ቤት ቢሮ ውስጥ የተገኙ ኮምፒዩተሮች፣ማስታወሻ ወረቀቶች፣ የምረጡ ቅስቀሳ ካሴቶችና የተለያዩ ሲዲዎች ሲሆኑ ሲፈርሙ ቆይተው አንዳንዶቹ በተለይ መጨረሻ ላይ በቀረቡላቸው ላይ "አልፈርምም፣ ይህ ከዚህ የተገኘ አይደለም፣ እናንተ ያስቀመጣችሁት ነው" ብለው አልፈረሙም። ያልፈረሙባቸው በምብና ገጀራ ታጠቁ የሚልና የሚገደሉ ባለስልጣናት የስም ዝርዝር ማለትም ጠ/ሚኒስትር መለስ ዜናዊ፣ ገነት ዘውዴ፣ አዲሱ ለገሰ የሚለው ጋር ሲደርሱ ባለቤታቸው እያየህ ፈርም አንዳንዱ እነሱ ያመጡት ነው ሲሏቸው አልፈርምም አሉ» በማለት መሰከሩ። ፖሊሶችና ታዛቢ የተባሉት እርስ በርስ ተፈታትሸናል ቢሉም የኢንጅነር ባለቤት ግን ፖሊሶቹ ወረቀቱን ሲያስቀምጡ ስላዩ ነው እያየህ ፈርም ያሉት።

ኢንጅነር ግዛቸው እኒህን ምስክር በደንብ ያውቋቸዋል። ነጋዴም አይደሉም የሚያውቋቸው ሌላ ቦታ ነው። ምስክሩ ሱቁ ይገኝበታል ያሉት ቦታ ሱቅ የለም፣ ይህን ደሞ ኢንጅነር ግዛቸው ሰፈራቸው ስለሆነ አካባቢውን በሚገባ ያውቁታል። ኢንጅነር ሰውየውን ትኩር ብለው እያዩ

«አቶ ገብረሊባኖስ እኔና እርስዎ ጠ/ሚኒስትር ቢሮ ለስብሰባ መጥቼ እኔ የደህንነት ሠራተኛ ነኝ ብለው ተዋውቀውኝ ዛሬ ለምን ነጋዴ ነኝ አሉ?» ብለው ጠየቁ ምስክሩ በመደናገጥ መልስ መስጠት አልቻሉም። ኢንጅነር ቀጥለው

«እርስዎ እኔ ቤት ውስጥ ደህንነቶቹ ወረቀቱን ሲያስቀምጡ አይተዋል፣ ሱቅዎ የት ነው ሲባሉ ቦሌ ት/ቤት ፊት ለፊት ነው ያሉትም ስህተት ነው። ቦሌ ት/ቤት ጎን ሱቅ የለም፣ ከኔ ቤት ፊት ለፊት ቦሌ ት/ቤት ነው አሉ።» የምስክሩ መልስ የተደነጋገረ ስለሆነ ፍርድ ቤቱ የማጣሪያ ጥያቄ አቀረበ «ፖሊስ ተፈተሸ ብለዋል፣ ፖሊስ እንዴት ይፈተሻል?» አለ። «እንግዲህ መፈተሽ ትችላላችሁ አሉን ሁሉም ግልጽ ነው» በሚል ምስክሩ መለሱና በዚሁ ተጠናቀቀ።



አብዛኛዎቹ ምስክሮች የተባሉት ወይ የመንግሥት ሰራተኞች ናቸው፣ አልያም የቀበሌ፣ ከዚህ ካለፈም የወጣት ማህበራት አባላት ናቸው።

ከወጣቶች የቀረበው ምስክር ወጣት ግርማ ጫኔ የሚባል ነው። ሲመሰክር «መኢአድ ጽ/ቤት ስብሰባ ነበር፣ ወጣቶችና ደጋፊዎች ተገኝተዋል እኔም አባል ስለነበርኩ ተገኘሁ። አባይነህ ብርሃኑ፣ ማሙሸት አማረ፣ መስፍን አማን ሰብሳቢ ነበሩ። ሲናገሩም "የ97ን ምርጫ ቅንጅት አሸንፎ ኢህአዴግ አሸንፌያለሁ ማለቱ ስለማይቀር የሕዝባችንን ድምጽ ለማስከበር ተጽእኖ ለማድረግ፣ በሚሰጣችሁ መመሪያ መሰረት ተከተሉን" አሉና ወዲያው አንድ የአዲስ አበባ ዩኒቬርሲቲ ተማሪ ወረቀት አምጥቶ ስለነበር አባይነህ ተባዝቶ ይበተን ብሎ ለማባዣም 100 ብር ሰጠን ወረቀቱ "ጥሪ ከአ.አ. ዩኒቬርሲቲ" ይላል፣ ማሙሸት "ለተማሪዎች አስፈላጊውን እገዛ እናደርጋለን " በማለት ተናግሯል። በዚያ መሰረት በየቦታው ረብሻ ይካሄድ ነበር» በማለት መሰከረ።

ሌላዋ ወጣት በዚሁ ጉዳይ ላይ ስትመሰክር የተጭበረበረውን ድምጽ ለማስመለስ ከአ፡አ ዩኒቨርሲቲ የመጣ ወረቀት ተባዝቶ ተሰጠን፣መሳለሚያ የሚገኘው መኢአድ ጽ/ቤት ከምሰራበት አጠገብ ነው።»

«መኢአድ መሆኑን በምን አወቅሽ?» ተባለች።

«ብርሃኑ ነጋ እዚያ ሲመጣ አየዋለሁ በዚያ ነው ያወቅሁት» አለች። በነገራችን ላይ ብርሃኑ ወደዚያ ሰፈር ሄዶ አያውቅም። መስካሪዋ ስለቅንጅት አለማወቋ ወይም የቤት ሥራዋን አለመስራቷን ነው የሚያሳየው።

ሌላው ለየት ያሉት ምስክር ወደ ፍርድ ቤቱም ሲገቡ የጸሐይ መነጽራቸውን እንዳደረጉ ነው። ሥራቸው በዩኒቨርሲቲው የጥበቃ ሃላፊነት ነው።

በአዲስ አበባ ዩነቨርሲቲ ሁከት ተፈጠረ። ሕገ ወጥ ወረቀት ተበተነ። በ29/9/97 ከምሽቱ 5:30 ሲሆን 700 የሚሆኑ ተማሪዎች ጩኸት እያሰሙ የአካባቢውን ጸጥታ ረበሹት። ማን ይጀምር ማን ይከተል አልታወቀም። "እንድርያስ፣ መለስ ከስልጣን ይውረዱ፣ ዳኜ (እራሱን ነው) ይሰቀል፣ ኢሕአዴግ መሃይም፣ ቅንጅት ምሁራን ይሉ ነበር። በማግሥቱ ለፕሬዜዳንቱ

አሳወቅሁኝ፣ እሳቸውም ለሚመለከተው አሳወቁ:: በ29 የተበተነው ወረቀት ከመኢአድ ቅንጅት ይላል:: የሥራ ማቆም አድማ እንዲደረግ ለማህበራትና ለተማሪዎች የተላከ ጥሪ ነው::» በማለት «የምስክርነት ቃል» የተባለውን ሰጠ::

የ50 ዓለቃ ግዛው ደምቢ፣ በደብረ ብርሃን ነዋሪና የወህኒ ቤት ሰራተኛ ነው:: እሱ ግን ሥራውን ሲያስመዘግብ ጡረታ ወጥቻለሁ፣ 55 ዓመቴ ነው ብሏል::« ኢን/ ኃይሉ ሻውል፣ አባይነህ ብርሃኑ፣ ሻለቃ ጌታቸው መንግሥቴን በ97 ዓ/ም አዲስ አበባ መጥቼ ተዋወቅኋቸው:: በኢ/ር ኃይሉ የተፈረመ ወረቀት ሰዎች እንዳደራጅ ተሰጠኝ:: ማሙሸት ለትግሉ ሰዎች እየመረጥኩ እንዳደራጅ ባዘዘኝ መሰረት 13 ሰው መርጬ አደራጀሁ:: ከነዚህ 3ቱ ሽፍቶች ናቸው:: ኢህአዴግ ካሸነፈ እኛን ቅንጅቶችን ስለሚያጠፋ መልሰው ማጥፋት እንዲችሉ ነው ብሎ የቀን ወጪ 75 ብር ተሰጠኝ::» በዚህ ላይ የመስቀልኛ ጥያቄ መሰል ቀረበ:: «የማረሚያ ቤት ሃላፊ ሆነው ከሰዎቹ ጋር እንዴት ተዋወቁ?»

«በ90 ዓ/ም ከሥራ ታግጄ ነበር:: በ93 መኢአድ ገባሁ:: በዚህም ምክንያት አገኘኋቸው::

«እርስዎ አሁንም የወህኒ ቤት አዛዥ ነዎት፤ እና እንዴት የድርጅት አባል ሆኑ? ጡረታስ የወጡት መቼ ነው?»

«በ1997» ችሎቱ ውስጥ በዚህ መላ ቅዱሱ በጠፋ አመሰካከር የመገረም ሳቅ ሲሳቅ ዳኛ ልኡል በምስክሩ ግራ መጋባትና መዘባረቅ ተናደው ሳቁን ሰበብ አድርገው «ችሎቱን አታውኩ» አሉ:: የምስክሮቹ ብዛት የትየለሌ ቢሆንም ሁሉንም ለማስጠናትና እውነት የሚመስል አመሰካከር ለማድረግ ብቃት አልነበረም::

"በስልጤ ሰፈር የስልጤ አዳራሽ ውስጥ በተደረገው የ22/12/97 ስብሰባ ላይ ተገኝሁ የሚሉት ምስክር አቶ ተስፋዬ አይፎክሩ ደግሞ፤ «ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ፤ ዶ/ር በፈቃዱ ደግፌ፤ አርቲስት ደበበ እሸቱ መድረክ ላይ ሆነው ስብሰባውን ይመሩ ነበር:: በመጀመሪያ ስኔ 1 ለሞቱት ሰማእታት የሕሊና ጸሎት እናድርግ ብለው ተደረገ:: ከዚያም ዶ/ር በፈቃዱ በጣልያን ጊዜ ሕዝቡ በዶማ በአካፋ በድንጋይ ጠላትን



ተከላክሏል:: የኢትዮጵያ ሕዝብ በመብቱ ከመጡበት ወደኋላ አይልም ብለዋል፤ አዳራሹ ሞልቶ ውጪው ሁሉ ሰው ብቻ ነበር:: ከ5 እስከ 6ሺህ የሚሆን ሕዝብ ነበር (ይህ የሚያሳየው ሕዝብ ለቅንጅት ያለውን ፍቅር ብቻ ነው) አብዛኛው ሰው በሰላማዊ ሰልፍ፤ በአድማ እንታገላለን ፓርላማ አትግቡ ነበር የሚለው:: ውይይቱ ለረጂም ጊዜ ተካሂዶ አትግቡ የሚለው ድምጽ ስለበረታ ሰብሳቢዎቹ በመጨረሻ "ወደፊት ጥሪ ስለምናደርግ ተጠባበቁ" ብለው አሰናበቱን» በማለት ቋጬ::

የምስክሮቹ አይነት ይህን የመሰለ ነበር:: አሁንም ምስክር መሰማቱ ቀጥሎ በ24/2/99 በተካሄደው ችሎት በዳንኤልና በነጻነት ክስ ላይ የቀረቡት 3 ምስክሮች ብቻ ነበሩ:: አንዱ ሞቷል ተባለ:: ሌላው ምስክሩ ከአዲሱ ገበያ የመጣው ነው:: ሲመሰክርም «ነጻነትን አውቀዋለሁ አንድ ሰፈር ነን:: 'ቤተሰባችንም ይተዋወቃል:: ነጻነት ስለቅንጅትና ምርጫ ከነገረኝ በኋላ ወጣቶችን እንዳስተባብር መመርያ ሰጠኝ:: እኔም ያንን ስፈጽም ነበር:: በአካባቢው ያሉ ሁኔታዎችን ሁሉ ለጥፋት በሚያመች መንገድ ለማውደም መታገል እንዳለብን አስረዳኝ:: እኔም ለሰዎች ይህንኑ በማለት እቀሰቅስ ነበር:: ታክሲ ውስጥ፣ መንገድ ላይ፣ በመዝናኛ ቦታ የማገኛቸውን እቀሰቅስ ነበር:: በኋላ ግን ያደረግሁት ሁሉ ትክክል አለመሆኑን ስረዳ ተደብቄ ቆይቼ በመጨረሻ ለፖሊስ እጄን ሰጠሁ:: የሚልና ሌላም ለማመን እጅጉን አስቸጋሪ የሆነ ምንም ከምኑ የማይገናኝ የምስክርነት ቃሉን ሰጠ::

ዳንኤልና ነጻነት የተባለውን ሁሉ ካዳመጡ በኋላ መስቀልኛ ጥያቄያቸውን አቀረቡለት::

ነጻነት፣ "እንተዋወቃለን አይደለም? "

ምስክር፣ "አዎን "

ነጻነት፣ "የት? "

ምስክር፣ "አንድ ሰፈር ነን "

ነጻነት፣ "ማንን ነበር የምትቀሰቅሰው?"

ምስክር፣ "ያገኘሁትን"

ነጻነት፣ "ከሰፈር እነማንን ቀስቅሰሃል? "

ምስክር፣ "ከሰፈር አልቀሰቀስኩም"

ነጻነት፣ "ያገኘሁትን ብለሃል፣ የቀሰቀስከው ሳታውቃቸው ነው? እንዴት ታናግራቸዋለህ?"
ምስክር፣ "በቃ አያቸውና እጀምራለሁ"
ነጻነት፣ "ዝም ብለህ ድንገት? "
ምስክር፣ "አዎ!"
ነጻነት፣ "የት ነበር የተደበቅከው?"
ምስክር፣ "አንድ ቦታ ሄጀ ተደበቅሁ"
ነጻነት፣ "ቀበሌው የቤት ቁጥሩስ? "
ምስክር፣ "አላውቀውም"
ነጻነት፣ "የማን ቤት ነው?"
ምስክር፣ "አላውቃቸውም"
ነጻነት፣ "ከቤት ወጥተህ ለመደበቅ ስትሄድ ለማን ነገርክ"
ምስክር፣ "ለማንም"
ነጻነት፣ "በኋላስ ፖሊስ ምን አለህ?"
ምስክር፣ "በቃ፣ቃሌን ተቀብለው ስትፈለግ ትመጣብለው ለቀቁኝ"
ነጻነት፣ "እና የት ሄድክ?"
ምስክር፣ "ወደ ቤቴ ሄድኩ"
ነጻነት፣ "ይህን ለማን ነገርክ?"
ምስክር፣ "ለማንም"
ነጻነት፣ "አንተ በደህንነት መኪና ነበር የምትጠቀመው ሰፈር ስትገባ ስትወጣ አይይህ ነበር?"
ምስክር፣ "አይ አይደለም"
ነጻነት፣ "እናትህ ይህን ነገር ያውቃሉ? ከቤተሰብህ ይህን የሚያውቅ አለ? "
ምስክር፣ "የለም"
ነጻነት፣ "ከጓደኞችህ ከሰፈር ልጆችስ?"
ምስክር፣ "ማንም አያውቅም"
ነጻነት፣ "ዝም ብለህ የማታውቃቸውን ከማስተባበር ጓደኞችህ አይቀሉህም ነበር?"
ምስክር፣ "እኔ እነሱን አላስተባበርኩም"
ነጻነት፣ "ለመሆኑ ሥራህ ምንድን ነው?"



ምስክር፣ "የባህል እቃዎች እሸጣለሁ"
ነጻነት፣ "የት ነው ሱቅህ? "
ምስክር፣ "ሱቅ የለኝም አከፋፋይ ነኝ" .. .. .. .. .. ..

ይሄ ነው ዋነኛ ምስክር ተብሎ የቀረበው:: ምኑም ከምኑ የማይያዝ፣ የማይገናኝ:: በ24/2/99 ጠዋት የተጀመረው የምስክር ማሰማት ቀጥሎ ከሰአትም ተካሄደ:: የቀረቡት ምስክሮች በአብዛኛው በሚቀርብላቸው መስቀልኛ ጥያቄ ድንብርብራቸው እየወጣ የተጠየቁትን ከመመለስ ይልቅ ንዴትና ብስጭት ሲታይባቸው ነበር:: ነጻነትም ሆነ ዳንኤል የበቁ የሕግ ባለሙያዎች በመሆናቸው ምስክሮቹ እንደታሰበው ቀላል አልሆነላቸውም:: አንድ ጊዜ መዋሸት ይጀምሩና ያንን ለማስተካከል ውሸት በውሸት ነው የሚሆኑት::

እንደገና ለ27/2/99 ተቀጠረ:: በዚህ እለት የነበረው የምስክሮች ሁኔታ የፍርድ ሂደቱን ያበላሸ አቃቤ ሕጎቹ በሚገባ ምስክሮቻቸውን ሳያስጠኑ ያቀረቧቸው መሆናቸውን፣ ምስክሮቹም ለተገባላቸው ቃል ለመቆም ያልቻሉ ሆነው ነው የዋሉት:: ዳንኤልና ነጻነት ቅዳሜ እለት ከዘወትር የዘመድ መገናኛ ቦታቸው አልነበሩም:: በኋላ፣ በበነጋው ከቤተሰብ እንደተሰማው ጭለማ ቤት አዛውረዋቸዋል:: ችግር ተፈጥሮባቸዋል:: ወህኒ ቤቱ በመስቀለኛ ጥያቄው አቃቤ ሕጎቹ ድል በመመታታቸው ተናዷል::
ሰኞ በ27/2/99 በዋለው ችሎት ዳንኤልና ነጻነት ጥሩ ሁኔታ ላይ አልነበሩም:: በቂ እንቅልፍ እንዳልተኙና ችግር እንደገጠማቸው ነገሩን:: ይህንንም ለፍርድ ቤቱ ሲያስረዱ፣

«የተከበረው ፍርድ ቤት! ለፍትሓዊ ዳኝነት ለታሠሩ ተገቢ አያያዝ ያስፈልጋል:: ባለፈው ቀጠሮ በቀረቡት ምስክሮች ላይ መስቀልኛ ጥያቄ በማቅረባችን ግፍ ተፈጽሞብናል:: ከችሎት እንደተመለስን ከነበርንበት ዞን ተወስደን ኮንቴይነር ውስጥ በጭለማ ካደርን በኋላ፣ በፊት ከነበርንበት 20 ሰው ካለበት ማደርያ ወደ 250 እስረኞች ወዳሉበት ተዛወርን:: የስነ ልቡና ጦርነት ነው የተካሄደብን:: መስቀልኛ ጥያቄ ስላቀረብን እንጂ ሌላ ምንም ሰበብ የለውም:: የቤተሰብ ጥየቃ ተከለከልን፣

ሲፈቀድም የአንድ ቤተሰብ አባላት በመሆናችንና አሁን ለያይተው ስላሰሩን ቤተሰባችንም ለጥየቃ ችግር ተፈጥሮበታል፤ ግፍ ነው። በአንድ ላይ ሊጠይቁን አልቻሉም። ክቡር ፍርድ ቤት፣ በዚህም የተነሳ ዛሬ ስነልቡናዊ ጉዳት ላይ ስለሆንን ማመሳከር አንችልም። አሁንም ክቡር ፍርድ ቤቱ ችግራችንን ተረድቶ በመከራከራችን የደረሰብንን ጉዳት በማየት ወደነበርንበት ቦታ እንድንመለስ እንዲያደርግልን በፍትሕ ስም እንለምናለን» በማለት አቤት አሉ።

አቃቤ ሕግ «አሁን እየሰማን ያለነው የኛ ጉዳይ አይደለም፤ ስለ ቅሬታውና ስሞታው ማረሚያ ቤቱ ሳይጠየቅ ውሳኔ መስጠቱ ልክ አይደለም። ማረሚያ ቤቱ የራሱ አስተዳደራዊ ሥልጣን አለው» በማለት ተቃውሞ አቀረበ።

ፍርድ ቤቱም «ማረሚያ ቤቱ የራሱ አስተዳደሪያዊ ሥልጣን ቢኖረውም የተወሰደው እርምጃ ትክክል ስላልሆነ ማረሚያ ቤቱን አንጠይቅም። የተወሰደው ሕገወጥ እርምጃ ነው ወደነበሩበት ዞን እንዲመለሱ በጥብቅ አዘናል የሚቀጥለው ለ30/2/99 ተቀጥሯል» በማለት ችሎቱ አበቃ።

እያንድንዱ የቀረበ የአቃቤ ሕግ ምስክር ለሚቀርብለት ጥያቄ መልስ በሚሰጥበት ጊዜ በንጹት የሚንተከተክ ይምሰል እንጂ የሚናገረውን ሃሰት እውነት ለማስመሰል በሚያደርገው ጥረት በውስጡ ያደረበት ጭንቀት ያስታውቃል። በቅድሚያ አቃቤሕግ ነው ላቀረበው ምስክር ጥያቄ የሚያቀርበው። ከሶስቱ አቃብያን አንደኛው ተመርጦ ነው ጥያቄውን የሚያቀርበው። ዐቃቤ ሕግ አብርሃም ተጠምቀ፣ የፍርድ ቤት የችሎት ሂደት ለብዙ ወራት ሲካሄድ ሊማር ሲችል አንዳችም የአቀራረብ ለውጥ አላየንበትም ከነበረበት ደረጃ 75 በመቶ ወርዶ ነው ያገኘሁት። እሱም እንደምስክሮቹ ነው። የሱን ደግሞ ከምስክሮች የሚለየው እያንዳንዳችንን የሚያይበት የጥላቻ መንፈስ ነው። አቃቤ ሕግ ለሕግ ፍትሓዊነት የሚቆም፣ እንዲያውም ለተከሳሽ ወገን የሚያደላ ሲባል የሰማሁትን አጥፍቶብኝ፣ ጭርሱን በዚያ ፍርድ ቤት ያለነውን ተከሳሾች በሙሉ አውጥቶ አጅበውን ከተቀመጡት



ፖሊሶች አንዱን ክላሽ ቀምቶ ቢረፈርፈን ደስታው ነበር የሚመስለው። ለነገሩ ሁሉም ዐቃቤዎች ተከፋፍለውን ግድግዳ እያስደገፉ በጥይት ቢጨርሱን ደስታቸው ነበር።

አቃቢያኑም ሆኑ ዳኞች ነጻ ሆነው፣ ለማንም ሳይወግኑ ለፍትህ ሚዛናዊነት በመቆም ሊፈርዱ ሊዳኙ ሲገቡ፣ ገና ተሰይመው ከመቀመጣቸው፣ ዳኞቹ ጥላቻቸውን ያሳያሉ። ከመድረኩ ላይ ተቀምጠው ቁልቁል ሲያዩን በአንዲት ደቂቃ ውሳኔ ከመኖር ወዳለመኖር ሊለውጡን እንደሚችሉ እያሰቡ፣ አልፎ አልፎ ሳያውቁት ፈገግ ይላሉ።

አቃቢያኑ "ለፈገግታ ያልታደሉ ናቸው" ማለት እችላለሁ። ለ21 ወራት ግድም ሳያቸው አንድም ቀን ያላየሁት ደህና ፊታቸውን ነው። ገና ወደ ፍርድ ቤቱ አዳራሽ ሲገቡ ኩራት አይሉት ሃፍረት ፊታቸውን ይከሰክሱና መጥተው በሰተግራችን ያስቀምጣቸዋል። አስተያየታቸው የጠላት፣ ስሜታቸው የጥላቻ መሆኑ በፊታቸው ይነበባል። ምስክሮቻቸውን በሚገባ ሳያስጠኑ ስለሚያመጧቸው የሚናገሩት እየጠፋቸው አራምባና ቆቦ ሲረግጡ ምስክሮች የዘላበዱትን መሰረት በማድረግ ከተከሳሾች አንዳንዶች መስቀልኛ ጥያቄ በሚያቀርቡበት ጊዜ አቃቢያኑ «ጉድ ሊያደርጉን ነው» በሚል ስሜት ሳያስፈቅዱ ድንገት ብድግ በማለት «ተቃውሞ!» ብለው ይጮሃሉ ዳኛ አዲልም ይፈቅዱላቸዋል።መፍቀድ ብቻ ሳይሆን ካዳመጡ በኋላ ተቃውሞውን በመቀበል ትእዛዝ ይሰጣሉ በዚህም ጥያቄው ይስተጓጎላል።ዳኛ አዲል « በተነሳ ጭብጥ ላይ ብቻ» በሚል መስቀለኛ ጥያቄውን ያቋርጡታል።

ለቀረበው ተቃውሞ፣ ተከሳሽ ያቀረበው ጥያቄ ከጭብጡ ያልራቀ መሆኑን ለማሳመን ገና ለንግግር አፉን ሲከፍት፣ ዳኛ ልኡል ጣልቃ በመግባት «በስነስርአት እንሂድ እንጂ! ከጭብጡ ወጥቷል ከተባለ ያንን መተውና ወደ ጭብጡ መግባት ነው የሚሻለው» በማለት የተነሳው ርእስ እንዲቋረጥ መመሪያቸውን ያጠናክራሉ።